# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 087 ኅዳር 27 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ - ገበሀ ገብሬ

# የኢፌዴሪ አየር ኃይል የበርካታ ትጥቆችና ብቁ አብራሪዎች ባለቤት ሆኗል

- ተቋሙ 88ኛ ዓመት የምስረታ በዓሉን በተለያዩ ዝግጅቶች እያከበረ ይገኛል
- 26 የአፍሪካ ሀገራት የሚሳተፉበት መርሀ ግብርም ይካሄዳል


ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- የኢፌዴሪ አየር ኃይል የበርካታ ትጥቆችና ብቁ አብራሪዎች ባለቤት መሆኑን የአየር ኃይሉ ዋና አዛዥ ሌተናል ጄነራል ይልማ መርዳሳ ተናገሩ። ተቋሙ ከኅዳር 20 ጀምሮ 88ኛውን የምሥረታ በዓል በልዩ ልዩ መርሀ ግብሮች እያከበረ ሲሆን 26 የአፍሪካ ሀገራት የአየር ኃይል አዛዦችና የአቪዬሽን ኩባንያዎች የሚሳተፉበት መርሀ ግብርም እንደሚኖር ተጠቁሟል፡፡

ከኅዳር 20 ጀምሮ በተለያዩ ዝግጅቶች እየተከበረ የሚገኘውን የኢፌዴሪ አየር ኃይል የምሥረታ በዓል አስመልክቶ መግለጫ የሰጡት የአየር ኃይሉ ዋና አዛዥ ሌተናል ጄነራል ይልማ መርዳሳ፤ አየር ኃይሉ በተለይ ከለውጡ በኋላ የበርካታ ትጥቆችና ብቁ አብራሪዎች ባለቤት ሆኗል ብለዋል፡፡

የኢፌዴሪ አየር ኃይል የሰው ኃይል ልማት ግንባታ ላይ

የኢፌዴሪ አየር ኃይል ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል





## «የፀጥታ ችግር የነበረባቸው አካባቢዎች አንጻራዊ ሰላም አግኝተዋል»

- መንገሻ ፈንታው(ዶ/ር) የአማራ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል የፀጥታ ችግር አጋጥሟቸው የነበሩ የክልሉ አካባቢዎች አንጻራዊ ሰላም ማግኘታቸውን የአማራ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ አስታወቀ፡፡

«የፀጥታ ችግር ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## ለዓባይ ግድብ እስካሁን ከ18 ቢሊዮን ብር በላይ ተሰብስቧል

አዲሱ ገረመው



አዲስ አበባ፡- ለዓባይ ግድብ ግንባታ ገቢ ማሰባሰብብ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ከ18 ቢሊዮን ብር በላይ ከኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን እንደተሰበሰበ የግድቡ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት አስታወቀ፡፡

የዓባይ ግድብ ግንባታ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት የሕዝብ ግንኙነትና ሚዲያ ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ኃይሉ አብርሃም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ለግድቡ ግንባታ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፉን አጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ ኅብረተሰቡ ለ13

ለዓባይ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



## ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ በ50 ሚሊዮን ዶላር የትራክተር ፋብሪካ ሊገነባ ነው

ዳግማዊት ግርማ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ በሞጆ ከተማ በ50 ሚሊዮን ዶላር የትራክተር ፋብሪካ ሊገነባ መሆኑን አስታወቀ፡፡ ድርጅቱ ለውጭ ገበያ አዳዲስ ሞዴል ያላቸውን መኪናዎች የማቅረብ ዕቅድም አለው ተብሏል።

የተቋሙ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አምባሳደር ሱለይማን ደደፎ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሃምሳ ሚሊዮን ዶላር ወጪ በአፍሪካ ደረጃ ትልቅ ሊባል የሚችል የትራክተር ፋብሪካ ሞጆ ላይ ሊገነባ ነው፡፡

ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል







# በቀጣይ አምስት ቀናት የሚኖረው የአየር ሁኔታ የደረሱ ሰብሎችን ለመሰብሰብ አመቺ ነው

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- በቀጣይ አምስት ቀናት የሚኖረው የአየር ሁኔታ የመኸር ሰብል አሰባሰብ ላይ ለሚገኙ አካባቢዎች አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡ በተወሰኑ የሀገሪቱ ክፍሎች ደግሞ ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እንስ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚጠበቅ ተገልጿል።

ኢንስቲትዩቱ በቀጣይ ጊዜያት የሚከሰተውን የአየር ፀባይ አዝማሚያ አስመልክቶ ለኢፕድ በላከው መግለጫ እንዳመላከተው፤ በቀጣይ አምስት ቀናት የሚኖረው የአየር ሁኔታ በተለይም ለመኸር ሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ላይ ለሚገኙ አካባቢዎች አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ፤ አርሶ አደሮች ይህንኑ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም በማሳ ላይ የሚገኙና የደረሱ ሰብሎችን በወቅቱ መሰብሰብ ይገባዋል።

በተጨማሪ በመስኖ የሚለሙ ሰብሎች፤ አትክልት፣ የፍራፍሬ ተክሎችና የመኸር ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ለዋግ መፈጠር ምቹ ሁኔታዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ አርሶ አደሮች ዘግይተዉ በተዘሩ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልገው በመግለጫው ተመላክቷል፡፡

እንዲሁም በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብና የበጋው ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ አጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚጠበቅ ተጠቁሟል፡፡

በሰሜን፤ በሰሜን ምዕራብና በመካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖር ኢንስቲትዩቱ ገልጿል።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አምስት ቀናት የኦሮሚያ፣ የአማራ፣ የደቡብ ኢትዮጵያ፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆን፤ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ ተብራርቷል።

እንደ መግለጫው ከሆነ፤ በመጪው የታህሳስ ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በዋነኛነት የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔተ ይስተዋልባቸዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተየይዞ በአንዳንድ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ሊጠናከር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡

በተጨማሪም በዚሁ ወር አልፎ አልፎ በሚኖሩ ቀናት ለዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገፅታዎች በመጠናከራቸው፤ በምዕራብና በደቡብ ኦሮሚያ፣ ከጋምቤላ ክልል የተወሰኑ አካባቢዎች፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚያገኙ ተመላክቷል።

የአየር ፀባይ ሁኔታ የውኃ ሃብትን ከማጎልበት አንጻር አዎንታዊ ሚና ስለሚኖረው የሚገኘውን እርጥበት በአግባቡ በማጠራቀም ለሃይል ማመንጫ፣ ለመስኖና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት መጠቀም እንደሚያስፈልም ኢንስቲትዩቱ ጠቁሟል።

# "ለሀገራዊ ምክክሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ ነን"

\- ዲያስፖራዎች

**ሳሙኤል ወንደሰን**



ወይዘሮ አዜብ አልፈሪድ



አቶ ኤርሚያስ መኮንን



ኡስታዝ ጀማል በሽር

ፎቶ፡- እዮብ ተፈሪ

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ለሚካሄደው ሀገራዊ ምክክር አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን ዲያስፖራዎች ገለጹ።

በአሜሪካ ቨርጂኒያ የሚኖሩት ኡስታዝ ጀማል በሽር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በርካታ ትውልደ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ ምክንያቶች ከኢትዮጵያ ውጪ ይኖራሉ። አካላቸው ከኢትዮጵያ ውጪ ይገኝ እንጂ ልባቸው ከኢትዮጵያ ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ለሀገራዊ ምክክሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ መሰረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የሃሳብ ልዩነትና አለመግባባት የሚታይ በመሆኑ በርካታ ችግሮች በሀገሪቱ ተከስተዋል ያሉት ኡስታዝ ጀማል፤ ይህንን ልዩነትና አለመግባባት ለመፍታት የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ተቋቁሟል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን ሰላም፣ አንድነት፣ መተማመን እና የተሸረሸሩ ማኅበራዊ እሴቶችን ለማደስ የሚሰራውን ሥራ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊደግፍና ሊያበረታታ እንደሚገባ ገልጸው፤ ከዚህ አንፃር ዲያስፖራው ለምክክር ኮሚሽኑ ማድረግ የሚጠበቅበትን ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን ተናግረዋል።

አቶ ኤርሚያስ መኮንን በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ኮሚሽነሮች በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ የዲያስፖራ ማኅበር አባላት ጋር በሚሊኒየም አዳራሽ ተወያይቷል። በዚህም የዲያስፖራው ማኅበረሰብ በሀገራዊ ምክክሩ እንዴት መሳተፍና ምን ማድረግ እንዳለበት እንዲሁም ኮሚሽኑ ከተቋቋመበት ጊዜ አንስቶ ምን ምን ሥራዎችን እንዳከናወነ ገለፃ መደረጉን አውስተዋል።

ዲያስፖራው በሀገሪቱ ኢኮኖሚ፣ ማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሁሌም ተሳታፊ ነው። በተለይ አሁን ላይ በሀገራዊ ምክክሩ ላይ ንቁ ተሳታፊ ሊሆን ይገባል ያሉት አቶ ኤርሚያስ፤ "ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑ ከእኔ የሚፈልገውን እና የሚጠብቀውን ለማድረግ ዝግጁ ነኝ" ብለዋል።

ትውልደ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ ሀገራት ይገኛሉ። ከዚህ አንፃር በሚኖሩበት አካባቢ የተለያዩ እውቀቶችን፣ ልምዶችንና ቴክኖሎጂዎችን የማግኘት እድል ገጥሟቸዋል። ይህንን ለኢትዮጵያ እድገት፣ ሰላም እና አንድነት መጠቀም ይኖርባቸዋል። ዲያስፖራው የኢትዮጵያ ሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን የተቋቋመበትን ዓላማ በመረዳት ልዩ ድጋፍ ማድረግ እንዳለበትም አስገንዝበዋል።

በአሜሪካ ሀገር ለ38 ዓመታት እንደኖሩ እና አሁን ደግሞ በኢትዮጵያ የሕፃናት ማቆያ ትምህርት ቤት ከፍተው እየኖሩ መሆናቸውን የገለጹት ደግሞ ወይዘሮ አዜብ አልፈሪድ ናቸው።

እንደ ወይዘሮ አዜብ ገለፃ፤ ሀገራዊ ምክክር ለኢትዮጵያ ውሳኝ ነው። መነጋገር፣ መደማመጥ እና መግባባት አስፈላጊ ነው። የሕፃናት ማቆያ ትምህርት ቤት የከፈትኩትም ልጆች መግባባትና መደማመጥ ቀዳሚ ምርጫቸው እንዲያደርጉት በማሰብ ነው። መነጋገርና መግባባት የነገሮች ሁሉ ቁልፍ ነው። ስለዚህ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ይህንን በሰከነ ልብ ማገናዘብ ይኖርበታል።

ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የሚጠበቅባቸውን ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን የገለጹት ወይዘሮ አዜብ፤ የሀገሪቱ ሰላምና ልማት እንዲረጋገጥ ዲያስፖራው እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ የበኩሉን ሚና እንዲወጣ አሳስበዋል።

# የቃሊቲ-

## ቱሉ ዲምቱ መንገድ በሦስት ወራት ይጠናቀቃል

**አመለወርቅ ከበደ**



አዲስ አበባ፡- የቃሊቲ -ቱሉ ዲምቱ መንገድ ግንባታን በሶስት ወራት ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ ርብርብ እየተደረገ እንደሚገኝ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን አስታወቀ፡፡

በአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ እያሱ ሰሎሞን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የቃሊቲ -ቱሉ ዲምቱ መንገድ ግንባታ በተለያዩ ምክንያቶች ቢዘገይም፤ በድጋሚ ተጀምሯል፤ አሁን ባለው ሂደትም በሶስት ወራት ለማጠናቀቅ ርብርብ እየተደረገ ነው፡፡

የመንገድ ግንባታ ሥራው አሁን ላይ 78 በመቶ እንደደረሰ የገለጹት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው፤ የግንባታ ሥራው ባለፈው ዓመት በሙሉ አቅም ሲሠራ ቆይቶ ፤ የመንገዱ የግራና ቀኝ ክፍል ለትራፊክ አገልግሎት ክፍት መደረጉን አስረድተዋል፡፡

በአንዳንድ ቦታዎች የመጨረሻ የአስፋልት ንጣፍ ሥራ ፤ የእግረኛ መንገድ ግንባታ፤ የመንገድ ዳር መብራት የማስገባት እና የድጋፍ ክንፎችን የማስገባት ተግባር እየተከናወነ ይገኛልም ብለዋል፡፡

አቶ እያሱ እንደተናገሩት፤ የመንገድ ፕሮጀክቱ 11 ኪሎ ሜትር ርዝመት እና 50 ሜትር ስፋት እንዲኖረው ተደርጎ በቻይና ኮንስትራክሽን ኮሚኒኬሽን አማካኝነት ግንባታው እየተከናወነ ይገኛል፡፡

ፕሮጀክቱ ትላልቅ የትራፊክ ማሳለጫ ድልድዮች እየተገነቡለት የሚገኝ ሲሆን ፤ በከተማው ከሚገኙት ስድስት ትላልቅ የትራፊክ ማሳለጫ ድልድዮች ሶስቱ በዚህ የመንገድ ፕሮጀክቶች ላይ እንደሚገኙም ተናግረዋል፡፡

ከድልድዮቹም አንዱ ቃሊቲ ማሰልጠኛ አካባቢ ባለው ቀለበት መንገድ ላይ የሚገኝ ሲሆን 240 ሜትር ርዝመት አለው፡፡ ሁለተኛው ወደ አቃቂ ከተማ በስር በኩል ከሚያስተላልፈው መንገድ በላይ በኩል የሚገነባ የትራፊክ ማሳለጫ ድልድይ ሲሆን 90 ሜትር ርዝመት አለው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ሦስተኛው የትራፊክ ማሳለጫ ድልድይ የሚገኘው በተለምዶ ጋሪ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ሲሆን፤ 50 ሜትር ርዝመት አለው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

የመንገድ ፕሮጀክቱ ከሚሸፍነው ርዝመትና ስፋት አንጻር፤ እየተገነቡ ከሚገኙት የትራፊክ ማሳለጫ ድልድዮች ትልቅ የሚባል እንደሆነ የገለጹት ኃላፊው፤ የፕሮጀክቱ አጠቃላይ በጀት 2 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር መሆኑንና የሚሻሻል ሂሳብ ካለ ወደፊት የሚገለጽ ይሆናል ብለዋል፡፡

አቶ እያሱ እንደተናገሩት፤ የመንገድ ግንባታው ከቻይና ኤግዚም ባንክ በሚገኝ የገንዘብ ብድር የተጀመረ ሲሆን፤ ባንኩ ገንዘቡን ለተቋራጩ በጊዜ መክፈል ባለመቻሉ ሊዘገይ ችሏል፡፡ ሆኖም መንግሥት ወጪውን በመሸፈኑ የገንዘብ ችግሩ ሊቀረፍ ችሏል፡፡

በተጨማሪ የቀድሞ መንገድ ጠባብ በመሆኑ አዲሱን የመንገድ ግንባታ ለማስፋት መነሳት የነበሩባቸው ቤቶችና መሰረተ ልማቶች መነሳት ነበረባቸው፡፡ በተለይም በመንገዱ የግራ ክፍል የሚገኘውን ከፍተኛ የውሃ መስመር ለማንሳት ከውጭ የሚገቡ እቃዎች በመዘግየታቸው የመንገድ ግንባታው ሊጓተት ችሏል ብለዋል፡፡

መንገድ መገንባቱ ብቻ ዋጋ የለውም ያሉት አቶ እያሱ፤ ኅብረተሰቡ የተሰራውን መንገድ ለታለመለት ዓላማ በመጠቀም ለመንገዱ ደኅንነት ኃላፊነቱን እንዲወጣም አሳስበዋል፡፡

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር
MINISTRY OF IRRIGATION AND LOWLANDS

# የታችኛው ርብ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ግንባታ ዘንድሮ ይጠናቀቃል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ ፡- በአማራ ክልል ደቡብ ጎንደር ዞን እየተገነባ የሚገኘው የታችኛው ርብ መስኖ ልማት ፕሮጀክት በተያዘው በጀት ዓመት እንደሚጠናቀቅ የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት እና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ ብዙነህ ቶልቻ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤በአሁኑ ጊዜ የታችኛው ርብ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ግንባታ 89 ነጥብ 92 በመቶ ደርሷል፡፡ ግንባታው በተያዘው በጀት ዓመት ለማጠናቀቅ ታቅዶ እየተሠራ ነው፡፡

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሀገሪቱ ከሚያከናውናቸው የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች አንዱ የሆነው የታችኛው ርብ መስኖ ልማት ፕሮጀክት በአንድ ነጥብ 93 ቢሊዮን ብር እየተከናወነ እንደሚገኝ አንስተው፤ፕሮጀክቱ ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅ ሶስት ሺህ 741 ሄክታር መሬት ማልማት የሚችል መሆኑን ተናግረዋል።ይህም ከስድስት ሺህ በላይ የአካባቢው ነዋሪዎችን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ አቶ ብዙነህ አስታውቀዋል፡፡

የፕሮጀክት የግንባታ ሥራ ዓባይ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ እንደሚከናወን አመልክተው፤ የማማከርና የቁጥጥር ሥራውን የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ሥራዎች ኮርፖሬሽን እየተሰራ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

በግንባታ ሂደቱ በአካባቢው ወሰን ማስከበር ብሎም የሥራ ተቋራጭ አቅም ውስንነት እና ያለበቂ ምክንያት ሥራ ማቆም እንደተግዳሮት የሚጠቀስ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

የመስኖ ፕሮጀክቱ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሄክታር መሬት ለማልማት ብሎም የግጦሽ ማሻሻያ እና የተራቆቱ ቦታዎችን መልሶ እንዲያገግሙ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑን ገልጸው፤ የአካባቢው ማኅበረሰብ ዝናብ ጠባቂ ከመሆን ይልቅ የተለያዩ የመስኖ አማራጮችን በመጠቀም የተለያዩ ምርቶችን በማምረት ተጠቃሚ መሆን እንደሚያስችል ነው የገለጹት፡፡

በዓመት ከ2 እስከ 3 ጊዜ በላይ በማምረት ከዝናብ የሚገኘውን ምርት እስከ ስድስት እጥፍ ሊያሳድግ የሚችል መሆኑን ጠቁመው፤ እንደሀገርም ያሉ የግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች(አግሮ-ኢንዱስትዎች) በቀላሉ የጥሬ ዕቃ ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ እንደሚፈጥር አመልክተዋል፡፡

አቶ ብዙነህ እንደገለጹት፤ ጥቅምት 2008 ዓ.ም የተጀመረው ይህ ፕሮጀክት በተያዘለት ጊዜ ለማጠናቀቅ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ባለሙያዎችን በመመደብ በቅርበት የክትትል እና ድጋፍ እያደረገ ነው፡፡ በተጨማሪም በየጊዜው ከሥራ ተቋራጩና አማካሪ ድርጅቶቹ ጋር የሦስትዮሽ ውይይቶችን በማድረግ ግንባታው የሚጠናቀቅበት ጥረት እያደረገ ነው ብለዋል፡፡

# አራት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጠ

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በሀዋሳ ከተማ 2016 የበጀት ዓመት በመጀመሪያው ሩብ ዓመት በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች አራት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠቱን የከተማው የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ጽሕፈት ቤት አስታወቀ፡፡



የሀዋሳ ከተማ ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ታደሰ ፍቅሬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ሥራ ዘርፎች አራት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ካፒታል ላስመዘገቡ 12 የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች አዳዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡

ፈቃድ ለጠየቁ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በኢንዱስትሪ፣ በሆቴሎች፣ በሎጅ እንዲሁም ሌሎችም አገልግሎት ሰጪ ዘርፎች እንዲሰማሩ ፈቃድ መሰጠቱን ጠቅሰዋል፡፡

ሀዋሳን ለኢንቨስትመንት ምቹ ለማድረግና ዘርፉን ለማስፋፋት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶችን በተለያዩ ዘርፎች እንዲሰማሩ ሰፊ ሥራዎች ተሠርተዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ባለሀብቶች በተለያዩ ዘርፎች ተሰማርተው ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩ ለማስቻል የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም የኢንቨስትመንት ዕድሎችን የማስተዋወቅ ሥራ እየተሠራ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

ወደ ከተማው በርካታ ባለሀብቶችን ለመሳብ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ገልጸው፤ የኢንቨስትመንት ማስፋፊያ ጽህፈት ቤቱ ወደ ሀዋሳ ለሚመጡ አልሚዎች አስፈላጊ ድጋፎችን እንደሚያደርግ አመልክተዋል፡፡

ጽህፈት ቤቱ በቀጣይ ተጨማሪ የሀገር ውስጥና አዳዲስ የውጭ ሀገር ባለሀብቶችን ለመሳብ የሚያስችል ዝርዝር ጥናት በማድረግ ለኢንቨስተሮች እያቀረበ መሆኑን የጠቆሙት ኃላፊው፤ ለአልሚዎችም ከ70 ሄክታር በላይ መሬት ማዘጋጀቱን አስታውቀዋል።

በኢንቨስትመንት ስም መሬት ወስደው ሳያለሙ ቦታውን አጥረው የሚያቆዩና በዕቅዳቸው መሰረት ወደ ሥራ ያልገቡ ባለሀብቶችን የኢንቨስትመንት የሊዝ አዋጅና መመሪያው በሚፈቅደው መሰረት ክትትልና ድጋፍ እንደሚያደርግ አስረድተዋል።

ለብዙ ጊዜ መሬታቸውን ሳያለሙ የቆዩትን እየለዩ መሆኑን ጠቁመው፤ ቦታቸውን ወደ መሬት ባንክ በማስገባት ለሚያለሙ ባለሀብቶች የማስተላለፉ ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ገልጸዋል።

የሐዋሳ ከተማን የኢንቨስትመንትና የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎች ከተለያዩ ቢሮዎች ጋር በቅንጅት እየተሰራ መሆኑን አቶ ታደሰ አመልክተዋል።


# ኮሚሽኑ ገበያን ለማረጋጋት በሚያደርገው ጥረት የባለድርሻ አካላትን ድጋፍ ጠየቀ

- በመዲናዋ በ170 የቅዳሜና እሁድ ገበያ ማዕከላት አገልግሎት እየሰጡ ነው
- ኮሚሽኑ 154 ሸማች ማኅበራትና 200 መዝናኛ ክበባትን ያስተባብራል

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- የሸማች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ገበያን ለማረጋጋት በሚያደርጉት ጥረት የባለድርሻ አካላት ድጋፍ መጠናከር እንደሚገባው የአዲስ አበባ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን አስታወቀ።

በኮሚሽኑ ስር የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት ለመዲናዋ ነዋሪ መሠረታዊ የፍጆታ እቃዎችን በተሻለ ዋጋ እንዲያገኝ እየሰሩ ያሉ ቢሆንም ኅብረተሰቡ የሚፈልገውን ያህል ግብዓት ማቅረብ አለመቻላቸውን የኮሚሽኑ የገበያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ሙሉሸዋ በቀለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገልጸዋል። ማኅበራቱ የሚገጥማቸውን የምርት አቅርቦት እጥረት በዘላቂነት ለመፈታት ከአርሶአደሮችና ከአምራች ኢንዱስትሪዎች ጋር የትስስር ስምምነቶችን በማድረግ እየሰራ እንደሆነ የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፤ በቀጣይም ከኢንዱስትሪ ባለቤቶች ጋር የሚያደርገውን ትስስር አጠናክሮ እንደሚቀጥልም ጠቁመዋል፡፡ እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፣ ትስስሩ በዋናነት ኢንዱስትሪዎችና አምራቾች ምርቶቻቸውን በቀጥታ ለኅብረት ሥራ ማኅበራቱ እንዲያቀርቡ የሚያስችል ሲሆን፤ ይህም በሸማቹና በአምራቹ መካከል በሚኖር ረጅም



**አቶ ሙሉሸዋ በቀለ**

ሰንሰለት ሳቢያ በምርቶች ላይ ሊኖር የሚችለውን የዋጋ ጭማሪ በማስቀረት ኅብረተሰቡ መሠረታዊ ፍላጎቶቹን ከሌላው ገበያ በተሻለ ዋጋ እንዲያገኝ የሚያግዝ ነው፡፡

በከተማዋ በተለያዩ አካባቢዎች 170 የቅዳሜና እሁድ ገበያ ማዕከላት መኖራቸውን የጠቀሱት ዳይሬክተሩ፤ ከከተማዋ ነዋሪ አንጻር የአቅርቦት ውስንነት ቢኖርም ኅብረተሰቡ አመኔታን የጣለባቸው ገበያዎች እየሆኑ እንደመጡና በማንኛውም ሁኔታ ከማኅበራቱ የሚሰጠውን አገልግሎት ማጣት እንደማይፈልግ ነዋሪው ከሚሰጠው ምላሽ መረዳት እንደተቻለም ገልጸዋል።

ኮሚሽኑ በሥሩ የሚገኙ 12 ማኅበራት፣ 154 መሠረታዊ ሸማች ማኅበራትና ከ200 በላይ መዝናኛ ክበባትን በማስተባበር ምርት ከነበረበት ዋጋ በምንም ምክንያት ከፍ ብሎ እንዳይሄድና ቀድሞ በተተመነለት ዋጋ እንዲሸጥ ለማድረግ እየሠራ እንዳለ አስታውሰው፣ በገበያው ውስጥ የሚታየው መተረማመስ ማኅበራቱ ከሌላው ገበያ በተሻለ ዋጋ ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግና ሚዛናዊ ገበያ እንዲኖር የሚያደርጉትን ጥረት እየፈተነው እንዳለ ተናግረዋል፡፡ የከተማዋ ገበያ በኮሚሽኑ ጥረት ብቻ መረጋጋት የሚችል አይደለም ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የገበያ ሰንሰለቶችን በማሳጠርና የምርት ቁጥጥር በማድረግ ረገድ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የክልል መስተዳድሮች፣ ኢንዱስትሪዎችና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ለማኅበራቱ ሲያደርጉ የነበረውን ድጋፍ የበለጠ በማጠናከር ገበያን ለማረጋጋት በሚደረገው ጥረት ሚናቸውን እንዲወጡ ጠይቀዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሙስሊሙ ማኅበረሰብ ለፈጠረው አንድነትና ለመንግሥት ጥረት እውቅና መሰጠቱ ተገቢ ነው!

ሙስሊሙ ማኅበረሰብ በሀገሪቱ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ህይወት ውስጥ ትልቅ ስፍራ ያለው ፤ በሀገረ መንግሥት ምስረታ ሆነ ፣ ሀገረ መንግሥቱን በማጽናት የዘመናት ታሪክ ውስጥ ሰፊ ታሪክ የጻፈ ነው። ሃይማኖቱ ያጎናጸፉትን መንፈሳዊ እሴቶች ፤ ይዟቸው ከዘለቃቸው ባህላዊና ማኅበራዊ እሴቶች ጋር በማስተሳሰር ለራሱ ፣ ለማኅበረሰቡና ለሀገሩ የሚተርፉ ትውልድ በመፍጠር ፤ ሀገር እንደሀገር ዛሬ ላይ እንድትደርስም የነበረውና ዛሬም ያለው አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው።

እንደ ሀገር ከመጣንበት ረጅም ዘመንና ዘመናቱ ከፈጠሯቸው የተለያዩ ትርክቶች አንጻር የራሱ ጥያቄዎች የነበሩት ፣ ለጥያቄዎቹ ምላሽ ለማግኘትም ሰላማዊ ትግሎችን በማካሄድ ፣ ለችግሮቹ መፍትሔ በማፈላለግም የሚጠቀስ ነው።

በሀገሪቱ ሕገመንግሥት የተደነገገው የሃይማኖት ነጻነት በመጠቀም፤ በግለሰብ ሆነ በማኅበረሰብ ማንነት ግንባታ ውስጥ ኃላፊነት የሚሰማው ትውልድ ለመቅረጽ ለሚደረገው ሀገራዊ ጥረት ሃይማኖቱ ፣ የሃይማኖት ተቋማቱ እና ምእመናኑ እያደረጉት ያለው ጥረት እውቅና የሚሰጠው ነው።

በተለይም በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ዘንድ ከለውጡ ቀደም ባለው ጊዜ የነበረውን ጭቆና እንደ ማኅበረሰብም ሆነ እንደ ሀገር ሲያስከፍለን የነበረውን ያልተገባ ዋጋ ለማስቀረት መንግሥት የጀመረውን የሰላም ጥረት ተቀብለው ያስመዘገቡት ስኬት የሚበረታታ ነው።

ፍቅር ፣ ሰላም እና አንድነት የየትኛውም ሃይማኖት አስተምሮ ዋንኛ ማጠንጠኛ እንደሆኑ ይታመናል። ከዚህ የተነሳም እነዚህን መንፈሳዊ እሴቶች ታሳቢ አድርገው ለሚዘረጉ እጆች አዎንታዊ ምላሽ መስጠት ለአስተምህሮው ተገዥና ብቁ ሆኖ የመገኘት አንዱ ማሳያ ነው።

ሙስሊሙ ማኅበረሰብም በተለያዩ ገፊ ምክንያቶች ገብቶበት ከነበረው መከፋፈል ወጥቶ አሁን ላይ ወደ አንድ የሚያመጣው መንገድ ላይ መቆሙም ሆነ ፤መንገዱን አማራጭ የሌለው አድርጎ መቀበሉ ለሃይማኖታዊ አስተምሮው ያለውን ተገዥነት ያመላከተ ነው።

ከሁሉም በላይ ችግሮችን /ልዩነቶችን ሃይማኖታዊ አስተምሮው በሚያዘው መንገድ በሰላማዊ መንገድ ቁጭ ብሎ በመነጋገር ለመፍታት የሄዱበት መንገድና የተገኘው አበረታች ውጤት እንደሀገር ለጀመርነው በንግግር ችግሮችን የመፍታት አዲስ ባህል ጥሩ መማሪያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

የትኛውም ችግር በየትኛውም መልኩ አቅም አግኝቶ የገዘፈ ቢመስልም፤ ከባለ ጉዳዩ /ባለቤቱ ሊበልጥ የሚችለው ፤ በሰከነ መንፈስና ፣ በተረጋጋ አእምሮ ቁጭ ብሎ ማየት የሚያስችል አቅም ሲታጣ ብቻ መሆኑን በተግባር ያሳየ ፤ ለሌሎች አሁነኛ ተመሳሳይ ችግሮች እንደ ማሳያም የሚወሰድ ነው።

መንግሥትም በሙስሊሙ ማኅበረሰባችን ዘንድ ተፈጥሮ የነበረውን አለመግባባት ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት በሰላማዊ መንገድ በራሳቸው አቅም እንዲፈቱ አስቻይ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ያደረገው ጥረት ከፍያለ ከበሬታ ሊሰጠው የሚገባ ነው። ለተገኘው ስኬትም ትልቅ አቅም ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

ሙስሊሙ ኅብረተሰብ በለውጡ የተገኘውን ችግሮች በሰላማዊ መንገድ በውይይት የመፍታት ዕድል እንዲጠቀም መድረኮችን ከማመቻቸት ጀምሮ፤ በመካከላቸው መተማመን እንዲፈጠር የተጓዘበትም ርቀት የለውጡ አንድ ትሩፋት ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው አዲስ ልምምድ ነው።

የእስልምና ጠቅላይ ምክር ቤት ሕጋዊ ሰውነት እንዲያገኝ የሚያስችል አዋጅ መጽደቁ፤ የእስልምና እምነት መርህን የተከተለ የፋይናንስ ተቋም እንዲቋቋም መደረጉ ፤ የሃይማኖቱ ተከታዮች የማምለኪያ ስፍራዎች እንዲያገኙ በመንግሥት በኩል የተደረገው ጥረት መንግሥት ለሃይማኖት ተቋማት ዕድገትና ለሰላማዊ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ያለውን ቁርጠኝነት ያመላከተ ነው።

መንግሥት በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ውስጥ የተፈጠረውን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ካደረገው ጥረት ጎን ለጎን በማኅበረሰቡ ለሚነሱ የተለያዩ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የሄደበት ርቀትና፤ ምላሾቹ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ውስጥ የፈጠሩት መነቃቃት ፤ እንደ ሀገር ለጀመርነው አዲስ ተሻጋሪ ትርክት ግብአት ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ተጨባጭ ተሞክሮ ነው።

ከዛም ባለፈ ሙስሊሙ ማኅበረሰብ ቀደም ባለው ጊዜ በሀገረ መንግሥቱ ግንባታም ሆነ ፤ ሀገረመንግሥቱን ለማጽናት ያደረጋቸውን ጥረቶች፤ በቀጣይ አጠናክሮ እንዲቀጥል ፤ድህነትን ታሪክ ለማድረግ ለጀመርነው እልህ አስጨራሽ ትግል ስኬት ተጨማሪ አቅም የሚሆን ነው!

**አዲስ ዘመን**
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

<u>የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ</u>
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

<u>ዋና አዘጋጅ</u>
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

<u>አድራሻ</u>
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

<u>የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ</u>
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

<u>የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር</u>
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

<u>የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች</u>
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

<u>የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል</u>
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

<u>የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ</u>
ስልክ - 011-1-26-43-39

<u>ማከፋፈያ</u> ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በምርት አሰባሰብ ሂደት፣ መዘናጋት እንዳይፈጠር!

<u>ፒያንኪ ዘኢትዮጵያ</u>

ግብርና የአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሕይወት መሠረት ነውና ስለግብርናው ዘርፍ ደግሞ ደጋግሞ ማውራት ተገቢም አስፈላጊም ነው:: በተለይም፣ በአብዛኞቹ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ከፍተኛው ዓመታዊ የግብርና ምርት የሚገኝበት፣ የመኸር እርሻ ምርት ስብሰባ ሥራ በሚከናወንበት በአሁኑ ወቅት ስለግብርናው መጠየቅና መከታተል እጅግ አስፈላጊ ነው:: የግብርናው ዘርፍ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ መሠረት ስለሆነ የዚህ ወሳኝ ዘርፍ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ትኩረት ይፈልጋል::

የግብርና ሚኒስቴር ይፋ ባደረገው መረጃ፣ ከ2015/16 የመኸር እርሻ 513 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይገኛል ተብሎ ይጠበቃል:: ታዲያ ይህን እቅድ ለማሳካት የምርት አሰባሰብ ሥራን በከፍተኛ ጥንቃቄና ትጋት ማከናወን ያስፈልጋል:: በምርት አሰባሰብ ወቅት የሚፈጠሩ ችግሮች ከፍተኛ የምርት ብክነት እንዲከሰት ያደርጋሉ:: የምርት ብክነት መከሰት ደግሞ በኅብረተሰቡና በሀገሪቱ ላይ ተራዛሚ ተፅዕኖዎችን የሚያስከትሉ ችግሮችን ይፈጥራል:: የምርት አሰባሰብ ሥራ ተገቢ ትኩረት ተሰጥቶት በሚገባ ካልተከናወነ፣ የምርት እጥረት እንዲፈጠርና የዋጋ ንረት እንዲከሰት ምክንያት መሆኑ አይቀርም::

ሀገሪቱ ከበቂ በላይ የምታመርታቸው ምርቶች ጭምር ዋጋቸው ሰማይ ነክቶ በተደጋጋሚ እንታዘባለን:: ለአብነት ያህል የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ከበቂ በላይ ተመርተው ከማሳ የሚያነሳቸው አጥተው ለብክነት እንደሚዳረጉ የምርቶቹ ባለቤቶች ሲናገሩ ደግመን ደጋግመን ሰምተናል:: በከተሞች ያለው የእነዚህ ምርቶች ዋጋ ግን «ጆሮ አይሰማ» የሚያሰኝ ነው::

የአትክልትና ፍራፍሬ ዋጋ ለማሳያነት ያህል ተጠቀሰ እንጂ በሌሎቹም ምርቶች ላይ ተመሳሳይ ችግር መከሰቱ አይቀርም:: የዚህ ችግር ስር ቢመዘዝ የምርት አሰባሰብ ድረስ እንደሚደርስ አያጠራጥርም:: አሁን ባለው ከፍተኛ የዋጋ ንረት ላይ ተጨማሪ የዋጋ ንረት ከተፈጠረ የኅብረተሰቡ የኑሮ ፈተና "ከድጡ ወደ ማጡ" ይሆናልና ለምርት አሰባሰብ ትኩረት በመስጠት ተጨማሪ ችግር እንዳይፈጠር መትጋት ይገባል::

የምርት ስብሰባ ሥራው ምርትን ሰብስቦ በጥንቃቄ ለፍጆታም ይሁን ለገበያ የማቅረብ ተግባርን ያካተተ እንዲሆን ጥረት ማድረግ ይገባል:: ይህን በማድረግ እያደገ ለመጣው የምግብና የገበያ ፍላጎት በጊዜ እና በጥራት ተወዳዳሪ የሆነ ምላሽ መስጠት እንዲሁም ጥራቱን የጠበቀ በቂ የሰብል ምርት ማቅረብ እና ዋና ዋና የምግብ ሰብሎች ለዘላቂ የግብርና ልማት ያላቸውን ሚና ማሳደግ ይቻላል::

የምርት ብክነትን ከሚቀንሱ ዘዴዎች መካከል አንዱ፣ ምርትን በዘመናዊ የምርት መሰብሰቢያ መሳሪያዎች መሰብሰብ ነው:: ይህ ግብርናውን በቴክኖሎጂ የማዘመን ተግባር የግብርናውን ዘርፍ በማሳደግ ሀገሪቱ የግብርና አቅሟን በመጠቀም ከድህነት እንድትላቀቅ ለማድረግ ከሚቀርቡ ምክረ ሃሳቦች መካከል አንዱ ነው::

በተለይ ትርፍ አምራች በሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚገኙ አርሶ አደሮች ዘመናዊ የማጨጃና የመውቂያ ማሽኖችን የሚያገኙባቸውን አሠራሮችን መዘርጋት እጅግ አስፈላጊ ነው:: ይህን አሰራር በመተግበር የምርት ጥራትን መጨመርና ብክነትን መቀነስ ይቻላል::

የምርት ብክነት እንዳይፈጠር ከሚደረገው ጥረት ባሻገር፣ የደረሱ ሰብሎች ወቅቱን ባልጠበቀ ዝናብ እንዳይበላሹም መትጋት ያስፈልጋል:: የብሔራዊ ሜቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩትም በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊከሰት ስለሚችል አርሶ አደሩ የደረሱ ሰብሎችን እንዲሰበስብ አሳስቧል::

አንዳንድ ክልሎችም ተማሪዎች በምርት ስብሰባ ሥራ ላይ እንዲሳተፉ የሚያስችሉ ውሳኔዎችን ተግባራዊ አድርገዋል:: እንዲህ ዓይነቶቹ ተገቢ ውሳኔዎች የመኸር እርሻ ምርት በሚሰበሰብባቸው በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ሊተገበሩ ይገባል:: ሰብሎች ከታጨዱ በኋላም በፍጥነትና በጥንቃቄ ወደ አውድማ እንዲገቡ መደረግ አለበት::

በኢትዮጵያ የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት ለማሳደግ የሚያስችሉ በርካታ ተግባራት ሲከናወኑ ቆይተዋል:: በመንግሥትና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ትብብር በተተገበሩት ተከታታይነት ያላቸው የግብርና ልማት እንቅስቃሴዎች የሀገሪቱን ምጣኔ ሀብት ያሳደጉና የሕዝቡን፣ በተለይም የአርሶ አደሩን፣ ሕይወት ያሻሻሉ ውጤቶች ተመዝግበዋል::

ከግብርና የሚገኘው ምርት በየዓመቱ ጭማሪ አሳይቷል፤ ቁጥሩ ቀላል የማይባል የህብረተሰብ ክፍልም ከድህነት መላቀቅ ችሏል:: የግብርናና ገጠር ልማትን ለማሻሻል የተወሰዱ ርምጃዎች ብዙ ባለሀብት አርሶ አደሮችን መፍጠርም ችለዋል::

ይሁን እንጂ እነዚህ ተግባራት ኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ ካላት አቅም አንፃር ሲመዘኑ ለሀገሪቱ የምግብ ዋስትና፣ የሥራ እድል ፈጠራና የምጣኔ ሀብት እድገትም ሆነ ለዘርፉ ችግሮች አስተማማኝ መፍትሔ የሰጡ አይደሉም:: አሁንም ግብርናው በዘላቂነት ከኋላቀር አስተራረስና ከዝናብ ጥገኝነት አልተላቀቀም፤ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በብዛት ከመጠቀም የራቀ ሆኖ ይታያል::

ሚሊዮኖች ከድህነት ወለል በታች እየኖሩ ነው:: በአጠቃላይ የምጣኔ ሀብት መዋቅራዊ ለውጥን እስካሁን ድረስ እውን ማድረግ አልተቻለም:: የምርት አሰባሰብን ጨምሮ በሌሎች የግብርናው ዘርፍ ስኬት ግብዓቶች ላይ የሚስተዋለው የትኩረት እጥረት እስካሁን በዘርፉ የተገኙ ውጤቶችን ወደኋላ እንዳይመልሳቸው ያሰጋል::

ወቅቱ በአብዛኞቹ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የመኸር እርሻ ምርት የሚሰበሰብበት ጊዜ በመሆኑ፣ ዋናው ሀገራዊ ትኩረት የምርት አሰባሰብ ሊሆን ይገባል:: የምርት አሰባሰቡ ዕለታዊ ክትትል ይፈልጋል፤ የጎደለውን መሙላት፤ የተበላሸውን ማስተካከል ያስፈልጋል::

ኢትዮጵያ ለብዙ ሰብሎች ተስማሚ ሥነ-ምህዳር ያላት ቢሆንም የሰብሎቹ ምርታማነት በሚፈለገው ደረጃ አለማደጉ፣ የምግብ ዋስትናን በዘላቂነት ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት ፈታኝ አድርጎታል:: ይህን ችግር ለማቃለል ከሚያስችሉ የመፍትሔ አማራጮች መካከል አንዱ ለምርት አሰባሰብ ሥራ ተገቢው ትኩረት መስጠት ነው::

የመኸር እርሻ ምርት ስብሰባ ሥራ የሚከናወንበት በዚህ ወቅት አርሶ አደሩ፣ የልማት ጣቢያ ሠራተኛው እንዲሁም አመራሩ ሁሉ ወደ ማሳ ዘልቆ ደፋ ቀና ማለት አለበት:: አርሶ አደሩ ምርቱን ይሰብስብ፤ የልማት ጣቢያ ሠራተኞች ሙያዊ/ቴክኒካዊ ድጋፍ ያድርጉ፤ አመራሩ ደግሞ ከአርሶ አደሩና ከባለሙያዎች በሚቀርቡ ጥያቄዎች መሠረት የጎደለው እንዲሟላ ትዕዛዝ ይስጥ፤ ክትትል ያድርግ!።

ከማሳ ዝግጅት ጀምሮ እስከ አጨዳና ድህረ ምርት አያያዝ ድረስ ለሰብሎች ሊደረግ ስለሚገባው ጥንቃቄ በግብርና ሚኒስቴር የብርዕና አገዳ ሰብሎች አመራረት ኤክስቴንሽን ማኑዋል ላይ በዝርዝር ተብራርቷል:: የልማት ጣቢያ ሠራተኞች ይህን የምርት አመራረት መመሪያ ከአርሶ አደሩ ልምድና ተሞክሮ ጋር በማቀናጀት እንዲተገበር በብርቱ መትጋት ይኖርባቸዋል::

የግብርናው ዘርፍ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ስለሆነ የዚህ ወሳኝ ዘርፍ እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ትኩረት ይፈልጋል:: ይህ ዘርፍ ለአፍታም ቢሆን ትኩረት ሊነፈገው አይገባም:: ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ግብርና ዘንግተው መኖር አይችሉም:: ቢያንስ፣ ለዓመታት የተመኘነው «ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ» እውን እስከሚሆን ድረስ ግብርናውን ለአፍታም ቢሆን መዘንጋት አንችልም!

# የሆቴሎች የአለባበስ ሥርዓት ረቂቅ ደንብ ይፋ ሆነ

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎች የሚደርስባቸውን አካላዊና ስነ ልቦናዊ ጫናን ያስቀራል የተባለለት ረቂቅ ደንብ ይፋ ተደረገ፡፡

አዲስ አበባ ባህል፣ ኪነጥበብና ቱሪዝም ቢሮ በሆቴልና መሰል አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ባለሙያዎች የደንብ ልብስ አለባበስ፣ የገፅታና የውበት አጠባበቅ እንዲሁም የጌጣጌጥ አጠቃቀም ሥነ-ሥርዓት ያወጣውን የደንብ ረቂቅ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አድርጓል።

በቢሮው የቱሪዝም ዘርፍ ኃላፊ አቶ ኃፍታይ ገ/እግዚአብሔር በወቅቱ እንደገለጹት፤ በባለሙያዎች የሚደርስን ጥቃት የሚያስቀር የአለባበስ ሥርዓት ረቂቅ ደንብ ውይይት ተደርጎበታል፡፡ የደንብ ረቂቁ ዓለም አቀፋዊ ተሞክሮዎችም የተካተቱበት ነው፡፡

በሂደቱም የቢሮው የቱሪዝም ባለሙያዎች፣ የኢትዮጵያ መስተንግዶ ማህበር፣ የአዲስ አበባ ሆቴሎችና ቱሪዝም ባለሙያዎች ማህበር፣ የቱሪዝም ማሰልጠኛ ተቋም እና የአዲስ አበባ ሆቴሎች ሥራ አስኪያጅ ማህበር እንደተሳተፉበት ገልጸዋል።

እንደ አቶ ሃፍታይ ገለጻ፤ ደንቡ በአዲስ አበባ ያሉ ሆቴሎችና መሰል ተቋማት ወጥ የሆነ ሥርዓት እንዲኖራቸው ከማገዙም በላይ ባህልና ወጉን ያልጠበቀ የአለባበስ ሥነ-ሥርዓትን በመቆጣጠር ኢትዮጵያዊ አለባበስና መስተንግዶ ሥርዓትን ለማስከበር ይረዳል፡፡

በዋናነትም ረቂቅ ደንቡ ባለሙያዎች የሚደርስባቸውን አካላዊና ስነ ልቦናዊ ጫናን ለማስቀረት ያለመ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የወጣው ረቂቅ በአዲስ አበባ ፍትህ ቢሮ ታይቶ በካቢኔ ከፀደቀ በኋላ ተግባራዊ የሚደረግ ይሆናል ያሉት ኃላፊው፤ በወጣው ረቂቅ መሰረት በተዋረድ ከማዕከል እስከ ክፍለ ከተማና ወረዳ ድረስ በባለሙያዎች ክትትልና ቁጥጥር መመሪያው የሚፈጸም ይሆናል ብለዋል።

የቁጥጥርና ክትትል ሥራው ባለሙያዎች የመንግሥት የሥራ ሰዓትን መሰረት በማድረግ የሚያረጋግጡ ሲሆን፤ የተለየ ጥቆማ ከደረሰ ግን ቢሮው ባልተጠበቀ ሰዓት በመፈተሸ እርምጃ መውሰድ እንደሚችል በውይይቱ ውስጥ ተጠቅሷል፡፡

በክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት መሰረት ጥሶ የተገኘ አካል በሕጉ መሰረት 50 ሺህ ብር የገንዘብ ቅጣት የሚጠብቀው መሆኑን አስገንዝበው፤ ቅጣቱን በተሰጠው ጊዜ ያልከፈለ አካልም ተቋሙን እስከማሸግ የሚደርስ እርምጃ ይሚወሰድ ይሆናል ተብሏል፡፡

ደንቡ ሆቴሎችን ጨምሮ 28 የተለያዩ ተቋማት ላይ ተግባራዊ የሚሆን ሲሆን፤ መመሪያውን ያልተገበሩ ተቋማት በሦስት ደረጃ የተከፈለ ቅጣት ይጠብቃቸዋል ሲሉ ገልጸዋል።

ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ
አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# የፀጥታ ችግር የነበረባቸው ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

የቢሮ ኃላፊው መንገሻ ፈንታው ዶ/ር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ከመታወጁ በፊት በበርካታ የክልሉ አካባቢዎች የጸጥታ ችግሮች ተከስተው የሕዝቡ እንቅስቃሴ ተገድቦ፣ የንግድና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ተዘግተው ነበር፡፡ ችግሩ ከክልሉ መንግሥት አቅም በላይ መሆኑን ገልጾ የፌዴራል መንግሥት ጣልቃ እንዲገባ በጠየቀው መሠረት ወደ ክልሉ ገብቶ የሰላም ማስከበሩን ሥራ ሲሠራ ቆይቷል፡፡

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታውጆ መከላከያ ሠራዊቱ ከክልሉ የፀጥታ ኃይል ጋር በተለያዩ አካባቢዎች የነበረውን የሰላም መደፍረስ ለማስተካከል ዋጋ ሲከፍል ነበር ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ በተሠራው ጠንካራ ሥራም በርካታ አካባቢዎች ላይ አንጻራዊ ሰላም ማስፈን ተችሏል።

ከዚህ ጎን ለጎን የክልሉን አመራር መልሶ የማደራጀት ሥራ መሠራቱን ጠቅሰው፤ በዚህም ከክልል ጀምሮ እስከ ወረዳና ቀበሌ ያለው አመራርና የፀጥታ ኃይል በአዲስ መልክ እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡ የፀጥታ ችግሮችን ከመቅረፍ ጎን ለጎንም የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለመፍታትና ልማቱን ለማስቀጠል ሕዝቡን የማወያየት ሥራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙ ጠቅሰዋል፡፡

ከቀን ወደ ቀን የክልሉ የሰላም ሁኔታ እየተሻሻለ መጥቶ በብዙ ቦታዎች ላይ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች ተገኝተዋል ያሉት ዶክተር መንገሻ፤ በተለይ ባለፉት ሳምንታት የሰላም ስጋት የነበረባቸው በምዕራብና ምስራቅ ጎጃም አካባቢዎች አንጻራዊ ሰላም ሰፍኗል፡፡ በሪፎርም የመጣው አመራርም ከስር ከስር ሕዝቡን እያወያየ ጉዳት የደረሰባቸው መሠረተ ልማቶች ተጠግነው ወደ ሥራ እንዲገቡ እያደረገ መሆኑን አብራርተዋል።

የጤና ተቋማት የመድኃኒት አቅርቦት ተደርጎላቸው አገልግሎት መሥጠት መጀመራቸውን ጠቅሰው፤ የትምህርት ተቋማትም ተከፍተው ተማሪዎች ወደ ትምህርተ ገበታቸው እንዲመለሱ እየተሠራ ነው፡፡ ሌሎች የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማትም ወደ ሥራ ገብተው ለሕዝቡ አገልግሎት እየሰጡ ነው ብለዋል።

በፀጥታ ችግሩ ምክንያት የንግድ ተቋማት በመዘጋታቸው የተለያዩ ሸቀጣ ሸቀጦችን ለማግኘትም አስቸጋሪ ሆኖ እንደነበር ያስታወሱት ዶክተር መንገሻ፤ አሁን ላይ የሸቀጦች ዋጋ እንዲረጋጋና የንግድ ተቋማት ለግብይት ክፍት እንዲሆኑ ተደርጓል ነው ያሉት፡፡

አብዛኛው የክልሉ አካባቢዎች ወደ ሰላማዊ እንቅስቃሴ እየተመለሱ መሆኑን ያስታወሱት ቢሮ ኃላፊው፤ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ግን አሁንም ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ በተለያዩ ውስን ቦታዎች ላይ ጥቃት በመሰንዘር ጉዳት የማድረስና ሕዝቡን ሰላም የመረበሽ እንቅስቃሴ ሙከራ እየተደረገ በመሆኑ ዘላቂ ሰላም የማስፈን ሥራ አጠናክሮ መሥራት የሚጠይቅ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በቀጣይም የመንግሥት መዋቅሩን የበለጠ ለማጠናከርና ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን መንግሥት በትኩረት ይሠራል ያሉት ቢሮ ኃላፊው፤ ሕዝቡም ከዚህ በፊት ሲያደርግ እንደነበረው ክልሉን ሙሉ በሙሉ ወደ ሰላማዊ እንቅስቃሴ ለመመለስ የሚደረገውን ጥረት እንዲደግፍ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# የኢፌዴሪ አየር ኃይል...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ትኩረት ሰጥቶ ሲሠራ ነበር ያሉት ሌተናል ጄነራሉ፤ በአየር ኃይሉ በተሰጣቸው ትምህርትና ሥልጠና በርካታ ዜጎች ለግዳጅ ብቁ ሆነዋል ብለዋል፡፡

በሀገሪቷ የአየር ኃይል ታሪክ ተሠርቶ በማያውቅ መልኩ፤ የአየር ኃይል አብራሪዎች እና ቴክኒሺያኖች የአመራር ብቃት ተጨምሮ ሥልጠና መሰጠታቸውን ተናግረዋል፡፡

ሠልጣኞቹ ከተሰጣቸው ትምህርት በተጨማሪ የ250 የበረራ ሰዓት ያጠናቀቁ እና የአመራርነት ትምህርት የወሰዱ ናቸው ብለዋል፤ በተጨማሪም በተቋሙ የሠለጠኑ የበረራ አስተማሪዎች በቅርቡ እንደሚመረቁ ተናግረዋል፡፡ በተጨማሪም አየር ኃይሉ በትጥቅ ረገድ በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቅሰዋል፡፡

የኢፌዴሪ አየር ኃይል ከለውጡ ማግሥት ጀምሮ የነበሩ ትጥቆችን የማሻሻል እና አዳዲስ ትጥቆችን የመታጠቅ ሥራ ሲሠራ መቆየቱን የጠቀሱት ሌተናል ጄነራል ይልማ፤ በተለይ አዳዲስ ትጥቆችን በመታጠቅ ረገድ በመንግሥት፣ በውስጥ አቅምና በተቋማት ትብብር በርካታ ሥራዎች መከናወናቸውን አብራርተዋል፡፡

በዚህም አየር ኃይሉ ኤሌክትሮኒክ “ዋር ፌሮች”፣ ሰው አልባ አውሮፕላኖች፣ ዘመናዊ ሄሊኮፕተሮች እና በርካታ ዘመኑ የደረሰባቸው ቴክኖሎጂዎች መታጠቁን አብራርተዋል፡፡ እነዚህ ትጥቆችም በመጪዎቹ ቀናት የሚመረቁ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ሀገራት ነፃነት የታገለች ሀገር እንደመሆኗ የምሥረታ በዓሉን ብቻዋን ማክበር እንደማይገባት ጠቅሰው፤ የምሥረታ በዓሉ በሀገር ውስጥ ከሚከናወኑ የፓናል ውይይቶች፣ ጉብኝቶችና የአየር ትርኢቶች እንዲሁም ሌሎች ዝግጅቶች በተጨማሪ 26 የአፍሪካ ሀገራት የአየር ኃይል አዛዦችና የአቪዬሽን ኩባንያዎች የሚሳተፉበት መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የምሥረታ በዓሉ በአየር ትርኢት ጭምር እንደሚከበር ጠቅሰው፤ በዘርፉ የላቀ ደረጃ የደረሱ የኢትዮጵያ ወዳጅ ሀገራት የሚሳተፉበት የአየር ትርኢት እንደሚካሄድ ጠቁመዋል፡፡

እንደ ዋና አዛዡ ገለፃ፤ የኢፌዴሪ አየር ኃይል በከፍተኛ ደረጃ እያደገ እና እየተለወጠ ነው፡፡ አየር ኃይሉ ወደፊትም ተመራጭ ሆኖ የሚቀጥል በመሆኑ አዲሱ ትውልድ ይህን ተገንዝቦ ተቋሙን ሊቀላቀል ይገባል፡፡

የምሥረታ በዓሉ ጥናት ላይ በመመሥረት ከኢትዮጵያ አየር ኃይል አመሠራረት ጋር በተያያዘ መልኩ እንዲከበር በተወሰነው መሰረት ዘንድሮ ከኅዳር 20 ጀምሮ የሚከበር ሲሆን፤ በቀጣይም በየዓመቱ ኅዳር 20 የኢትዮጵያ አየር ኃይል ቀን ሆኖ እንደሚከበር ሌተናል ጄነራል ይልማ መርዳሳ ገልጸዋል፡፡

# ለዓባይ ግድብ እስካሁን...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ዓመታት ያህል በቦንድ ግዥ፣ በ8100 የአጭር ጽሁፍ መልዕክትና ሌሎች የገቢ አሰባሰብ ሂደቶች የግድቡ ግንባታ ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያለምንም መቆራረጥ ለግድቡ ድጋፉን ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በዚህም ግድቡ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም 18 ቢሊዮን 613 ሚሊዮን 548 ሺህ 672 ብር ተሰብስቧል፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፤ ለግድቡ ግንባታ በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሦስት ወራት ውስጥ በ8100 አጭር የጽሁፍ መልዕክት ከ33 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር በላይ፣ ከሀገር ውስጥ ቦንድ ሽያጭና ስጦታ ከ273 ሚሊዮን 960 ሺህ ብር በላይ፣ የዲያስፖራ ቦንድ ሽያጭና ስጦታ አራት ሚሊዮን 31ሺህ 298 ብር፣ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ የስጦታ አካውንት ከ71 ሚሊዮን ብር በላይ እንዲሁም በልዩ ልዩ መልክ የተሰበሰበውን ጨምሮ በአጠቃላይ በሩብ ዓመቱ 383 ሚሊዮን 213 ሺህ 72 ብር ተሰብስቧል፡፡ በወር በአማካኝ እስከ 130 ሚሊዮን ብር ከኅብረተሰቡ እየተሰበሰበ ነው፡፡

ለግድቡ ገቢ ለማሰባሰብ እየዋለ ያለው የህዳሴ ግድብ ዋንጫ በአሁኑ ወቅት በሲዳማ ክልል እንደሚገኝና ህዳር 29 ቀን ክልሉ ዋንጫውን ለሌላ ክልል ሲያስረክብ ተጨማሪ ከፍተኛ የገንዘብ ገቢ እንደሚጠበቅ ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል።

ግድቡን የማጠናቀቅ ሥራው ሰፊ ሀብት የሚጠይቅ ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ከሕዝቡ አሁንም እስከ 20 ከመቶ ሀብት ይጠበቃል ሲሉ ገልጸዋል፡፡ የግድብ ግንባታ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት በዚህ ዓመት አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ማቀዱንም ገልጸዋል፡፡

በአፈጻጸም ረገድ ባለፉት አምስት ዓመታት ከለውጡ ወዲህ የገቢ መጠኑ እያደገ መሆን ጠቅሰው፤ በአብዛኛው በዓመት እስከ አንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር እየተሰበሰበ እንዳለ ገልጸዋል፡፡ “ወቅታዊ የሀገር ውስጥ ሁኔታን ግምት ውስጥ በማስገባት አሰባሰቡ ጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛል” ብለዋል፡፡

ከዚህ ቀደም በርካታ ቦንድ ለኅብረተሰቡ መመለስ እንደተቻለ እንዲሁም ትልልቅ ቦንድ የገዙ አካላት አድሰው እንደገና ግዢ መፈጸማቸውንም ተናግረዋል፡፡ ይህም ለገቢ አሰባሰቡ ትልቅ አስተዋጽኦ ማበርከቱን ነው የጠቀሱት፡፡ ኅብረተሰቡ 8100 የአጭር የጽሁፍ መልዕክትን ጨምሮ በተለያዩ የገቢ ማሰባሰቢያ አማራጮች የጀመረውን አስተዋጽኦ ግድቡ እስከሚጠናቀቅ ድረስ አጠናክሮ እንዲቀጥልም ዳይሬክተሩ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

እንደ አምባሳደሩ ንግግር፤ ፋብሪካው ትራክተር የሚገጣጥም ሳይሆን ትራክተሩን ለማምረት የሚያስችሉ ዕቃዎችን የሚያመርት እራሱን የቻለ ፋብሪካ ነው።

አምባሳደር ሱሌይማን ፋብሪካው የትራክተር ሞተር ጭምር የሚያመርት ስለመሆኑ ጠቅሰው፤ ባሉን ፋብሪካዎችም የመኪና የውስጥ ክፍል “ሻንሲ” የመሥራት አቅም እያዳበርን በመሆኑ፤ ሞተር ማምረት ከቻልን መኪና የማምረት አቅም ላይ እንደርሳለን ብለዋል፡፡ ከእኛ አቅም በላይ የሚሆኑትን ደግሞ ለሌሎች የሚሠሩ አካላት በመስጠት ሥራውን ለውጤት እናበቃለንም ሲሉም አክለዋል።

ተገዝተው በሚመጡ ትራክተሮች ብቻ የኢትዮጵያን ግብርና ማዘመን አይቻልም ያሉት አምባሳደር ሱሌይማን፤ ስለዚህም ኢትዮጵያ የራሷን “ብራንድ” መትከል ስለሚገባት በሚሊዮን የሚቆጠር ትራክተር የሚያመርት ፋብሪካ መገንባት አለበት ብለን ወደ ተግባር በመግባት ላይ እንገኛለን ብለዋል።

ኢትዮጵያ እያደገ የሚሄደውን የሕዝብ ቁጥር ለመመገብና ግብርናዋን ዘመናዊ ለማድረግ አርባ ሚሊዮን የሚጠጉ ትራክተሮች እንደሚያስፈልጋት የተናገሩት አምባሳደር ሱሌይማን፤ አሁን በመላ ሀገሪቱ በተጨባጭ ያሏት የትራክተሮች ቁጥር ከ100 ሺ እንደማይዘል ግምት እንዳላቸው ጠቅሰዋል፡፡

እንደ አምሳደሩ ንግግር ከሆነ፤ ኢትዮጵያ ባላት የትራክተር ቁጥር ደግሞ ምርታማ ሆና ሕዝቧን መመገብ ባለመቻሏ ከፍተኛ የምግብ እጥረት ያጋጥማታል፤ ይህ ደግሞ ለሀገሪቱ አደጋ ነው።

ቀጣይ የኢትዮ ኢንጂነሪንግ ዕቅድ ተዘርዝረው የተሰጡትን ኃላፊነቶች በአግባቡ እንዲወጣ ማድረግ ስለመሆኑ የጠቀሱት አምባሳደር ሱሌይማን፤ የሀገሪቱን የኢንዱስትሪ ዘርፍ መምራት ዋነኛው ተልዕኮው ስለሆነ እሱ ላይ ጠንክሮ ይሰራል ብለዋል።

በሀገር ውስጥ የማይመረቱና በሕዝብ ተፈላጊ የሆኑ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት ክፍተትን መሙላት አንዱ ዓላማው ስለሆነ በዚህ ዘርፍም ውጤት ለማምጣት ይጥራል ሲሉም አክለዋል።

ኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ጥናትና ምርምር በማድረግም የሀገሪቱ ኢንዱስትሪዎች ዘመናዊ አሰራርን እንዲከተሉና ተወዳዳሪ እንዲሆኑም ለማድረግ ይሰራል ያሉት አምባሳደሩ፤ በቀጣይም ለውጭ ገበያ አዳዲስ ሞዴል ያላቸውን መኪናዎች የማቅረብ ዕቅድ አለው። እነዚህን ተልዕኮዎቹን ለማሳካት ከወዲሁ የጀመራቸው ሥራዎች አሉም ብለዋል።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# ‹‹የኃይል መቆራረጥ፤ የመለዋወጫ ችግር እና ስርቆት የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ድርጅትን እየፈተኑት ነው››

-አቶ አክሊሉ ሂቢሶ

የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ተወካይ



እፀገነት አክሊሉ

የባቡር ትራንስፖርት በርካታ ሰዎችንና ዕቃዎችን ለማጓጓዝ ተመራጭ የትራንስፖርት ዘርፍ ነው:: ኢትዮጵያውያንም የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ከሆኑ ሰንበትበት ብለዋል። የባቡር ትራንስፖርት የተጀመረው እኤአ በ1820 በእንግሊዝ ሀገር መሆኑ ይነገራል። ጅማሮው በእንግሊዝ አገር ይሁን እንጂ፣ ኢትዮጵያም በበኩሏ በባቡር ትራንስፖርት ተጠቃሚነት ከመቶ ዓመት በላይ ያስቆጠረ ታሪክ እንዳላት የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያ በኢትዮ ጅቡቲ የባቡር መስመር ዝርጋታ በባቡር ትራንስፖርት በርካታ ዓመታትን ያስቆጠረች ሲሆን፤ በኋላም በ2008 ዓ.ም የቀላል ባቡር የትራንስፖርት አገልግሎት በአዲስ አበባ ከተማ መሰጠት ተጀምሯል።

የቀላል ባቡር አገልግሎት መጀመሩ የትራንስፖርቱን ችግር ከመቅረፉ ባሻገር ለኢኮኖሚ እድገትና ለማኅበራዊ ለውጥም ጉልህ ፋይዳ እንዳለው በወቅቱ ተስፋ ተጥሎ ሲገለጽ ነበር።

የከተማዋን የትራንስፖርት እጥረት ለማቃለል ተገንብቶ አገልግሎት የጀመረው የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንዚት አገልግሎት CREC (China Railway Group Limited) ከተባለ የቻይና ኩባንያ ጋር EPC/Turn-key/ የግንባታ ስምምነት ተፈራርሞ ጥር 23 ቀን 2003 ዓ.ም የግንባታ ሥራውን መጀመሩም የሚታወስ ነው::

በ475 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር የተገነባ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 85 በመቶ የቻይና የገቢ-ወጪ ባንክ (China EXIM bank) በብድር የተገኘ ሲሆን 15 በመቶ በኢትዮጵያ መንግሥት የተሸፈነ ነው:: ይህ የባቡር መስመር 34 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው በሁለት አቅጣጫዎች የሚጓዝ፤ የምሥራቅ-ምዕራብ መነሻ ከአያት አደባባይ መዳረሻው ጦር ኃይሎች ሆስፒታል ሲሆን 17 ነጥብ 4 ኪሎ ሜትር ርዝመት አለው::

የሰሜን-ደቡብ መስመር መነሻ ከዳግማዊ ምኒሊክ አደባባይ መዳረሻው ቃሊቲ ሲሆን 16 ነጥብ 59 ኪሎ ሜትር ርዝመት አለው:: ሁለቱ መስመሮች ከመስቀል አደባባይ እስከ ልደታ ቤተክርስቲያን 2 ነጥብ 7 ኪሎ ሜትር የጋራ ሀዲድ ይጠቀማሉ::

የቻይና ስታንዳርድ ጌጅ 1 ነጥብ 435 ሚሊ ሜትር ስፋት ያለው ባለ ሁለት ሀዲድ በመሬት፤ በዋሻ ውስጥ እና በድልድይ የሚጓዝ ሲሆን የእግረኛ እና የመኪና ማቋረጫዎች አሉት::

የዲዛይን ፍጥነቱ 80 ኪሎ ሜትር በሰዓት የኦፕሬሽን ፍጥነቱ ደግሞ 70 ኪሎ ሜትር ነው:: 39 የመሳፈሪያ እና መውረጃ ጣቢያዎች ያሉት ሲሆን 27 በመሬት ላይ 9 በድልድይ ላይ 2 በከፊል ድልድይ እንዲሁም አንድ በዋሻ የሚገኙ ጣቢያዎችን ይዟል::

39 የትኬት መቁረጫ ቢሮዎች፣ 18 የኃይል መቀበያ ጣቢያዎች፣ 22 ሊፍቶች እና 12 እስካሌተሮች ያሉት ሲሆን ለ18 ሰዓታት በሦስት ፈረቃ አገልግሎት ይሰጣል::

በ2008 ዓ.ም መጀመሪያ የኦኘሬሽን ሥራውን በይፋ የጀመረው የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንዚት አገልግሎት ሸን ዘን ሜትሮ ግሩፕ የተባለ የቻይና ኩባንያ ለ3 ዓመታት የማስተዳደር እና ጥገና ውል ሥራ (ኮንትራት) ሠርተዋል:: አንድ ነጠላ ባቡር በአንድ ጊዜ 317 መንገደኞች ማጓጓዝ የሚችል ሲሆን በአጠቃላይ 41 ባቡሮች አሉት ::

የአዲስ አበባ ቀላል ባቡት ትራንዚት አገልግሎት አሁናዊ ሁኔታን በተመለከተ ከተቋሙ የኦፕሬሽን ማዕከል ዳይሬክተርና የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንስፖርት ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ ተወካይ ከሆኑት አቶ አክሊሉ ሂቢሶ ጋር ቆይታን አድርገናል::

**አዲስ ዘመን ፡- የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንስፖርት አሁናዊ ሁኔታ ምን መልክ አለው?**

**አቶ አክሊሉ፡-** ሁላችንም እንደምናውቀው አዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንስፖርት ድርጅት መስከረም 2008 ዓ.ም ጀምሮ በይፋ የትራንስፖርት አገልግሎቱን ለከተማው ትራንስፖርት ተጠቃሚዎች በመስጠት ላይ ይገኛል:: ላለፉት 9 ዓመታትም የትራንስፖርት አገልግሎቱን ለብዙኃን ተጠቃሚዎቹ ምቹ ቀልጣፋና አስተማማኝ በሆነ መልኩ በመስጠት በከተማው ውስጥ ያለውን የትራንስፖርት ችግር በማቃለል ላይ የሚገኝ ነው::

ይህ የትራንስፖርት አማራጭ በከተማዋ ዋና ዋና በሆኑ ሁለት መስመሮች ማለትም ከጦር ኃይሎች አያት እንዲሁም ከቃሊቲ እስከ ጊዮርጊስ ድረስ ባሉት መስመሮቹ ከፍተኛ የተሳፋሪ ቁጥርን በማመላለስ በትራንስፖርት ዘርፉ ላይ የበኩሉን ጉልህ ሚናና ድርሻ እየተጫወተ ያለ ድርጅት ነው::

ድርጅቱ ሥራውን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ተሳፋሪዎችን እያገለገለ ሲሆን ይህንንም በአኃዝ ለመጥቀስ በቀን ከ 150 ሺ በላይ የሚሆን ሰው አሁን ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች ቁጥሩ ዝቅ ብሎ እስከ 70 ሺ ሰው አገልግሎት እንዲያገኝ እየሠራ ነው:: በነገራችን ላይ የትራንስፖርት ድርጅቱ ሥራውን በሙሉ አቅሙ መሥራት ቢችል በቀን እስከ 2 መቶ ሺ ሰው ማጓጓዝ ይችል ነበር:: ይህንን የሚደግፍ መሠረተ ልማት የሰው ኃይልና ቴክኖሎጂ ቢኖረውም በአንዳንድ ምክንያቶች ግን የአቅሙን ያህል መሥራት እንዳይችል ሆኗል::

**አዲስ ዘመን ፡- አሁን ላይ የትራንስፖርት ድርጅቱ የአቅሙን ያህል እየሠራ ሳስመሆኑ ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው?**

**አቶ አክሊሉ፡-** አሁን ላይ ድርጅቱ የሚሰጠው አገልግሎት እየቀነሰ በመምጣቱ የተሳፋሪዎቹም መጠን በዛው ልክ እየወረደ መጥቷል:: ይህም በዋናነት አገልግሎቱ ሲጀመር የተገዙ ባቡሮች ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት አገልግሎትን ቢሰጡም አስፈላጊው መለዋወጫ አልቀረበላቸውም፤ ይህ ሁኔታ ደግሞ በባቡሮቹ ላይ በጉልህ የሚታዩ የቴክኒክ ችግሮች እያመጣ ስላለ ባቡሮቹ አገልግሎት እንዳይሰጡ ተደርገዋል:: ይህ ሁኔታ ደግሞ አሁን ላይ የትራንስፖርት አገልግሎቱን በውስን ባቡሮች እንድንሰጥ አስገድዶናል::

ያለፉት ዘጠኝ ዓመታት አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩት ባቡሮች ደግሞ በጊዜ ሂደት መጠገን ስላለባቸው ይህንን ጥገና ደግሞ ለማድረግ ብዙ አሳሪ ምክንያቶች በተለይም የመለዋወጫው ጉዳይ አልባት ሊያገኝ ባለመቻሉ በውስን ባቡሮች እየሠራን ነው:: ጥቂትም ቢሆኑ አስተማማኝ ቴክኒካል ብቃት ላይ ናቸው ብለን ያመንባቸውን ብቻ በሥራ ላይ አውለን ኅብረተሰቡ አገልግሎት እንዲያገኝ እያደረገን ነው::

**ሌላው በመሠረተ ልማቶቹ ላይ እየደረሱ ያሉት የትራፊክ አደጋዎችና ስርቆቶች ናቸው:: በዚህም የኃይል ተሸካሚ ገመዶች ይሰረቃሉ፤ የመገናኛ ኬብሎችም ይወሰዳሉ የሚደርሱ የትራፊክ አደጋዎችም በባቡሩ እንዲሁም በሀዲዱ ላይ ከፍተኛ ጉዳትን ያስከትላሉ**

**አዲስ ዘመን ፡- የባቡር ትራንስፖርት ዘርፉ በብዙ መንገዶች እየተፈተነ እንዳለ ነግረውናል፤ አሁን ላይ የባቡር ትራንስፖርቱ ፈታኝ ችግር ብለው ለይተው የሚያስቀምጡት ምንድን ነው?**

**አቶ አክሊሉ፡-** ከላይ የጠቀስኳቸው ፈተናዎች በሙሉ ለድርጅቱ ከባድና የሕልውና ጥያቄ የሚያስነሱ መሆናቸው ሊሰመርበት ይገባል:: ባቡሩ ሥራውን ሲጀምር በ8 ደቂቃ ጣቢያዎች ላይ መድረስ ይችል ነበር፤ ከዛ ግን 10፣ 12፣ 15 ደቂቃዎች እየተባለ ተራዝሟል:: ዛሬ ላይ ግን በዚህ ደረጃ በጣቢያው ላይ የሚደርስ ባቡር ሊኖረን አልቻለም:: የዚህ ትልቁ ምክንያት ደግሞ የባቡሮች ቁጥር መመናመን ነው:: አሁን ላይ ከላይ እንደገለጽኩት በመለዋወጫ እጥረት የቆሙት ባቡሮች ቁጥራቸው 60 በመቶ ያህል ነው:: ይህንን ባብራራልሽ አገልግሎቱን ስንጀምር 41 ባቡሮች ነበሩን አሁን ላይ ሥራ እየሠሩ ያሉት 18 ብቻ ናቸው ሌሎቹ ቆመዋል:: በመሆኑም እንደ ድርጅት ዋና ችግር ብለን ከለየነው መካከል ይህኛው ተጠቃሽ ነው::

ሌላው በተደጋጋሚ የሚያጋጥመው የኃይል መቆራረጥ ሲሆን በዚህ ምክንያት ባቡሮች በመንገድ ላይ ይቆማሉ ፤ ተሳፋሪዎችም ይጉላላሉ:: ሌላው በመሠረተ ልማቶቹ ላይ እየደረሱ ያሉት የትራፊክ አደጋዎችና ስርቆቶች ናቸው:: በዚህም የኃይል ተሸካሚ ገመዶች ይሰረቃሉ፤ የመገናኛ ኬብሎችም ይወሰዳሉ የሚደርሱ የትራፊክ አደጋዎችም በባቡሩ እንዲሁም በሀዲዱ ላይ ከፍተኛ ጉዳትን ያስከትላሉ:: አሽከርካሪዎች አጥር ጥሰው ይገባሉ፤ መሠረተ ልማቱ ላይ ጉዳት ይደርሳል፤ አንዳንድ ማቋረጫዎች ላይ ከባቡር ጋር የመጋጨት ሁኔታዎች ይፈጠራሉ:: ይህ ሁኔታ ደግሞ በሁለት መንገድ ጉዳት ያደርሳል:: አንደኛው በንብረቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት መድረሱ ሲሆን፤ ሁለተኛ የአገልግሎት አሰጣጡ እንዲረበሽ ወይም እንዲስተጓጎል ያስገድዳል:: በዚህም ደንበኞች ከትንሽ ደቂቃ ጀምሮ እስከ ሰዓታት ድረስ ይጉላላሉ:: ተቋሙም የሚያጣው ገቢ ቀላል አይደለም::

**አዲስ ዘመን ፡- ይህ እንግዲህ ከባድና ለድርጅቱም ፈተና የሚሆን ችግር ነውና ለመፍታትስ የተደረገው ጥረት ምን ይመስላል?**

**አቶ አክሊሉ፡-** ይህንን ከባድ ችግር ለመፍታት ለበርካታ ጊዜያት ከተለያዩ አካላት ጋር ሰፊ ውይይቶችን አድርገናል ችግሮቹንም ለመቅረፍ ብዙ ጥረቶች እየተደረጉ ነው:: በመሆኑም ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የሚጠይቀው መለዋወጫ እስካልተሟላ ድረስ ግን አገልግሎቱን በሚፈለገው ልክ መስጠቱ የሚቻል አይመስለኝም:: የኃይል መቆራረጡን አልባት ለመስጠት ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ጋር እየተሠራ ያለ ሥራ አለ:: በመሠረተ ልማቱ ላይ እየደረሱ ላሉ ስርቆቶችንም ለመከላከል ከመጀመሪያ ጀምሮ የፖሊስ ጥበቃ የነበረ ቢሆንም በመካከል ተቋርጦብን ብዙ ሀብቶቻችንን አጥተናል:: ከግንቦት ወር ጀምሮ ግን ከአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ጋር በመነጋገርና በመስማማት በመሠረተ ልማቱ ላይ የ 24 ሰዓታት የፖሊስ ጥበቃ እንዲኖር ተደርጓል:: ለዚህም አዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን 1ሺ 5 መቶ የሚሆኑ የፖሊስ አባላትን ለጥበቃ በማቆሙ አሁን ላይ ስርቆቱ በጣም ቀንሷል::

**አዲስ ዘመን ፡- ከ 41 ባቡሮች መካከል አሁን**

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

## ‹‹የኃይል መቆራረጥ፤ የመለዋወጫ ችግር...

ከገጽ 7 የዞረ

**ሳይ አገልግሎት እየሰጡ ያሉት ከግማሽ በታች የሚሆኑት ናቸው ፤ እንደው ችግሩ በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ በሥራ ላይ ያሉትስ ባቡሮች ሳስመቆማቸው ዋስትና አለ?**

**አቶ አክሊሉ ፦** ትክክል ነው እነዚህ ባቡሮች ብቻቸውን ጫና እየበዛባቸው ነው፤ የመለዋወጫ እጥረቱ በዚሁ ከቀጠለ ደግሞ አንቺም እንዳልሽው ባቡሮቹ ላለመቆማቸው ዋስትና የለም:: ነገር ግን የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ድርጅት ከነሐሴ 13 ቀን 2014 ዓ.ም ጀምሮ ወደከተማ አስተዳደሩ ገብቷል:: ከዛን ጊዜም ጀምሮ ከተማ አስተዳደሩ በተለያዩ መልኮች ድጋፉን እያደረገ ሲሆን ተቋሙን ሪፎርም ለማድረግ አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ያሉ ችግሮችንም ለመፍታት በጀት ከመመደብ ጀምሮ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ላይ ነው:: በዚህም የቆሙ ባቡሮች መለዋወጫ ተገዝቶላቸው ተጠግነው ድርጅቱ በሙሉ አቅሙ አገልግሎቱን እንዲሰጥ የራሱን ጥረት እያደረገ ነው::

**አዲስ ዘመን ፦ ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት የባቡር ትራንስፖርቱ በተለያዩ ፈታኝ ችግሮች ውስጥ ቢሆንም አገልግሎቱን አላቋረጠምና እንደው በዚህ ሥራ ውስጥ ጠንካራ ጎናችን ነበር ብለው የሚያነሱት ነገር ይኖር ይሆን?**

**አቶ አክሊሉ፦** ምንም እንኳን ድርጅቱ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ እያለፈ ቢሆንም አገልግሎቱ ግን በምንም መልኩ ሳይቆራረጥ ባሉት ባቡሮች ሥራው እየተሠራ ነው:: የሚገርመው ነገር ይህ አገልግሎት እየተሰጠ ያለው ባለፉት ዘጠኝ ዓመታት አንድ መለዋወጫ እንኳን ሳይገዛ ነው:: ከዚህ አንጻር 70 ሺ ሰዎችን በ32 ከሚሎ ሜትር ላይ ማመላለስ ለእኛ የጠንካራ ጎናችን ማሳያ ነው::

በዚህ ከባድ ችግር ውስጥ ሆነን በቀን ለ70 ሺ ሰው አገልግሎት መስጠት ማለት እንደ ቀላል የሚወሰድ አይደለም:: የባቡር ትራንስፖርቱ በመለዋወጫ እጥረት ብቻ ሳይሆን እየተፈተነ ያለው በኬብል ስርቆት በመሠረተ ልማቱ ላይ እየደረሰ ባለው የትራፊክ አደጋ ነው::

ድርጅቱ ባለሙያዎችን እያበቃ በውስጥ አቅሙ የሚሰጣቸው የጥገና አገልግሎቶች በጠንካራ ጎንነት ሊነሱለት የሚገቡ ናቸው:: በዚህም እስከ አሁን ድረስ መለዋወጫዎችን በማሻሻል (ሞዲፋይ) በማድረግ እንዲሁም አንዱን በአንዱ በመተካት ባለሙያዎች እውቀታቸውን እየተጠቀሙ ጥገናዎችን እያከናወኑ ነው ድርጅቱን እዚህ ያደረሱት::

ሌላው አሁን ላይ የባቡር አገልግሎቱ በሙሉ በኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች እየተመራ መሆኑም የጥንካሬው ማሳያ አድርጎ መውሰድ ይቻላል:: የአስተዳደር (ማኔጅመንት) አካላት በሙሉ ኢትዮጵያውያን ናቸው፤ ከውጭ አገር የመጣና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለውን ቴክኖሎጂ ወደ ሀገራችን በማምጣትና በማላመድ የባቡር ስምሪቱን ጥገናውን ኦፕሬሽኑን የጥንቃቄ መርሆዎቹን በጠቅላላ አስፈላጊ የሆኑትን በሙሉ ኢትዮጵያውያኑ ባለሙያዎች እንዲተገብሯቸው በማድረግ ላይ እንገኛለን::

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያውያን ባቡር አሽከርካሪዎች እንዲሁም ስምሪት ባለሙያዎችና የጥገና ሠራተኞች እንዲሁም የአስተዳደር አካላት እየሠራን እንገኛለን:: አሁን ላይ ምንም ቻይናውያን የሉም::

**አዲስ ዘመን ፦ ችግሮቹን ለመቅረፍ ታዲያ ምን እያደረጋችሁ ነው?**

**አቶ አክሊሉ፦** የድርጅቱ ችግር ይታወቃል፤ ትኩረትም አግኝቶ በመሠራት ላይ ነው:: ከተለያዩ ተቋማት የተውጣጡ አባላት ያሉበት የቴክኒካል ኮሚቴም የችግሩን አሳሳቢነት ተገንዝቦ የመጨረሻ የውሳኔ ሃሳቡን አሳልፏል:: ቦርዱም አቅጣጫ አስቀምጧል:: በዚህም የቆሙት ባቡሮች ወደ ሥራ እንዲገቡ ይሆናል ብለን እናስባለን:: ከዛ ውጪ ደግሞ ከቻይና መንግሥት ጋር በመነጋገር 7 አዳዲስ ባቡሮችን ለማግኘት ጥረቶች እየተደረጉ ነው:: የአዲስ ባቡር ግዢንም በተመለከተ አቅጣጫ ተቀምጦ ጥናቶች አሉ:: በዚህም ድርጅቱ አቅሙን አጎልብቶና ሙሉ ኃይሉን ተጠቅሞ በትራንስፖርት ዘርፉ ላይ ያለውን ችግር ለማቃለል ይሠራል::

**አዲስ ዘመን ፦ የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ድርጅት አገልግሎቱን የማስፋት እቅድ አለው?**

> **ለባለፉት ዘጠኝ ዓመታትም የባቡር ትራንስፖርት ተሞክሮ ተብሎ የጣሊያንና የስዊዲን መንግሥት መዋቅር ሠርተው በዛም ሠራተኞች ተበረታተው እንዲሠሩ የሚያስችል ማበረታቻዎች ተደርገዋል**

**አቶ አክሊሉ፦** የአዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንስፖርት ድርጅት የመሠረተ ልማት ዝርጋታው ሁለተኛ ክፍል (ፌዝ 2 ) አለው:: ይህም ማለት እስከ 70 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን የባቡር መሠረተ ልማት ዝርጋታ ነው:: ነገር ግን ከአራት ዓመት በፊት ጥሩ ሂደት የነበረው የቻይና ኤግዚም ባንክም ብድር እያመቻቸ የነበረ ቢሆንም አሁን ላይ ሀገራችን በገባችባቸው የተለያዩ ችግሮች ምክንያት ሥራው ቆሟል::

በጠቅላላው ግን ይህ ክፍል ሁለት ግንባታ ሲከናወን አሁን በሥራ ላይ ያሉ ባቡሮችም ይሁኑ አዳዲስ የሚገዙትን እንጠቀማለን:: በነገራችን ላይ ነባሮቹ ባቡሮች የቆይታ ጊዜ አላቸው ምን ያህል ኪሎ ሜትር ድረስ ነው ማገልገል የሚችሉት የሚለውም ይታወቃል:: ያ እስኪደርስ ባሉት እንጠቀማለን ማስፋፊያው ሲጠናቀቅ ደግሞ ሌሎችንም አዳዲስ ባቡሮችን እናስማራለን::

**አዲስ ዘመን፦በቀጣይ የሚገነባው ሁለተኛና ሦስተኛ ምዕራፍ የባቡር መሠረተ ልማቶች ከዚህኛው የሚለዩበት ሁኔታ ይኖር ይሆን?**

**አቶ አክሊሉ፦** አዎ ይለያሉ ፤ለምሳሌ ሁለተኛው ምዕራፍ የሚሠራው በሜትሮ ስታይል ከመሬት በታች ሆኖ ነው :: ለምሳሌ ፒያሳ ላይ ያለው ሽሮሜዳ ድረስ ይዘልቃል፤ አያት የሚያበቃው እስከ ለገጣፎ እንዲወጣ ይሆናል፤ በተመሳሳይ ጦርኃይሎች ላይ የሚያበቃው እስከ ጀሞ እንዲሁም የቃሊቲው ቂሊንጦ ድረስ አገልግሎቱን እንዲሰጥ ተደርገው እንደሚገነቡ ነው ፕላኑ የሚያሳየው::

የባቡር ኢንዱስትሪ ለአንድ ሀገር እድገት ወሳኝ ሚና ያለው ከመሆኑ ጋር በተያያዘ እንዲሁም እድገትን ተከትለው የሚመጡ የትራንስፖርትና የመንገድ መሠረተ ልማት ፍላጎቶችን ለመመለስ የሚጠቅም ከመሆኑ አንጻር ይህ የባቡር ማስፋፊያ ፕሮጀክት ሥራው እንዲጀመር አጥብቀን እንፈልጋለን::

ብዙ ሰዎችን በአንዴ የሚያመላልስ፤ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀም፤ ነዳጅ የማይፈልግ ከመሆኑ አንጻር ዶላርን በማስቀረት የአየር ብክለትን ከመከላከል አንጻር ሚናው የጎላ በመሆኑም ባቡር መስመሩ መገንባት አለበት:: በእርግጥ ከፍ ያለ የአገር አቅምን የሚጠይቅ ቢሆንም ይገነባል የሚለው ተስፋችን ግን ሙሉ ነው::

**አዲስ ዘመን፦ አሁን ላይ የባቡር አገልግሎቱን ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያውያን እየተዳደረ ከመሆኑ አንጻር የባለሙያዎችን አቅም በማሳደግ እና ቴክኖሎጂዎችን በማላመድ በኩል የተሄደበት ርቀት ምን ያህል ነው?**

**አቶ አክሊሉ፦** የቻይናው ሼንዘን ሜትሮ ተቋም ድርጅቱን ሲያስተዳድር በነበረበት ጊዜ የኦፕሬሽንና የጥገና አገልግሎትን ነበር በኮንትራት የወሰደው:: በዚህም ለሦስት ዓመት ያህል ቆይቷል፤ እኛ ደግሞ የመጀመሪያው ዓመት ላይ አብዛኞቹን ቴክኖሎጂዎች ለመቆጣጠር ችለን ነበር:: ለምሳሌ የባቡር ስምሪቱ የጊዜ ሰሌዳ የሚባለውን 95 በመቶ በኮምፒውተር የተደገፈና ማዕከል ላይ የሚሠራ ከመሆኑ አንጻር በመጀመሪያው ዓመት ነው ልጆቻችን የተማሩት፤ በአሁኑ ወቅትም ራሳችን የምንሠራው ሥራ ሆኗል::

የባቡር ማሽከርከርን ሙያን ሙሉ ለሙሉ በመጀመሪያው ዓመት አውቀናል:: ዋናውና መሠረታዊውን ጥገናም ቢሆን በራሳችን ልጆች ሙሉ በሙሉ እያሠራን ከመሆኑም በላይ አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎችንም እንዲሠሩ እየተበረታቱና እየሠሩም ነው:: በዚህም ሽግግሩ ትልቅ አቅም የፈጠረልን ነው ማለት ይቻላል::

**አዲስ ዘመን፦ እንደ ድርጅት ከገቢ አንጻር የታስመለትን ግብ እየመታ ነው ማለት ይቻላል ?**

**አቶ አክሊሉ፦** ባደጉትም ሆነ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ሲሰጡ ዋና ዓላማቸው የዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ያላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎችን ኢኮኖሚ ወይም እንቅስቃሴ ማሳለጥ ነው:: በተለይም በታዳጊ አገሮች ላይ የብዙኃን ትራንስፖርት ኢኮኖሚውን ለማሳለጥ የሚሠራ እንጂ ትርፍ ይገኝበታል ተብሎ አገልግሎት ላይ የሚውል አለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል:: በመሆኑም አብዛኞቹ በመንግሥት ድጎማ የሚኖሩ ናቸው:: መንግሥት ደግሞ እነዚህን ድርጅቶች የሚደጉምበት ዋና ዓላማው ዜጎች ምቹ በሆነ ትራንስፖርት አማራጭ ተጠቅመው በሥራ ገበታቸው ላይ በሰዓቱ መገኘታቸው ለእሱ ትልቅ ትርፍ በመሆኑ ነው::

ከዚህ አንጻር እንደ ከተማ ከየትኛውም የትራንስፖርት አማራጭ የቀነሰ ክፍያን የሚያስከፍለው ባቡር ብቻ ነው:: ላለፉት ዘጠኝ ዓመታት የተለያዩ የታሪፍ ማሻሻያዎችን አድርገናል ይህም ቢሆን ግን በክፍያ ረገድ ከሁሉም ትንሹ ባቡር ነው::

**አዲስ ዘመን፦ በሠራተኞች አያያዝ ላይ የሚነሱ አንዳንድ ቅሬታዎች እንደነበሩ እናውቃለንና እነዚህን ከማረም አኳያ እንደ ማኔጅመንት ምን ተሠራ?**

**አቶ አክሊሉ፦**ኢንዱስትሪው አዲስ ከመሆኑ አንጻር አዲስ ባለሙያዎችና እውቀት ያለበት ተቋም ነው:: አብዛኛው ሰው ወጣት በመሆኑም የተሻለ እውቀትም ያላቸው ናቸው:: እንደ ተቋም ደግሞ ለእነዚህ ባለሙያዎች የተሻለ ነው የሚለውን ሁሉ ይሰጣል:: ለባለፉት ዘጠኝ ዓመታትም የባቡር ትራንስፖርት ተሞክሮ ተብሎ የጣሊያንና የስዊዲን መንግሥት መዋቅር ሠርተው በዛም ሠራተኞች ተበረታተው እንዲሠሩ የሚያስችል ማበረታቻዎች ተደርገዋል:: አሁንም ትራንስፖርት ቢሮ በበላይነት እየመራው በመሆኑ በሚሠራው ሪፎርም ውስጥ አስገብቶታል:: በዚህም የሠራተኞች ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም እየተሻሻለ ይሄዳል ተብሎም ይጠበቃል:: በመሆኑም ኢንዱስትሪውን የሚመጥን ለሠራተኛውም ምቹ የሆነ የአገራችንን ነባራዊ ሁኔታም የጠበቀ ሥራን ለመሥራት እየጣርን ነው::

**አዲስ ዘመን፦ድርጅቱ ካለው ሰፊ ጠቀሜታ አንጻር በእቅዱ መሠረት አገልግሎቱን ያዳርስ ዘንድ ከማን ምን ይጠበቃል ይላሉ?**

**አቶ አክሊሉ፦** አዲስ አበባ ቀላል ባቡር ትራንስፖርት ድርጅት በጣም ጠቃሚ ፕሮጀክት ነው:: አንድ ሀገርም ከባቡር ትራንስፖርት ውጪ መኖር እንደማይችል ማሰብ አለብን:: በምሥራቅ አፍሪካም የእኛ ቀላል ባቡር የመጀመሪያው ነበር:: የከተማዋን እንቅስቃሴ በማሳለጥ ኢኮኖሚውን በማመጣጠን በኩልም የሚኖረው ሚና በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም:: ስማርት ሲቲ የሚለውንም ከማምጣት አንጻር ሚናው የጎላ ነው::

ነገር ግን ይህንን ያህል ጥቅም ያለው ተቋም ሥራው በታሰበው ልክ እየሄደ ካለመሆኑም በላይ የአቅሙን ያህል አገልግሎት እንዳይሰጥም እየሆነ ነው:: የዚህ ድርጅት ችግር እስከ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ድረስ የሚታወቅ ነው፤ በመሆኑም ከመለዋወጫዎቹ በተጨማሪም ይገባሉ የተባሉት 7 ባቡሮች በቶሎ ወደሀገር ቢገቡ አገልግሎቱን በማሳለጥ በከተማዋ የሚስተዋለውን የትራንስፖርት ችግር እንፈታበታለን፤ ሕዝባችንንም የማገልገል አቅማችንን ያሳድግልናል::

በጠቅላላው ቻይናን ጨምሮ የአደጉ አገራት በሙሉ የእድገታቸው መሠረት ባቡር ነው:: ትልልቅ የመንግሥት ባለሥልጣናት ባቡር ነው የትራንስፖርት መጓጓዣቸው:: በመሆኑም የእኛንም አገር ባቡር ትራንስፖርት እዛ ላይ ማድረስ ያስፈልጋል:: ከመሠረተ ልማቱ ጀምሮ ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ ግን ደግሞ ችግሮቹ የሚታወቁ በመሆናቸው ዛሬ ተነስተን መሠረተ ልማት ወደማፍረስ አንሄድም፤ ግን ችግሮቹን ፈተን የተሻለ ተቋም ለማድረግ ሁሉም የመንግሥት አካላት በጋራ መሥራት ይኖርባቸዋል::

**አዲስ ዘመን ፦ ቀረ የሚሉት መልዕክት ካለ?**

**አቶ አክሊሉ፦** በሌሎች አገሮች የባቡር ትራንስፖርት ባለባቸው አካባቢዎች ላይ ሰውም ሆነ ተሽከርካሪ ወደመሠረተ ልማቱ እንዲገባ በምንም መንገድ አይፈቀድም:: አጥሩ ውስጥ አይጸዳዱም፤ አይነግዱም፤ ተሽከርካሪም አይገባም:: ለዚህ ደግሞ ዋነኛው አደጋው ከባድ በመሆኑና መሠረተ ልማቱም እንክብካቤ የሚፈልግ ስለሆነ ነው:: ወደእኛ ሀገር ስንመጣ ደግሞ የዚህ ተቃራኒ ነው የሚስተዋለው:: ሰዎች የባቡሩን ጡሩንባ እየሰሙ እንኳን ዳር ይዘው ለማሳለፍ አይፈልጉም፤ አሽከርካሪዎችም ለመተባበር ፍቃደኛ አይሆኑም፤ ንግዶች ይነገዳሉ፤ በመሆኑም መሠረተ ልማቱ የሁላችንም መሆኑን በመገንዘብ ከእኩይ ድርጊቶቻችን ብንታቀብ ጥሩ ነው ::

**አዲስ ዘመን፦ስነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ::**

**አቶ አክሊሉ፦**-እኔም አመሰግናለሁ

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ዘርፈ ብዙ ትኩረትና መፍትሄ የሚፈልጉት የአምራች ዘርፉ ተግዳሮቶች

**አንተነህ ቸሬ**

የኢትዮጵያ የማምረቻ ዘርፍ በርካታ ችግሮች እንዲቃለሉና የመዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግር እቅዱ እንዲሳካ ዘርፈ ብዙ ጥረቶች እየተደረጉ ይገኛሉ። እነዚህ ጥረቶች ሀገሪቱ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ካላት እምቅ አቅምና ከዘርፉ ችግሮች ስፋት አንፃር ሲመዘኑ በቂ ባይሆኑም አበረታች ውጤቶችን አስገኝተዋል።

በ2016 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሩብ ዓመትም፣ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ በዕቅድ በተያዙ ዋና ዋና ግቦች አበረታች ውጤት መመዝገባቸው ተጠቁሟል። ለኢንዱስትሪ የሚሆኑ ግብዓቶችን በማቅረብ፣ ገቢ ምርቶችን በመተካት፣ ምርቶችን ለውጭ ገበያ በማቅረብና አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በመሳብ የተሻለ አፈፃፀም ተመዝግቧል። ከአምራች ኢንዱስትሪው 38 ነጥብ ሰባት ሺህ ቶን ምርት ለውጭ ገበያ በማቅረብ ከ72 ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢም ተገኝቷል።

የኢንቨስትመንት ፈቃድ የወሰዱና ሥራ የጀመሩ አዳዲስ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሃብቶች እና የገበያ ትስስር የተፈጠረላቸው ኢንዱስትሪዎች ቁጥር ጨምሯል። የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ተኪ ምርት መጠን ለማሳደግ በተደረገው ድጋፍና ክትትል 366 ሚሊዮን ዶላር በማዳን የእቅዱን 82 በመቶ ማሳካት ተችሏል።

በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚ አቶ ጥላሁን ዓባይ እንደሚገልፁት፣ በሩብ ዓመቱ በከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች 16ሺ400 የሥራ እድሎች የተፈጠሩ ሲሆን፣ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ደግሞ ለ33ሺ 328 ዜጎች የሥራ እድል ፈጥረዋል። 527 አዳዲስ ኢንዱስትሪዎች (475 አነስተኛና 52 መካከለኛ) ተቋቁመዋል፤ ይህም ባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከነበረው አፈፃፀም (419) ጋር ሲነፃፀር የ26 በመቶ እድገት አሳይቷል።

ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የፋይናንስ አቅርቦትን ለማሻሻል የተከናወኑ ሥራዎችን በተመለከተ፤ ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ለሥራ ማስኬጃና ለሊዝ ፋይናንስ አንድ ቢሊዮን 175 ሚሊዮን ብር ለማቅረብ ታቅዶ፣ ከአንድ ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር በላይ ማቅረብ ተችሏል። ለከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ደግሞ 12 ቢሊዮን ብር ብድር ለማቅረብ ታቅዶ፣ ከ10 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር በላይ ቀርቧል።

በውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ረገድ ደግሞ፣ ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች የግብዓት ማሟያ 25 ሚሊዮን ዶላር እንዲሁም ለከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ደግሞ 161 ሚሊዮን ዶላር እንዲቀርብ ተደርጓል። በሩብ ዓመቱ በአምራች ዘርፉ ወደ ውጭ ከተላከው ምርት የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች ድርሻ 7364 ነጥብ ስምንት ቶን (19 በመቶ) ሲሆን፣ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ድርሻቸው ደግሞ 10 ነጥብ አንድ ሚሊዮን ዶላር (14 በመቶ) ነው። የፀጥታ አካላት ዩኒፎርምን በሀገር ውስጥ ማምረት በመቻሉ በተኪ ምርት ረገድ የነበረው የጨርቃ ጨርቅ ዘርፍ አፈፃፀም አበረታችና ከታቀደው በላይ ሆኖ ተመዝግቧል።

በሩብ ዓመቱ የተከናወነው ሌላው ተግባር ለአምራች ኢንዱስትሪዎች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት ነው። በዚህ ዘርፍ የተመዘገበው አፈፃፀም ባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ከተከናወነው ጋር ሲነፃፀር ቅናሽ አሳይቷል። በሩብ ዓመቱ ለ421 አነስተኛና መካከለኛ አምራቾች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተሰጥቷል፤ ባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ግን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ያገኙ አምራቾች አንድ ሺ 278 ነበሩ።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል፣ የአምራች ዘርፉ በብዙ ችግሮች ውስጥ እንደሚገኝ ጠቁመው፣ በሩብ ዓመቱ አበረታች ውጤቶች መመዝገባቸውን ይገልፃሉ። እሳቸው እንደሚሉት፣ እያሽቆለቆለ የነበረው የማምረት አቅም አጠቃቀም ተሻሽሏል። የማምረት አቅም በአማካይ 55 ነጥብ ስምንት በመቶ ደርሷል። የኃይል አቅርቦት ጥሩ መሻሻል አሳይቷል። ባለድርሻ አካላት ለዘርፉ ያላቸው ግንዛቤ እያደገ ነው። አዳዲስ ባለሀብቶችን በመሳብ ረገድ የተከናወነው ተግባር እንዲሁም አምራቾች በችግሮች ውስጥ ሆነውም ሥራቸውን ለማስፋፋት ያላቸው ተነሳሽነት የሚያበረታታ ነው።

> **የግብዓት አቅርቦትንና የሕግ ማዕቀፍ ዝግጅትን አቀናጅቶ ማንቀሳቀስ የሚችል የማስፈፀም አቅም ካልተፈጠረ የሚዘጋጁ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተጨባጭ ለውጦችን ሊያመጡ አይችሉም**

እስካሁን ድረስ ሀገሪቱ ከምትሰጠው አጠቃላይ ብድር ውስጥ ለአምራች ዘርፉ ሲሰጥ የቆየው 12 በመቶ እንደነበር ያስታወሱት ሚኒስትሩ፣ በ2015 በጀት ዓመት 60 ቢሊዮን ብር ብድር ለአምራች ዘርፉ መሰጠቱን አስታውቀዋል። የብድር መጠኑ ወደ 24 በመቶ ከፍ እንዲል መወሰኑን ይገልፃሉ።

የሀገር ውስጥ ምርቶች በመንግሥት ግዥ ቅድሚያ እንዲሰጣቸው አቅጣጫ ስለመቀመጡ የሚናገሩት አቶ መላኩ፣ ለተኪ ምርት ልማት ትልቅ ትኩረት እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ። «120 ሚሊዮን ሕዝብ ያለው ሀገር እንዴት ራሱ አምርቶ እንደሚጠቀም ማሰብ አለበት። አሁን ባለው ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ገንዘብም ተይዞ ሸቀጥ የማይገኝበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው። ስለሆነም ገቢ ምርትን የሚተካ፣ ከዚያም አልፎ ኤክስፖርት ሊያደርግ የሚችል ስትራቴጂ ሊኖረን ይገባል» ሲሉ አስገንዝበዋል።

ለዚህ ችግር ድርሻ ካላቸው ምክንያቶች አንዱ የአቅም ውስንነት መሆኑን አቶ መላኩ ይጠቅሳሉ። «ግብዓት ቀርቦ፣ መሠረተ ልማት ተሟልቶ፣ የፖሊሲ ማሻሻያ ተደርጎ፣ ሌሎች ሥራዎችም ተሰርተውም በመንግሥት ተቋማትም ሆነ በግሉ ዘርፍ የአቅም ውስንነት ችግሮች ይስተዋላሉ። የግብዓት አቅርቦትንና የሕግ ማዕቀፍ ዝግጅትን አቀናጅቶ ማንቀሳቀስ የሚችል የማስፈፀም አቅም ካልተፈጠረ የሚዘጋጁ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተጨባጭ ለውጦችን ሊያመጡ አይችሉም። ስለሆነም አቅምን መፈተሽና ስትራቴጂካዊ ማስተካከያዎችን ማድረግ ያስፈልጋል» ይላሉ።

ተገቢው ትስስር ባለመፈጠሩ ምክንያት አቅርቦቱ ኖሮም ጭምር የሚፈጠር የግብዓት እጥረት እና የምርት ጥራት ችግሮች እንዳሉ የሚጠቆሙት አቶ መላኩ፣ በዘርፉ አመራሮች ላይ የሚታዩ የግንዛቤና ተዛማጅ ክፍተቶችን በማስተካከል ዘርፉን ማሻገር እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ።

ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ አበረታች ውጤቶች ቢመዘገቡም ኢንዱስትሪዎች በቂ ድጋፎችን እያገኙ አይደለም። በቀላሉ መፈታት የሚችሉ ችግሮች ሁሉ ሳይፈቱ ይቆያሉ። በታችኞቹ የአስተዳደር እርከኖች መፈታት የሚችሉ ግን ያልተፈቱ ብዙ ናቸው። ድጋፍ ቢደረግ ኖሮ ይቃለሉ የነበሩ ችግሮች አልተፈቱም። ድጋፎች መሬት መንካት አለባቸው። የእያንዳንዱን ኢንዱስትሪ ችግር የለየ ምልከታና ድጋፍ ያስፈልጋል። «የዘርፉ ችግሮች እንዲፈቱ ከተፈለገ፣ በግልጽ መነጋገር ያስፈልጋል። የተገኙ ትንንሽ ውጤቶችን በማጉላት ብቻ የሚገኝ ጥቅም አይኖርም» በማለት የዘርፉን ችግሮች ለማቃለል በእውቀት የታገዘ ቅንጅታዊ አሰራር እንደሚያስፈልግ ያስገነዝባሉ።

በሩብ ዓመቱ ከተከናወኑ ተግባራት መካከል የአምራች ዘርፉን ውጤታማነት የሚያሳድጉ ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች ዝግጅት ይጠቀሳል። ከእነዚህ ስትራቴጂዎች መካከል በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሰው የአምራች ዘርፍ የአቅም ልማት ስትራቴጂ ነው። የግብዓት (ጥሬ ዕቃ)፣ የሰው ኃይል፣ የቦታ፣ የኃይል፣ የፋይናንስና የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ችግሮችን በአስተማማኝነት ለመፍታት የአምራች ዘርፉን አቅም የሚያሳድግ የአቅም ልማት ስትራቴጂ ማዘጋጀትና መተግበር አንዱ ወሳኝ የመፍትሔ ርምጃ ተደርጎ ስለተለየ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከባለድርሻና አጋር አካላት ጋር በመተባበር የዘርፉን ችግሮች በመለየት ወደ መፍትሔው የሚያደርሱ አሰራሮችን የሚመራ የአምራች ዘርፍ የአቅም ልማት ስትራቴጂ አዘጋጅቷል።

ስትራቴጂው የግሉ ዘርፍ በአምራች ኢንዱስትሪው እድገት ዋና ባለድርሻ እንዲሆን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተፅዕኖ ያላቸው አካላት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ፣ መንግሥት ለባለሃብቶች በቂ ድጋፍና ክትትል እንዲያደርግ፣ ለባለሀብቱ የተፈቀዱ ማበረታቻዎች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንዲደረጉ እንዲሁም አምራች ኢንዱስትሪው በግል ባለሃብቶች ተመራጭ ዘርፍ እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር እንዲያግዝ ታስቦ የተዘጋጀ የአሰራር መመሪያ ነው።

የሚኒስቴሩ የስትራቴጂክ ጉዳዮች ሥራ አስፈጻሚው አቶ ጥላሁን እንደሚገልፁት፣ የአምራች ኢንዱስትሪ አቅም ግንባታ ስትራቴጂ ማዘጋጀት ያስፈለገው በመንግሥትና በግል ተቋማት ያለው ተቋማዊ አቅም (የሰው ሀብት፣ አደረጃጀት፣ የአሰራር ሥርዓት፣ መሠረተ ልማት) በርካታ ክፍተቶች ያሉበት በመሆኑ ነው። ስትራቴጂው የአምራች ኢንዱስትሪ ባለድርሻ አካላት የዘርፉን ችግር በሚገባ ተረድተው የተሟላና ውጤታማ የሆነ ድጋፍ እንዲሰጡ እንዲሁም ዘርፉ ያለበትን አጠቃላይ ደረጃ ለመገምገም ያስችላል ተብሎ ይጠበቃል።

ከዚህ በተጨማሪም ስትራቴጂው ትልቅ አቅም ያላቸውን አምራቾችን ለመሳብ፣ ከሌሎች ሀገራት ጋር ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት፣ የዘርፉ ተቋማዊ አቅም ሙሉ ቁመና እንዲኖረው እንዲሁም ለውጦችን ቀጣይና ዘላቂ ለማድረግ እና በዘርፉ ያለውን የእውቀት፣ የአመለካከትና የክህሎት ክፍተት ለመሙላት ያግዛል። በአጠቃላይ ስትራቴጂው የግሉ ዘርፍ በአምራች ኢንዱስትሪው የምጣኔ ሀብት ድርሻ ውስጥ ትልቁን ሚና እንዲወጣ የሚያስችል መደላድል ለመፍጠር እገዛ እንደሚያደርግና በ10 ዓመቱ የልማት እቅድ በማምረቻው ዘርፍ የተቀመጠውን መዋቅራዊ ሽግግርን የማሳካት እቅድን እውን ለማድረግ ትልቅ ሚና እንደሚኖረው አቶ ጥላሁን ያስረዳሉ።

አቶ መላኩ ስትራቴጂዎቹን በተመለከተ ሲናገሩ «ስትራቴጂዎቹና መመሪያዎቹ የአሰራር ማነቆዎችን ለመፍታት የተዘጋጁ የፖሊሲ ማስፈፀሚያ ማዕቀፎች ናቸው። እያንዳንዱ ዘርፍ ምን ዓይነት መመሪያ እንደሚያስፈልገው የመለየት ሥራዎች ተሰርተዋል። እነዚህ ስትራቴጂዎች ‹አሁን ያሉትን ችግሮች በጥናት ላይ ተመስርተን ካልፈታን፣ ዘርፉ ሙሉ በሙሉ መውደቁ አይቀርም› በሚል መነሻ የተዘጋጁ ናቸው። ስትራቴጂዎቹን የመጠቀም/ያለመጠቀም ጉዳይ የአምራች ዘርፉን አፈፃፀም የማሻሻል/ያለማሻሻል ጉዳይ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል። ስትራቴጂዎች ወደ መፍትሔ የሚወስዱ መንገዶች በመሆናቸው መፍትሔው ላይ ለመድረስ ስትራቴጂዎችን በሙሉ አቅም መተግበር ያስፈልጋል። ችግሮችን ለመፍታት የችግሩን መነሻና መድረሻ መረዳት ያስፈልጋል። መፍትሔ የሚገኘው በስትራቴጂዎች ትግበራ ነው። ፍላጎትን በመግለፅ ብቻ የሚፈታ ችግር የለም፤ ኢንዱስትሪ እውቀት ይፈልጋል። ስትራቴጂዎችን ማዘጋጀት ብቻ ግብ አይደለም። የስትራቴጂው ዝግጅት ብዙ ገንዘብና የሰው ኃይል ተመድቦ የተከናወነ በመሆኑ ሰበብና ምክንያት መፍጠር ሳያስፈልግ ለትግበራው ቁርጠኛ ሆኖ መሥራት ያስፈልጋል» ይላሉ።

መንግሥት የኢንዱስትሪው ዘርፍ ችግሮችን ለማቃለል እየተገበራቸው ከሚገኙ የመፍትሔ ርምጃዎች መካከል እየተተገበረ ያለው የ«ኢትዮጵያ ታምርት» ሀገራዊ ንቅናቄ ተጠቃሽ ነው። የንቅናቄው ዋና ዋና ዓላማዎች የአምራች ኢንዱስትሪውን ችግሮች በጋራ በመፍታት ለዘርፉ ዘላቂ ልማትና ተወዳዳሪነት ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ዘርፉ ለኢኮኖሚያዊ መዋቅራዊ ሽግግር የበኩሉን አስተዋጽኦ እንዲወጣ ማስቻል እንዲሁም በዘርፉ ያለውን የሥራ ባህል ማሻሻልና የኢንዱስትሪ ምርቶችን ጥራትና ተወዳዳሪነት በማሳደግ ገቢ ምርቶችን የመተካት ሽፋንን ማሳደግ ናቸው።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሐሰን መሐመድ በ«ኢትዮጵያ ታምርት» ንቅናቄ የኢንቨስትመንት ፍሰቱ በመጨመር እና የተዘጉ ኢንዱስትሪዎች ሥራ እንዲጀምሩ በማድረግ ከ18 ሺህ 800 በላይ የሥራ ዕድል መፍጠር እንዲሁም 370 አምራች ኢንዱስትሪዎችን ወደ ሥራ መመለስ እንደተቻለ ይገልፃሉ። በንቅናቄው ሥራ ያቆሙ ኢንዱስትሪዎችን ወደ ሥራ ከመመለስ ባሻገር የኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም ከነበረበት 48 በመቶ ወደ 58 በመቶ ማደጉንም ይናገራሉ።

የማስፈፀም አቅምን መገንባት፣ የማምረት አቅም አጠቃቀምን ማሳደግ፣ የግብዓት አቅርቦት ችግሮችን መለየት፣ «ኢትዮጵያ ታምርት» ንቅናቄን አጠናክሮ ማስቀጠል፣ ቀሪ የስትራቴጂ ዝግጅት ሥራዎችን ማጠናቀቅ፣ ለኢንዱስትሪ የሰው ኃይል አቅርቦት ክትትል ማድረግ፣ ክልሎችንና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን መደገፍ፣ ኤክስፖርትን ማሳደግ እና የተቀናጁ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ውጤታማ ማድረግ የዘርፉ ቀጣይ ዋና ዋና ትኩረት አቅጣጫዎች መሆናቸውን ሚኒስትሩ አቶ መላኩ ገልጸዋል።

# ጎሜ

# ለኢትዮጵያ የሚበጃት መከባበር ነው

**ምሕረት ሞገስ**

እነዘውዴ መታፈሪያ እንደልማዳቸው የመንግሥትን ጥፋት እያነሱ ከመውቀስ ወጣ ብለዋል። የዛሬ የመወያያ ርዕሳቸው የኖረ የመከባበር እሴት እንዳይጠፋ መጠንቀቅ እና ከበፊቱ በተሻለ መልኩ ማዳበር የሚል ነው። ቀድሞም ቢሆን ለሀገር ስኬት ማኅበረሰብ ላይ መሥራት አለበት፤ በማኅበረሰብ አስተሳሰብ ላይ ዕድገት ካልመጣ ለውጥ ማስመዝገብ አይቻልም የሚለውን የገብረየስ ገብረማሪያምን ሃሳብ የሚደግፍ ነበር። ተሰማ መንግሥቴም በማኅበረሰብ ላይ በመሥራት ያለፈውን የመተሳሰብ እና የመተጋገዝ መንፈስ በማጠናከር ሁሉንም በሚያስማማ እና በሚያከባብር መልኩ ወደ አንድ መንፈስ መሳብ ተገቢ ነው የሚለውን አስተያየት በፅኑ ይደግፋል።

ገብረየስ ‹‹እኔ ቀድሞም ቢሆን ኢትዮጵያን አላሳድግ ያሏት በየጊዜው ከተፈራረቁት መንግሥታት ባልተናነሰ መልኩ ማኅበረሰቡ ነው የሚል እምነት አለኝ።›› ብሎ ሲናገር፤ ዘውዴ በበኩሉ ‹‹በእርግጥም የየዘመኑ መንግሥታት የቻሉትን ሲሞክሩ ነበር። ዋናው ችግር ግን ማኅበረሰቡ እግር ጎታች የሚሆንበት አጋጣሚ በጣም ብዙ በመሆኑ ሀገራችን ተቀብራለች የሚለው ጉዳይ እኔንም ያስማማኛል። ነገር ግን ማኅበረሰብ ላይ ለሚታዩ ዘመን አመጣሽ ችግሮች በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ ዘላቂ ችግር ሊያስከትሉ የሚችሉ አዝማሚያዎችን በጊዜ መቆጣጠር የመንግሥት ኃላፊነት ነው። በዚህ በኩል በተለይ የመከባበር እሴት እንዲያድግ በማመቻቸት በኩል በየጊዜው የተሠሩ ሥራዎች ቢኖሩም ክፍተት ነበረባቸው። ይህን ተከትሎ አሁን አንዱ ሌላውን አክብሮ የሚራመድበት ሁኔታ ተመናምኗል›› ሲል በእርሱ በኩል ያለውን እምነት ገለፀ።

ዘወትር ሁለቱንም የሚቃወመው ዘውዴ ዛሬ ከሁለቱም ሃሳብ ጋር በሚያስማማ መልኩ ሃሳቡን ቀጠለ፤ ‹‹በእርግጥም በተለይ አሁን አሁን ሠለጠንን በማለት ሽማግሌን እና የሃይማኖት አባትን ለመስማት እና ለማክበር ፈቃደኛ ያለመሆን ዝንባሌ እየተስተዋለ ነው። ይህ ማኅበረሰቡ መልካም እሴቱን በገዛ እጁ ገዝግዞ እየጣለ መሆኑን ያረጋግጣል። ጎንበስ ብሎ ሰላምታ እና ክብር የሚሰጣቸው የሃይማኖት አባቶች እና የሀገር ሽማግሌዎች በአንዳንድ አውቀናል ባይ የዕውቀት ድሃዎች በድፍረት ሲንቋሸሹ እና ሲሰደቡ ማየት እውነትም ማኅበረሰቡ ወዴት እያመራ ነው የሚል ጥያቄን ያስነሳል።›› ሲል በዘመኑ መከባበር መቅረቱን ለማስረዳት ሞከረ።

ገብረየስ ከዘውዴ ቀጠል አድርጎ ‹‹ማኅበረሰቡ ራሱ የማን ውጤት እንደሆነ ልንዘነጋ አይገባም። የግለሰብ ስብስብ ማኅበረሰብን ይፈጥራል። ግለሰብ የተለያየ እሴትን የሚሸረሽር ሃሳብ ሲሰጥ፤ ከማኅበረሰብ የተነጠለ ለማስመሰል ቢሞክርም ያነሳው ሃሳብ ገዢ አግኝቶ ወደ ማኅበረሰቡ ሊዘልቅ ይችላል። ስለዚህ ግለሰብ ተነጥሎ መታየት አይችልም። መንግሥት የማኅበረሰብ ውጤት ነው። ማኅበረሰብ ደግሞ የግለሰቦች ስብስብ ነው። እዚህ ጋር መረዳት ያለብን ችግሩን ወዲህ እና ወዲያ እያልን ከምንጎትተው ማንኛውንም ግለሰብ ማክበር እና መከባበር ከራሱ የሚጀምር መሆኑን ቢያምን ጥሩ ነው ›› ሲል ሀሳቡን አጠናከረ።

ገብረየስ ደግሞ፤ ‹‹አንዱ ሌላውን ታናሽ ታላቁን እያከበረ፤ ታላቅ ታናሹን እየመከረ ሁሉም በመተሳሰብ ሕይወቱን ማሻሻል ሲኖርበት፤ ምክር አልሰማ አስተያየት አልቀበል ሲል አንዱ ሌላውን እየጠለፈ ሲገድል እና ሲገዳደል ሀገር ከማደግ ይልቅ እንደካሮት ቁልቁል ትቀበራለች። ጭራሽ የበላይ የታላቅንም ሆነ የበታች የታናሽን ምክር ከመስማት ይልቅ ሙገሳ እና መሞካሸትን ብቻ መፈለግ፤ የሚገስፅ እየሠራህ ያለው ትክክል አይደለም አስተካክል የሚል ሽማግሌ ሲገኝ ከማክበር እና የተሰጠውን አስተያየት ተቀብሎ ከማስተካከል ይልቅ ለማንቋሸሽ መሞከር ፍፁም ተገቢነት የጎደለው ነው።›› ሲል እርሱም የሚያምንበትን ተናገረ።

> **ከሽማግሌዎች እና ከሃይማኖት አባቶች በዕውቀት የዳበረ ሒስ መቀበል ይገባል። ይህ ከመንግሥትም ሆነ ከየትኛውም ዜጋ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በሽማግሌዎች በኩልም ያፈነገጠን ማረቅ፤ የሚታዩ እንቅስቃሴዎች በስሜታዊነት በደም ፍላት ሳይሆን በማስተዋል በብልሃት እንዲካሔዱ መስመር ለማበጀት መሥራት አለባቸው**

ተሰማ እፊቱ የተቀመጠውን ቢራ እየተጎነጨ፤ ‹‹በፊትም ቢሆን የነበረው ችግር ራስን እንደጀግና ማሞካሸት እና ሌሎችን ከማክበር ይልቅ እንዳላዋቂ እየቆጠሩ ማጥላላት ሀገር ሲጎዳ ቆይቷል። በዚህ ሒደት የበሰበሰ መኖሩን መካድ አይቻልም። ነገር ግን መበስበስን ለማመን ዝግጁነት ካለ መታደስ ይቻላል። ሥነምግባር ያለው ራሱን በራሱ የሚያርም ከሰፊው ሕዝብ ጋር በመከባበር አብሮ ለመጣመር የተዘጋጀ ካለ በሩ ክፍት ነው። ነገር ግን ከማኅበረሰብ ጋር ለመጣመር ከስህተት ነፃ ለመሆን በማያቋርጥ መልኩ ራስን ለማረም ዝግጁነት ያስፈልጋል። ከዚህ በተቃራኒው ሌሎችን ለማሳነስ መሞከር ፍፁም ተገቢነት የሌለው እና የታናሽንም ሆነ የታላቅን ሞራል የሚነካ ኅብረተሰቡን ወደ ኋላ የሚጎትት ነው። አሁን ለደረስንበት ደረጃ ያደረሰን የመረጥነው መንገድ ተቃራኒ በመሆኑ ነው።›› ሲል ያለውን እምነት ገለፀ።

ገብረየስ በበኩሉ፤ ‹‹ዋናው ጉዳይ ግን አሁንም ቢሆን ከሽማግሌዎች እና ከሃይማኖት አባቶች በዕውቀት የዳበረ ሒስ መቀበል ይገባል። ይህ ከመንግሥትም ሆነ ከየትኛውም ዜጋ የሚጠበቅ ሲሆን፤ በሽማግሌዎች በኩልም ያፈነገጠን ማረቅ፤ የሚታዩ እንቅስቃሴዎች በስሜታዊነት በደም ፍላት ሳይሆን በማስተዋል በብልሃት እንዲካሔዱ መስመር ለማበጀት መሥራት አለባቸው። ትውልዱ አንበገርም በማለት መበታተንን በአንድነት መንፈስ በማልፈስፈስ አንድነታችንን እናጠናክር ብለው በሚያግባቡ ጉዳዮች ላይ በማተኮር ማኅበረሰቡ እንዲታነፅ ተደጋጋሚ ትግል ያስፈልጋል። ነገር ግን ይህንን ደግሞ በተለይ መንግሥት በፅኑ መደገፍ አለበት›› ሲል ተናገረ።

ተሰማ፤ ‹‹እኔ በበኩሌ በደም ፍላት የሚንቀሳቀሱትን አልደግፍም። አሮጌ ነገር ሊቆሽሽ እና ሊበላሽ ሊበሰብስ ይችላል። ነገር ግን ሲበሰብስ መታደስ አለበት። በመከባበር እንዲታደስ ማገዝ ይገባል። ከዛ ውጪ ይሉኝታ የሌለው ሰው ለራሱ አዘውትሮ ሽር ጉድ ይላል እንደሚባለው ለራስ ብቻ ክብር እየሠጡ ራስን ተራራ ማሳከል አያዋጣም። የሀገርን እና የሕዝብን ችግር፤ እንዲሁም ደስታን እንደራስ ከማየት ይልቅ እየተስተዋለ እንዳለው የግል ትርፍ እና ዝርፊያ ላይ ማተኮር ድፍረት ከመሆን አልፎ ማንንም የማያድኑር በመሆኑ ከወዲሁ መጠንቀቅ ይገባል።

ልጆችን፣ ወጣቶችን፣ ሽማግሌዎችን እና የሃይማኖት አባቶችን አለማክበር ዘመን አመጣሽ ቅጥ ያጣ ቅንጦት ሲሆን፤ ይህ ቅንጦት እና አመል ማጣት ለሀገሩ ተቆርቋሪ ሕዝብ ለሀገር ዕድገት ኃይል ይሆናል የሚለው ሃሳብ በተቃራኒው እንዲተገበር ያደርጋል። ምንም እንኳ ቅራኔዎች ቢኖሩም ቅራኔዎቹን ለመፍታት መናናቅ፣ መጠላላት እና ጦርነት ውስጥ መግባት ሳይሆን ተከባብሮ በመነጋገር መፍታት ዘመናዊነት ነው። ቅራኔን ተከባብሮ ከመነጋገር ውጪ ራስን በማዋደድ ሌላውን በማዋረድ ላይ ከተመሠረተ የመጠላላት ደረጃውን ከፍ ከማድረግ ውጪ የሚሰጠው ምንም ዓይነት ጠቀሜታ የለም።›› ሲል የሚያስበውን ተናገረ።

ገብረየስ በተሰማ ንግግር ላይ ሀሳብ ለመጨመር ፈልጎ፤ ‹‹በእርግጥም ቅራኔን የመፍቻው ምርጥ መንገድ በመከባበር ላይ የተመሠረተ ሰላማዊ የመወያያ መድረክ ነው። አሁን አሁን እንኳን በውስጥ ከውጪ ኃይልም ጋር ጦርነት ውስጥ መግባት የሚያዋጣ አይደለም። እንደውም የውጪ ጠላትን የማሸነፊያው ጥበብ እርስ በእርስ ተነጋግሮ ችግርን መፍታት እንጂ አስታራቂ ሽማግሌ የሚለውን አልሰማም ብሎ የውጪ ጠላት የመሣሪያ ሽያጭ ገበያን ማሟሟቅ ሞኝነት ነው። ጦርነት ለመክፈት እየተሯሯጡ በተንሻፈፈ መልኩ መቀጠል ቀድሞም ቢሆን እንደማያዋጣ አምናለሁ።

በጦርነት ከመቀጠል በመከባበር ተሳስቦ በመነጋገር ፖለቲካውን አንድ ደረጃ ማሳደግ የተሻለ ነው። ለዚህ ግን ማኅበረሰቡ ፈቃደኛ መሆን አለበት። ማኅበረሰቡ በሽማግሌ ለመመከር፣ ለመነጋገር ችግሩን በፈቃደኝነት ለመፍታት ሲሞክር ማመቻቸት ደግሞ የመንግሥት ድርሻ ነው። ሁለቱም ማኅበረሰቡም ሆነ መንግሥት በተቃራኒው መንገድ ከተራመዱ ያሰቡበት መድረስ አይችሉም። በአንድ አጋጣሚ የተገነባው ሁሉ መፍረሱ አይቀርም። የማኅበረሰብ እሴት እየተሸረሸረ ከፈራረሰ፤ የፈራረሰን ሕዝብ መምራት ስለሚያዳግት አደጋው እስከመበተን የሚያድግ ይሆናል። ለዚህ ሁሉ መፍትሔው መከባበር ነው።

ቀድሞም ቢሆን በሰላማዊ መንገድ ተከባብሮ በአንድነት መኖር ይበልጣል በማለቴ ከፖለቲካው ዓለም ተባርሬያለሁ። በመባረሬ አልከፋም። ነገር ግን ከፖለቲካው ከወጣሁ ከሁለት አሥርት ዓመታት በላይ አስቆጥሬ ያየሁት ተመሳሳይ አለመከባበርን መሆኑ ያሳዝነኛል። በቀዳማይ ኃይለ ሥላሴ ዘመን በተሻለ መልኩ መከባበር ነበር። ነገር ግን መከባበሩ ፍፁምነት የጎደለው ስለመሆኑ አይዘነጋም። ያ ከቀን ወደ ቀን እየጎደለ የቀጠለው መከባበር ንጉሥን እንደፈጣሪ ከማየት ይልቅ ወደ ማዋረድ አሽቆለቆለ። ከላይም ሕዝብን አለማክበር፤ ለሕዝብ ሥልጣን ላለመስጠት ማንገራገር ሙሉ ለሙሉ ሥልጣን አሳጣ። የማኅበረሰቡም የላዩን አካል አለማክበር መልካም ውጤት አላስከተለም።

በደርግ ዘመንም የሃይማኖት አባቶችን እና አዛውንቶችን እንዳላዋቂ ማየት ምክራቸውንም አለማዳመጥ ሀገሪቷን ለከፍተኛ ጦርነት ዳረጋት። አለመከባበር እና አለመደማመጥ ባመጡት ጣጣ ሕዝብ አለቀ፤ ሀገር ወደመ። መሣሪያ ቢቆለልም ሥልጣንን ማጣት የግድ ሆነ። ቀረብ አድርጎ ማነጋገር ሲቻል ጠያቂን ባለማክበር በተፈጠረ ስህተት ሕዝብ አለቀ። አገር ወደመ። በዘመነ ኢሕአዴግም ሆነ አሁን በለውጡ ዘመን በተመሳሳይ መልኩ ከታች ወደ ላይም ሆነ ከላይ ወደ ታች ተገቢው መከባበር ባለመኖሩ ተደጋጋሚ ጦርነቶች ተከሰቱ። የብዙዎች ሕይወት ጠፋ። ሕዝብም ሀገርም ተጎዳ።

ለሁሉም መፍትሔው መከባበርን መሠረት አድርጎ መነጋገር እና መደማመጥ ነው። ቀድሞ በመከባበር ላይ ያልተመሠረተ መነጋገር ባለመግባባት መቋረጡ አይቀርም። ስለዚህ አሁን ላይ ለኢትዮጵያውያን ዋነኛው መፍትሔ ግጭት፣ ማፈናቀል፣ ቂምን መውጣት እና ጦርነት ሳይሆን መሠረታዊው መፍትሔ በመከባበር ላይ የተመሠረተ መመካከር እና መወያየት ነው። አንዱ ሌላውን አክብሮ፤ አንዱ ራሱን በሌላው ቦታ ላይ አስቀምጦ በአንክሮ ካዳመጠ እና ሁሉም ከተደማመጠ የኢትዮጵያ ችግር የሚቃለልበት ቀን ሩቅ አይሆንም። ችግሩ ከመቃለል አልፎ ሙሉ ለሙሉ የሚቀረፍበት ሁኔታም ሊፈጠር ይችላል። ስለዚህ በእኔ እምነት ኢትዮጵያን የሚያድናት መከባበር ነው።›› ሲል ተሰማ ንግግሩን ቋጨ።

ተሰማ፤ ‹‹አንጀቴን አራስከው በእርግጥም ዋነኛው መፍትሔ እርስ በእርስ ተከባብሮ ተመካክሮ ችግርን ማቃለል ነው። ማንም የማንም የበላይ መሆን አይችልም። ማንም ማንንም ተጭኖ እንዲከበር ማድረግ አይችልም። ታናሽ ታላቅን፤ ታላቅም ታናሽን ካከበረ ችግሩ ይፈታል። ይህ የእኔም እምነት ነው። እኛ እርስ በእርሳችን ስንከባበር ዓለም ያከብረናል። ያለበለዚያ እናንተ ‹ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይሸከመውም› እንዳላችሁት በዓለም የተናቅን እንሆናለን። ሽማግሌን ከማክበር እና ታላላቆች የሚሉትን ከመስማት በተጨማሪ እርስ በእርስ ካልተከባበርን በፖለቲካውም ሆነ በኢኮኖሚ መውደቃችን አይቀርም። ውድቀታችን ለጠላቶቻችን ደስታን የሚፈጥርላቸው ከመሆኑም በተጨማሪ፤ ከወደቅንበት እንዳንነሳ እንዳይኮረኩሙን ተጠንቅቀን ተከባብረን ብናድግ ይሻለናል።›› አለ።

ዘውዴም፤ ‹‹እኔም እንደማምነው ግጭት እና ጦርነት ለማንም አይበጅም። የረጋ ደም ጥቁር ሆኖ ጨለማን የሚያሳይ መቅሰፍት ነው። ቆመንም ተኝተንም ስለ ጥቁር ደም ማሰባችን እስከ አሁን ያመጣብንን አይተናል። በኖረው እሴታችን ሽማግሌዎችን በማክበር እና እርስ በእርስ በመከባበር ላይ አድርገን፤ የቀን የሌሊት ሕልማችን በረጋ ደም ምትክ ብሩህ ተስፋ የሚያሳየውን የረጋ ወተት ስናይ ኢትዮጵያ ከሕመሟ ትፈወሳለች። እኛ ኢትዮጵያን ስናከብራት፤ ዓለምም ኢትዮጵያን ያከብራታል።›› ብሎ እንደለመደው ወደ ቤቱ ለመሔድ ከመቀመጫው ተነሳ።

# የዘመን ጥበብ

## “ጎልያድ እማን ፍታት!”

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ሰሞኑን ጥበብና ግጥም ፍቅራቸው ጠንቶ በጫጉላ ቤት ያሉ ጥንዶች መስለዋል። ባለፈው ሳምንት ከብሔራዊ ቲያትር የጀመርነው ጉዞ ዛሬም ከሀገር ፍቅር ደጅ አድርሶናል። ጥበብ ውላ ትግባ እንጂ ማደሪያዋን አታጣም። የዛሬው ርዕሰ ጉዳያችን የሆነው “ጎልያድ እማን ፍታት” የተሰኘው የግጥም መድበል ደራሲዋ ማህሌት ጌታቸው(መልሕቅ) ደግሞ ሦስተኛውን የጥበብ ልጇን ተገላገልኩ ትለናለች። እኛም ‘እንኳን ጥበብ ማረችሽ’ ብለናል።

የማለዳዋ ጀንበር ከወደ ምሥራቅ ወጥታ ከሀገር ፍቅር ሰማይ ላይ የፀሐይ ብርሃኗን ቁልቁል መፈንጠቅ ተያይዛዋለች። ከሐረር የበቀለችው ደራሲዋ ማህሌት ጌታቸው የፀሐይዋን የተፈጥሮ ምህዋር ተከትላ የጥበብ ብርሃኗን በግጥም ሥራዎቿ ልትለግስ በሀገር ፍቅር ተገኝታለች። ለ3ኛ ጊዜ ወግ ማዕረጓን ለማየት የበቃችው ደራሲ ከዚህ ቀደም ሁለት ሥራዎች ጀባ ብላለች። በ2005ዓ.ም “የኔ” የተሰኘውን የግጥም መድብሏን አሰናድታ ለግጥም አፍቃሪያን አድርሳለች። ሁለተኛው ሥራዋ ደግሞ በ2010ዓ.ም በእውነተኛ ታሪክ ላይ ተመርኩዛ የጻፈችው “የቀለጠች ሻማ” የተሰኘው ሥራዋ ሲሆን በሴቶች ጥቃት ላይ የሚያጠነጥን መጽሐፍ ነው። ሴቶች በሴተኛ አዳሪነት ሕይወት ውስጥ የሚደርስባቸውን አካላዊና ሥነ ልቦናዊ ጥቃትን እያተተ ወደ አዲስ የሕይወት መስመር የሚገቡበትን መንገድ ጠቆም ያደርጋል። ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ያነሳሳት ነገር ‘ሜርሲ ቻፕልስ’ በተሰኘ ግብረ ሰናይ ድርጅት ውስጥ በመምህርነት በምታገለግልበት ወቅት ካየችውና ካጋጠሟት ጉዳዮች መነሻነት ስለመሆኑ ትናገራለች። “ሴተኛ አዳሪዎቹን ቀርቦ ጓደኛ በማድረግ እንዲሁም ደግሞ ለምልከታ በእኩለ ሌሊት ብቅ እያልኩ በውጣ ውረድ የተሞሉ ብዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎች አሳልፌ በመጨረሻም ለፍሬ የበቃ መጽሐፍ ነው” በማለት በወቅቱ ስለነበረው ሁኔታም ከማንሳት አልቦዘነችም። በእነዚህ ሁለት መጻሕፍት አልፋ፤ በሁለት እግሮቿ ለመቆም እየታገለች ደግሞ፤ ምርኩዝ የሆናትን 3ኛ ሥራዋን በግጥም ስንኞች አጅባ “ጎልያድ እማን ፍታት” ስትል መጥታለች። የግጥም መድብሉ የተዋቀረበት አካላዊ ቁመና በዋናነትም ፍቅር፣ ሰላም፣ ሀገርና ማህበራዊ ዳርቻዎቻችንን እየተሻገረ እልፍ ጉዳዮችን ያስመለክተናል። ከዚህ በተጨማሪም ደራሲዋ በሰዋሰው ማንነት ውስጥ እየጠለቀች አንዳንድ ጊዜ ከራስ፤ ከተፈጥሮና ፈጣሪ ጋር የሚደረጉ ውስጣዊ ግጭቶችን በጥያቄና ለምን በሚል ምላሽ ፍለጋ ውስጥ ስትዳክር እንገነዘባለን።

**ስምን?**

ለምን ወሰደክብኝ ብቻዬን ፈለከኝ፤
እንዲህ ነው ምትወደኝ?
ቀናተኛ አምላክ መሆንክን አውቃለሁ፤
እንዲህ ከወደድከኝ ውሰደኝ ብያለሁ።
ምክንያቱን አትጠይቀኝ ሁሉን አውቀህ ሳለህ፤
ከልቤ ልኬት ውስጥ ያለውን እያየህ።
አቅቶህ አይደለም ሉዓላዊ እኮ ነህ፤
መልስልኝ ባክህ ባክህ ልለምንህ!
በሱሙ እንዳልጠራው ሰዎች ያውቁብኛል፤
አምላኬ ብቻውን ለኔ ይበቃኛል፤
እንዳልል ሰው ነኝ ሰው ያስፈልገኛል፤
መልስልኝ ባክህ እጅጉን ከፍቶኛል፤
የሆነ ጉድለቴ ህመም ሆኖብኛል፤
ህመም በርትቶብኝ ማውራት ተስኖኛል።
ከሆነ አጥንት ላይ እኔን የፈጠርከው፤
እንድሞላው ነበር እሱን ያጎደልከው፤
መሙላት የተሳነኝ ምን ብትሳሳት ነው።
....
ወይ እኔን ውሰደኝ ለእርሱ ካጎደልኩት፤
ኧረ እንዲያውም ይቅርብኝ ፍቅርን ቱ! አልኩት።

ኅዳር 22 ቀን ረፋድ በሀገር ፍቅር ቲያትር በነበረው በዚሁ የመጽሐፍ ምረቃ ላይ በአሁኑ ሰዓት “የቀድሞ የሐረር ሙዚቀኞች ማህበር”ን መስርተው በ4 ኪሎ የከተሙት የቀድሞው የሰሜን እዝ ኪነት ቡድን አባላትን ጨምሮ አርቲስት ሥዩም ተፈራ፣ ትዕግስት ባዩ፣ ሕይወት አራጌ፣ ቃቂ ተስፋዬና ሌሎች የጥበብ ሰዎችም ታድመውበታል። ጀማሪ ገጣሚያንና ድምጻውያንም የተለያዩ ሥራዎቻቸውን በማቅረብ የመድረኩ ጌጥ ሆነዋል። ማህበራዊ ሚዲያን ለበጎ ተግባር በመጠቀም



ደራሲ ማህሌት ጌታቸው ( መልሕቅ)



ለኪነ ጥበቡና ማህበራዊ ጉዳዮቻችን መነቃቃትን እየፈጠሩ ካሉ የቲክቶክ መንደር ጌቶችም ሌላ ውበት ነበሩ። ሌላው የመድረኩን ድባብ ሞልቶ ዓይን ሳብ ልብ ወሰድ የሚያደርገው የታዳጊ ሕጻናቱ የፋሽን ትርኢት ነበር። በቆንጆ ዲዛይን በተሸመኑ አልባሳት አሸብርቀው ወዲያ ወዲህ ሲሽሞነሞኑ ታይተዋል።

ደራሲዋ ማህሌት ጌታቸው(መልሕቅ)ና “ጎልያድ እማን ፍታት” የተሰናሰኑበት የሕይወት ገጽታ ከመቅድሞቿ በተለይ መንገድ ነው። “ይህን መጽሐፍ ስጽፍ ሀዘን ጥላውን አጥልቶብኝ...በመከፋት የልብ ስብራት ውስጥ በአንድ ዓይኔ ሆኜ ነበር የጻፍኩት” በማለት በሕይወት ጊዜ ውስጥ የተቀዳውን መራራ ጽዋ፤ ዛሬ በጣፋጭና በመልካም የደስታ መዓዛ ተለውጦ ለማየት ስለመብቃቷ ታወሳለች። ግጥም ለገጣሚው ያበጠውን የውስጣዊ ስሜት ማስተንፈሻ የሰላም መርፌ ነው። ከሌሎች የጥበብ ሥራዎች በተለየም ውስጣዊ ማንነትና ስሜትን በማንጸባረቅ እኔነትን አጉልቶ የማሳየት ባህሪ አለው። በገጣሚው ግጥም ውስጥ የራሳችንን የሆነው የሕይወት እንዝርት ሲሾር እንመለከትበታለን። የደራሲዋ የግጥም ስብስቦች በብዛት ከራሷ ሕይወት የቀዳችው ቢሆንም እያንዳንዳችን እራሳችንን እናገኝባቸዋለን። በየጊዜው ውስጣዊ ስሜቶቿን በግጥም ስንኞች እያሰፈረች በማህበራዊ ሚዲያው የቲክቶክ መንደር ብቅ በማለት ስሜቷን ለተከታዮቿ ታጋራቸው ነበር። ይህም በሚያዩዋት ዘንድ መልካም አጋጣሚና እድልን ፈጥሮላታል። ሦስተኛ ልጇ የሆነውን ይህን የግጥም መድብል ለመጽሐፍነት እንዲበቃ የረዷትም እኚሁ በቲክቶክ መንደር የሚያውቋትና የሥራዎቿ አድናቂ የሆኑ ወጣቶች ስለመሆናቸው ተናግራለች። በወቅቱ ከነበረችበት የድባቴ ዓለም የልብ ስብራቷን ተመልክተው፤ እነዚህ የግጥም ሥራዎችሽ እንደ ንፋስ ላይ አቧራ በነው መቅረት የለባቸውም በማለት፤ ሊያ ግሩፕና ሞዴል ዞላን ጨምሮ በሀገር ውስጥና በውጭ የሚኖሩ በርካቶች ተሰባስበው የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ “ጎልያድ እማን ፍታት” ታትሞ ለዚህ ወግ ማዕረግ ሊበቃ ሆነ።

ሰሞነኛው የግጥምና የጥበብ ፍቅር ጠቢባኑን ብቻም ሳይሆን በተለያዩ ጊዜያት የሀገር ባለውለታ የነበሩ ጀግኖችንም በድጋሚ ያስታውሰን ይዟል። በመጽሐፍ ምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ወቅት የቀድሞው የምሥራቅ እዝ የኪነት ቡድን አባላት ስለመገኘታቸው ከላይ ጠቆም ለማድረግ ሞክረን ነበር። ታዲያ እዚህ የመገኘታቸው ምስጢር ግብዣ ብቻ አልነበረም። ‘ጀግና ጀግናን ይወልዳል’ እንዲሉ የደራሲዋ ወላጅ አባት ድምጻዊ ጌታቸው ተሰማ የኪነት ቡድኑ አባል የነበረ በመሆኑ ነው። በመድረኩ ከታደሙ ከእነዚህ አባላቱ መሃከል አንዱ የነበረው ወልደ አማኑኤል ዱባለ እንዲህ ሲል በጥቂቱ ያስታውሰዋል፤ “ከዛሬ 40 ዓመታት በፊት የምሥራቅ እዝ የኪነት ቡድን ለሀገር የሚዋደቁ ጀግና የጦር ሠራዊቶችን ብቻም ሳይሆን በኪነ ጥበቡ አንቱ የተባሉ የጥበብ እንቁዎችንም ሲያፈራ የነበረ ነው። የመንግሥት ለውጥ ሲመጣ ግን እንደቀልድ የቀድሞ የደርግ ሠራዊት ተብለን ተበታተን። ከጊዜያት በኋላም አንድ አስደንጋጭ ነገር ገጠመን። በወቅቱ ኮከብ ድምጻዊና የቡድኑ የመድረክ ፈርጥ የነበረው ግርማ ከበደ፤ ዞር ብሎ የሚያየው አጥቶ ከጎዳና ወድቆና በመጨረሻም ሞቶ ተገኘ። አስከሬኑ ምኒልክ ሆስፒታል ከተመረመረ በኋላ ማዘጋጃ ሊቀብረው ሲሰናዳ ሕልፈቱን ሰማንና ተሰባስበን መጣን። በክብር ግብዓተ መሬቱን ከፈጸምን በኋላ ለምን ቡድኑን ዳግም አናቋቁመው የሚል ሃሳብ ተነስቶ፤ ዳግም ወደምንወደው ሕዝብና ሙያ ተመለስን። ከአዲስ አበባ ባህልና ቱሪዝም ቢሮም እውቅናን አግኝተን ዛሬ በአራት ኪሎ፤ በራሳችን ቤት ውስጥ ተሰባስበን በመሥራት ላይ እንገኛለን። ይህ የመጽሐፍ ምረቃ ለኛ ትልቅ ትርጉም አለው። የእርሷ አባትና የኛ ጓደኛ የነበረው ጌታቸው ተሰማ...ምን ነበር ኖሮ ይሄን ባየ...ሁለገብ የጥበብ ልጅ ነበር። በመረዋ ድምጹ ብቻ ሳይሆን በሙዚቃ መሳሪያውም በኦርጋን፣ በክራር፣ በጊታር፣ በድራምና ሳክስፎኑ ሁሉ ችሎታው ወሰን አልባ ነበር። ነገር ግን 1979ዓ.ም የኪነት ቡድኑ ለኤርትራው ጦርነት ቅስቀሳ ወደ ሰሜኑ ሄዶ ከተገደሉ 17 ሰዎች መሃከል፤ አንዱ እርሱ ሆነና እንደወጣ ሳይመለስ ቀረ። ልጁ ልጃችን ናትና ደስታው የኛም ጭምር ነው...” ሲል፤ ሁሉንም ከትዝታ ቀድቶ በእውነተኛ የስሜት ቋጠሮ ገለፀው።

ደራሲ ማህሌት ጌታቸው በ”ጎልያድ እማን ፍታት” ክንብንብ አምራና አሸብርቃ፤ በግጥም ሥራዎቿም ተሞሽራ ብትታይም፤ መድረኩ ግን የእርሷ ብቻ አልነበረም። ጀማሪና እውቅ ገጣሚያን በመድረኩ ተፈራርቀውበታል። ግሩምና አንጀት አርስ የግጥም ሥራዎች ተደምጠዋል። በዚህ ወቅት ከታዳሚነቱ ባሻገር የተሳታፊነቱንም ዕድል በማግኘት ጥቂት ነገሮችን ለማለት የቻለው አንደኛው የጥበብ ሰው ገና ስንመለከተው የ90ዎቹ የሙዚቃ ጠረን ትውስ እያለን በትዝታ ወደኋላ እንድንጓዝ የሚያደርገንና የደራሲዋ አብሮ አደግ የሆነው ድምጻዊ ቃቂ ተስፋዬ ነበር። መቼም አዳራሹ በሐረር ክዋክብት፤ በድሬ ጠበብት ደምቋልና ቃቂ ተስፋዬም ስለ ሐረር አውርቼ እንዳልጠግብ ሰምቼ እንዳልረካ የሚያደርጉኝ ብዙ ምክንያቶች አሉኝ ሲል “ያልተበረዘች ሀገር፤ ያልተበረዘች ኢትዮጵያ ናት። አባቴ ክርስቲያን እናቴ ሙስሊም...ፍቅር አካል ለብሶ የቆመባት...ሀገር በግጥም ይገነባልና” በማለት እንዲህ ሲል ስለ ሐረር ገጠመላት፤

ሰው ሲሆን ለሀገሩ እንግዳ፤
ታውቃለች ሁሉን አቅርባ አላምዳ።
የሀረሯ ወጣት ቆንጂት፤
ቤት ለንግዳ ስትል አቤት።
ድሪያው ሽርጡ ሲያምርባት፤
ውብ ክንብንብ ጸጉሯ ሽፍኗት።
ሥርዓት ባህሏን አክባሪ፤
አየሁኝ ቆንጆ ከሐረሪ።
ከድሬ ብንወጣም ከሀረር ብንርቅም፤
እንደ አለማያ ሀይቅ ፍቅራችን አይደርቅም።
በምሥራቅ ፀሐይ ጀንበር ደምቃ፤
በጀጎል ግንብ ስር ተደብቃ።
የኖረች ሐረር ውብ ከተማ፤
ውሃ እንጂ ማን ፍቅር ሊጠማ።

በርግጥም ቃቂ አልተሳሳተም። እንኳንስ ሕዝቧና በንፉግነትና በአስቀያሚነት የምንስላቸው ጅቦችም እንኳ የሐረርን አፈር እረግጠው አየሯን ሲምጉ በፍቅር ውቃቢ ተለክፈው ፍቅር ፍቅር ይሸታቸዋል። መሶብሽ መሶቤ፤ ኪስህ ኪሴ ነው እያሉ ተሳስቦ የመኖርን ኢትዮጵያዊነት ዛሬም ቢሆን ከሐረሮች ማጀት አልተንጠፈጠፈም። ፍለጋ ብንወጣ ምናልባትም የምናገኘው እዚያ ይሆናል።

በእለተ ቅዳሜዋ ረፋድ፤ የጥበብ ሰዎችንና ወዳጅ ዘመዱን ከሀገር ፍቅር ያሰባሰበው ዋነኛ ጉዳይ የ”ጎልያድ እማን ፍታት” የግጥም መድብል ምረቃ ስለመሆኑ አይዘነጋም። ከነበሩ በርካታ ዝግጅቶች መገባደጃ ላይ የምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ተካሂዷል። አንጋፋውን የኪነ ጥበብ ደጀን ሥዩም ተፈራን ጨምሮ ሌሎች መራቂ የክብር እንግዶችም በጋራ ሆነው ከታዳሚው ፊት በመቆም መጽሐፉን መርቀው ከመልካም ምኞት ጋር አብስረውታል። “ከመሞቴ በፊት አሥር መጽሐፍትን የመጻፍ እቅድ አለኝ” ስትል በቀልድ ቢጤ የታጀበውን እውነተኛ ሕልሟን ጠቆም ያደረገችው ደራሲ ማህሌት ጌታቸው፤ በሴትነቷ በበቀሉ መንጠቆዎች ሳትያዝና ለስንክሳሮቿ ሳትረታ፤ ሰፊውን የጥበብ አድማስ ዛሬም አሻግራ ትመለከታለች። ከዚህ በኋላ በርካታ መጻሕፍትን ጽፋ የማበርከት ተስፋን እንደሰነቀች አሁን አንድ በጅምር ያለ ሥራ ስለመኖሩ ተናግራለች። የሴት ልጅ ጥቃት የሚያንገበግባት በመሆኗ፤ በጅምር ያለው ይህ መጽሐፏም በዚሁ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው። አሁን ብዙ የሞራል ስንቅና ተስፋን ተሞልቻለሁና እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ አራተኛውን ልጄን እታቀፋለሁ ስትል በልበ ሙሉነት ገልጻለች።

ጥበብ ውበትና ፍካት ለጥበብ እጆች፤ ዳርቻ አልባ ፍቅር ወሰን አልባ ሰላም ለሀገር ልጆች፤ የማይነጥፍ ብዕር የማያልቅ ማህደር ለጥበብ ደጆች...በማለት ብሩህ ተስፋና ለምለም ምኞታችንን በማስከተል፤ በስተመጨረሻም ከ”ጎልያድ እማን ፍታት” የግጥም መድብል አንደኛውን ገጽ በመግለጥ ይቺን ግጥም ጋበዝናችሁ።

**አትሳቅ**

የጥርስ ነጸብራቅ ከሩቅ እየጠራ፤
እንደ ሰብአ ሰገል ያመጣል እያበራ።
ስለዚህ አትሳቅ ፈገግታህ ያመኛል፤
ልትሔድ ነው እያለ ያመላልሰኛል።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## አብርሆት - ለልበ ብርሃኖች

**እዮሩስ ተስፋዬ**

በዓለም ከ46 ሚሊዮን ሰዎች በላይ ዓይነ ሥውራን መሆናቸውን መረጃዎች ያመላክታሉ። 235 ሚሊዮን ሰዎች ደግሞ ከፊል የእይታ ችግር ያለባቸው ናቸው። በኢትዮጵያ ቁጥሩን ይህን ያህል ነው ብሎ ለማስቀመጥ ጥናቶች ባይኖሩም ቁጥሩ ቀላል እንደማይሆን ግን ይገመታል።

ዓይነ ሥውራን ስለሚገጥማቸው ችግር እንዲሁም መፍትሔዎችን ለማመላከት 31ኛው ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ቀንን ምክንያት በማድረግ "አብርሆት ለልበ ብርሃኖች" በሚል መሪ ቃል ለዓይነ ሥውራን በዓይነ ሥውራን የተዘጋጀ የውይይት መርሃ ግብር ሰኞ ኅዳር 24 ቀን 2016ዓ.ም በአብርሆት ቤተ መጻሕፍት ተካሂዷል።

የአብርሆት ቤተ መጻሕፍት ዋና ዳይሬክተር ባየሁ ማሞ (ኢንጂነር) በመርሃ ግብሩ ላይ እንደተናገሩት፤ ከዚህ ቀደም የነበሩት ዓይነ ሥውራን ለመሠረታዊ ትምህርት ያልታደሉ ነበሩ። በአሁን ወቅት ግን በብሬል እና በቴክኖሎጂ በመታገዝ ብዙ ፈተናዎችን አልፈው ውጤታማ የሆኑ በርካቶች ናቸው።

‹‹ዓይነ ሥውርነት ሰውን የሚገልጽ ባህሪ አይደለም፤ በቀላሉ ዕይታቸውን ብቻ የሚነካ ነገር ነው›› ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ነገር ግን በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው ውስጥ ብዙ ችግር እንደሚገጥማቸው ይናገራሉ። በትምህርት፣ በሥራ እና በሌሎች የአካታችነት እጦት ሳቢያ ማህበራዊ ተስፏቸው ይገደባል። በመሆኑም አሁን በመንግሥት እየተሠራ ያለው ሥራ የሚበረታታ ሲሆን፤ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር የሁሉም ኃላፊነት ነው። በመሠረተ ልማት፣ በአካታች ትምህርት እና ልዩ ችሎታቸውን በመጠቀም የሥራ ዕድሎችን በመፍጠርም መደገፍ ያስፈልጋል። ዓይነ ሥውራን በሁኔታቸው ከመገደብ ይልቅ በችሎታቸው የሚከበሩበትን ዓለም በመፍጠር የአብርሆት ቤተ መጻሕፍት ምሳሌ እንደሚሆን የተናገሩት ዳይሬክተሩ፣ በቤተ መጽሐፍቱ ሦስተኛ ወለል ለዓይነ ሥውራን ቦታ በማዘጋጀት ብቸኛው ቤተ መጽሐፍት እንደሆነ ገልፀዋል።

የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ በበኩላቸው፤ ዓለም አቀፉ የአካል ጉዳተኞች ቀን ለ31ኛ ጊዜ ሲታሰብ ‹‹ለአካል ጉዳተኞች ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት እና ለዘላቂ የልማት ግቦች ስኬት ትርጉም ያለው ትብብር›› በሚል መሪ ቃል መሆኑን አስታውሰዋል። እንደ ሚኒስትራ ገለፃ፣ አካል ጉዳተኝነት ከተጠቃሚነት ሊገድብ አይገባም፤ አካል ጉዳተኝነት አለመቻል ሳይሆን ነገሮችን በተለየ መንገድ እና ሁኔታ መከወን መቻል ነው። ማግኘት ያለባቸውን ጥቅም እንዲሁም ተሳታፊነታችን ለማረጋገጥ መሥራት ይገባል።




በመድረኩ ከዓይነ ሥውራን ጋር የተያያዙ የተለያዩ ጥናቶች ቀርበዋል፣

ለአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነት የተለያዩ ሕጎች፣ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ቢኖሩም የተበታተኑ ናቸው የሚሉት ሚኒስትሯ፣ እነዚህን ሰብሰብ በማድረግ የተጠቃለለ የአካል ጉዳተኞች ሕግ አስገዳጅ ሆኖ ሁሉም ሊተገብረው በሚገባ መንገድ ለማዘጋጀት እየተሠራበት እንደሚገኝ ተናግረዋል። አክለውም ጉዳዩ የአካል ጉዳተኞች ብቻ መሆን እንደሌለበትና ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ትርጉም ያለው ትብብር ሲያደርጉ ውጤት ከማምጣት ባሻገር የአካል ጉዳተኞችን ተሳታፊነት ማረጋገጥ እንደሚቻል አብራርተዋል።

በመድረኩ የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ፤ ‹‹አካል ጉዳተኝነት አለመቻል አይደለም። ይልቁንም በውስጥ ያለውን ችሎታ በልዩ ሁኔታ መከወን መቻል ነው። ልዩ ችሎታቸውን እና ብቃትን ለመከወን ግን ድጋፎችን ማድረግ ብሎም ሁኔታዎችን ምቹ ማድረግ ያስፈልጋል።›› ሲሉ ተናግረዋል። በምሥራቅ አፍሪካ ቀዳሚው የሆነው አብርሆት ቤተ መጻሕፍት ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ሁኔታን መፍጠሩ የሚበረታታ እንደሆነ የጠቆሙት ከንቲባ አዳነች አቤቤ፤ የማንበቢያ ቦታ ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን በውስጣቸው ለሀገር የሚጠቅም በርካታ መጻሕፍትን ለአንባቢዎች ማቅረቡ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው ነው። እንደ ከተማ አስተዳደርም ሥራዎች አካታችነትን የሚተገብሩ ለማድረግ አዳዲስ ሕንጻዎች ዲዛይን ሲደረጉ እንዲሁም የቀድሞ ሕንጻዎች ቅርጻቸውን ሳይቀሩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ለአካል ጉዳተኞች ምቹ እንዲሆኑ ተደርገው እየተሠሩ ናቸው። በቀጣይም ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይገባል። ሌሎችም እንዲህ ያለውን ሥራ መተግበር ይጠበቅባቸዋል።

የዓለም አቀፍ ፖለቲካ ሳይንስ እና የዓለም አቀፍ ግንኙነት ተመራማሪ የሆኑት ፕሮፌሰር ዓለምአየሁ ገብረማርያም፤ ቤተ መጻሕፍቱ ከተገነባ ጀምሮ በርካታ ማሕበራዊ ኃላፊነቶችን እየተወጣ እንደሚገኝ በመግለጽ፤ ማኅበረሰቡ አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ ከአስተሳሰብ ጀምሮ ቃላት አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባው ይናገራሉ። ፕሮፌሰሩ እንደገለፁት፤ በ2020 በወጣው የስታቲስቲክስ መረጃ መሠረት 8 ነጥብ 8 ሚሊዮን ሰዎች በተለያየ ደረጃ የማየት ችሎታቸው ቀንሷል። ይህን አስመልክቶ በኅብረተሰቡም ይሁን በመንግሥት በኩል አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ ይገባል።

በኢትዮጵያ ዓይነ ሥውራን ብሔራዊ ማህበር የአካቶ ትምህርት አሰልጣኞች አስተባባሪ አቶ ከተማ ባየልኝ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ መሠረት፤ ዓይነ ሥውራን ለማንበብ ከሚጠቀሙባቸው መንገዶች መካከል ብሬል፣ ኮምፒውተር፣ የድምጽ ቅጂዎች ይጠቀሳሉ። ነገር ግን በትምህርት ቤቶች ‹‹የልዩ ፍላጎት መምህራን ናቸው›› ተብለው ብሬል የሚያስለጥኑ አሰልጣኞች ብቃት አጠያያቂ በመሆኑ መሻሻል ይገባዋል።

ሌላው የብሬል ተደራሽነት ቁጥር አናሳ ሲሆን ፍላጎትና አቅርቦቱን ማጣጣም ይገባል። ከዚህ በተጨማሪም የብሬል ሕትመት ዋጋ መናር ለብሬል ተደራሽነት እንደ አንድ ችግር መሆኑን በመጥቀስ፤ በብሬል ተደራሽነት የመንግሥት ተሳትፎ አናሳ መሆኑ እንዲሁም ዓይነ ስውራን ተማሪዎች የኮምፒውተር ትምህርት እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት እየተማሩት ባለመሆኑ ለእነርሱ አመቺ የሆኑ ሶፍትዌሮችን በመጠቀም ትምህርቱ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ያስረዳሉ።

አቶ ፋሲካ አጌና በአዲስ አበባ ፍትህ ቢሮ አቃቤ ሕግ ናቸው። እርሳቸው ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ ዓይነ ሥውራንም ይሁኑ ሌሎች የማንበብ ችግር ያለባቸው ሰዎች እንደ ማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል የማንበብ እና የማወቅ ፍላጎታቸው ከፍተኛ ነው። ነገር ግን አብዛኛው መጻሕፍት ተደራሽነት ይጎድላቸዋል። በየዓመቱ ከሚታተሙ መጻሕፍት መካከል ለዓይነ ሥውራን እና የንባብ ውስንነት ላለባቸው ተደራሽ የሚሆኑት ከሰባት በመቶ ብቻ እንደሆነ ዓለም አቀፍ ጥናት እንደሚያመላክት በመግለጽ፤ በዚህም ከንባብ የተገፋ ሰፊ ማኅበረሰብ እንዳለ አመላካች ነው ይላሉ። ክፍተቱን ለማጥበብ አካቶ እና ተደራሽ አድርጎ መሥራት ይገባል።

እንደ አቶ ፋሲካ ማብራሪያ፤ መንግሥት ‹‹የማራካሽ ስምምነት›› ፈርሞ አጽድቋል። ስምምነቱም መጻሕፍት ተደራሽ እንዳይሆኑ የሚከለክሉ የቅጂ መብቶች ሕጎች ላይ ገደቦች እንዲሁም ልዩ ሁኔታዎች እንዲካተቱ የማድረግ ዓላማ ያለው ነው። ይህም የሕትመት ውጤቶች በተለይም ለዓይነ ሥውራን እና የንባብ ችግር ላለባቸው ልዩ በሆነ መንገድ እንዲያዘጋጁ የሚያስገድድ ነው። ስምምነቱ መፈረሙ ይበል የሚያሰኝ ሲሆን፤ ከመፈራረም የዘለለ ሥራ ግን ከመንግሥት ይጠበቃል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋ እና የሥነ ጽሑፍ አራተኛ ዓመት ተማሪ ኃይለ ልዑል ምስጋናው፣ ብሬል ማንበብ የቻለው በራሱ ብርቱ ጥረት መሆኑን ይናገራል። እርሱ እንደሚለው፣ ሥርዓተ ትምህርቱ መፈተሽ አለበት፣ ለንባብ አመቺ የሚባሉ ሁኔታዎችም መፈጠር አለባቸው። የብሬል ተደራሽነት ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለማረም፤ ራሱን የቻለ ሥርዓተ ትምህርት መቅረጽ እንደሚገባ የመፍትሔ ሃሳብ ያቀረቡት አቶ ፋሲካ፤ የብሬል ትምህርት ለዓይነ ሥውራን እና ዓይነ ሥውራንን ለሚያስተምሩ መምህራን መስጠት ቢቻል ችግሩን ያቀለዋል።

# ዓለም አቀፍ



## በዓለም አቀፍ የተማሪዎች ምዘና የሲንጋፖር ተማሪዎች በሒሳብና ሳይንስ ትምህርቶች ቀዳሚ ደረጃን ያዙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የሲንጋፖር ተማሪዎች በሒሳብ፣ በሳይንስ እና በንባብ ቀዳሚ ደረጃ መያዛቸውን 38 አባል ሀገራት ያሉት የኢኮኖሚ ትብብር እና ልማት ድርጅት (ኦኢሲዲ) ጥናት አስታውቋል፡፡

ተማሪዎች እውቀታቸውን እና ክህሎቶቻቸውን በተጨባጭ በዓለም ላይ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት ምን ያህል እንደሚጠቀሙ ለመለካት ዓለም አቀፍ የመመዘኛ ጥናት መካሄዱ ተገልጿል።

በዚህም ዕድሜያቸው 15 ዓመት የሆኑ ታዳጊዎች ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገባቸውን ነው ጥናቱ ያመላከተው።

ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ ከ149 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ከ15 የግል ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ ስድስት ሺህ 606 ተማሪዎች ውስጥ ሲንጋፖር በ2022 ዓለም አቀፍ የተማሪዎች ምዘና መርሐ ግብር (ፒሳ) በሒሳብ፣ ሳይንስ እና ንባብ 1ኛ ደረጃን መያዟ ተመላክቷል፡፡

ሲንጋፖርን ተከትለው አየርላንድ፣ ጃፓን እና ደቡብ ኮሪያ ከሁለተኛ እስከ አራተኛ ያለውን ደረጃ መያዛቸው ተጠቁሟል፡፡

በድርጅቱ በየሦስት ዓመቱ የሚካሄደው ጥናት በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ለአንድ ዓመት መዘግየቱም ተጠቅሷል።

ውጤታቸው በ2018 ከነበረው ጋር ሲነፃፀር፣ በፒሳ ምዘና እ.አ.አ. በ2022 የተሳተፉ የሲንጋፖር ተማሪዎች በሒሳብ ውጤታቸውን አስጠብቀው በሳይንስ ከፍተኛ መሻሻል ያሳዩ ሲሆን በንባብ ግን መጠነኛ መቀነስ ማሳየታቸው ተገልጿል።

የሲንጋፖር ትምህርት ሚኒስቴር በሀገሪቱ ተማሪዎች ላይ ያለው የንባብ መቀነስ በሌሎች በርካታ ሀገራት ካሉ እኩዮቻቸው ጋር ተመሳሳይ መሆኑን አንስቷል፡፡

ይህም በዓለም አቀፍ ደረጃ በንባብ ልምድ ላይ ያለውን ለውጥ የሚያንፀባርቅ ነው ሲል መግለፁን ዘ ስትሬይትስ ታይምስ ዘግቧል።

## የአውሮፓ ኅብረት በሽብር ሥጋት የተነሳ ለተጨማሪ የደኅንነት ጥበቃ 30 ሚሊዮን ዩሮ መደበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የአውሮፓ ኅብረት በሽብር ሥጋት የተነሳ ለተጨማሪ የደኅንነት ጥበቃ 30 ሚሊዮን ዩሮ መደበ።

የአውሮፓ ኅብረት የውስጥ ጉዳዮች ኮሚሽን ኃላፊ ይልቫ ጆሃንሰን በእስራኤል-ሐማስ ጦርነት ምክንያት በማህበረሰቦች መካከል የተፈጠረው መካረር የጥቃቶችን ሥጋት እንደጨመረው ተናግረዋል።

በገና በዓል ወቅት በአውሮፓ ኅብረት አባል ሀገራት ውስጥ "ከባድ የሽብር ጥቃት ሊፈጸም ይችላል" የሚል ሥጋትም ማየሉን አመላክተዋል።

በዚህም ሥጋት ምክንያት ኅብረቱ ለተጨማሪ የደኅንነት ጥበቃ 30 ሚሊዮን ዩሮ መመደቡን ጁሃንስን ተናግረዋል። ኃላፊዋ ይህንን ከማለታቸው ከቀናት አስቀድሞ ፓሪስ ውስጥ አንድ ጎብኚ በስለት ተወግቶ ተገድሎ ነበር።

ሆኖም ባለስልጣኗ በፈረንጆቹ የገናና አዲስ ዓመት በዓላት ወቅት የሽብር ጥቃት አለ ለማለት ያስደፈራቸው የተለየ መረጃ ስለመኖሩ ያሉት ነገር የለም።

ጆሃንሰን ከአውሮፓ ኅብረት የሀገር ውስጥ ጉዳዮች ሚኒስትሮች ስብሰባ በፊት በሰጡት አስተያየት "ይህንን ጉዳይ በቅርቡ ፓሪስ ውስጥ አይተነዋል። እንዳለመታደል ሆኖ ከዚያ ቀደምም ተመልክተነዋል" ብለዋል።

በተመሳሳይ የጀርመን የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትርም "ጽንፈኝነትና ስሜት ቀስቃሽ ንግግሮች በበረከቱበት ጊዜ የአውሮፓ ኅብረት የቅርብ ክትትል ሊያደርግ ይገባል" ሲሉ አሳስበዋል።



ባለፈው ቅዳሜ ፓሪስ ውስጥ የ23 ዓመቱ ጀርመናዊ ቱሪስት በስለት ጥቃት ተፈጽሞበት ከተገደለ እንዲሁም ፍቅረኛውና ሌላ የብሪታኒያ ቱሪስት ጉዳት ከደረሰባቸው አንድ ቀን በኋላ የአውሮፓ ኅብረት ለምክክር ተቀምጧል።

ሁለቱ ጀርመናውያን ጥንዶች ኤፍል ታውር (የፓሪስ ዝነኛ ማማን) ጨምሮ በፈረንሳይ የተለያዩ መስህቦችን እየጎበኙ ፎቶ ሲነሱ ነበር ግድያው የተፈጸመው።

በሥፍራው በቁጥጥር ስር የዋለው ተጠርጣሪው ከዚህ ቀደም ከፓሪስ ወጣ ባለ አካባቢ የሽብር ጥቃት ለመፈጸም ሲያሴር ነበር በሚል ታስሯል።

የፈረንሳይ ፀረ ሽብር ዐቃቤ ሕግ የተጠርጣሪውን ባህሪ በተመለከተ እናቱ ሥጋት እንዳላት ገልጻለች።

ባለፈው ሳምንት በገና ገበያ ላይ ጥቃት ሊፈጽሙ ሲያሴሩ እንደነበር የተጠረጠሩና በተለያዩ ቦታ የነበሩ ሁለት ሰዎች ተይዘዋል። በተመሳሳይ በገና በዓል ገበያ ላይ በስለት ጥቃት ሊፈጽም ነበር የተባለ ባለፈው ዓመት ጀርመን የገባ የ20 ዓመት ኢራቃዊ ወጣትም ታስሯል።

የጀርመን የደኅንነት ቢሮ ኃላፊ ከገና በዓል ባሻገር በቀጣይ በሚካሄዱ እንደ ፓሪስ ኦሊምፒክ እና አውሮፓ ሻምፒዮንሺፕ ያሉ ታላላቅ ሁነቶች ላይ ጥቃት ሊኖር እንደሚችል ተናግረዋል። በዚህና በተለያዩ የደህንነት ስጋቶች ምክንያት የአውሮፓ ኅብረት የቁጥጥር ስራዎቹን ማጠናከሩን አስታውቋል።

# ነፃ ሃሳብ

## አማራጭ የባህር በር ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የዲፕሎማሲ አቅምን ማጎልበት

**ታሪኩ ዘለቀ**

ለቀይ ባህር የቀረበው የአፍሪካ ቀንድ ከሌሎች የአፍሪካ ቀጠናዎች ልዩ ገፅታ አለው:: አካባቢው የበለፅገ ታሪክን እና ባህልን ያዘለ የአፍሪካ አካል ነው:: የመንግሥት ምስረታ ታሪክም በአፍሪካ ቀንድ ረጅም ታሪክ አለው:: ከቀኝ ግዛት መስፋፋት በፊት ስር የሰደደ የመንግሥት ምስረታ ታሪክ ያለው ሕዝብ የሚኖርበት አካባቢ ነው:: ቀኝ ገዢዎች ወደ ቀጠናው ሲመጡ በነበረው ሀገር በቀል ሃይማኖትና ታሪክ ላይ ሌላ ታሪክ ይዘው መጥተዋል::

በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቀኝ ግዛት በአፍሪካ ቀንድ በተጠናከረ መንገድ መስፋፋት የጀመረው ስዊዝካናል መከፈቱን ተከትሎ ነው:: የዓባይን ወንዝ ከምንጩ ጀምሮ እስከ ማረፊያው ግብጽ ድረስ ያለውን ለመቆጣጠር ከሚደረግ ፉክክር ጋር የተያያዘ ነው:: የቀይ ባህርን አስፈላጊነት ስትራቴጂክ ሚናን ተከትሎ ቀኝ ገዢዎች አካባቢውን ለመቆጣጠር የነበረው ፉክክር ጋር በተያያዘ የቀጠናችንን ታሪክ ልዩ ያደርገዋል::

በቀዝቃዛው ጦርነት ጊዜም በአሜሪካኖችና በሶቪየቶች/በምዕራባዊያንና በሶቪየት/ መካከል የነበረው ፉክክርና ፍልሚያ በአፍሪካ ቀንድ ላይ በተጠናከረ መንገድ ይንፀባርቅ ነበር:: ይህ ታሪክ በጠለቀ መልኩ ኢትዮጵያንም ይመለከታታል::

ቀይ ባህርና ጂኦ ፖለቲካውን በተመለከተ ጥናት እና ጽሑፍ በማቅረብ የሚታወቀው ሰለሞን ባርናባስ እንደሚገልፀው፤ የቀይ ባሕር አካባቢ ከፍተኛ የዓለም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚደረግበት፣ በርካታ መርከቦች በስዊዝ ካናልና በባብኤል ማንዴብ ሸርጦች የሚተላለፉበት፣ ከዚህ የተነሳም ሀገራት ትኩረት ሰጥተውት ፀጥታው የተረጋጋ እንዲሆን የሚጓጉለት አካባቢ ነው።

ከዚህም ባለፈ በርካታ የአካባቢው ሀገራት በባሕር መተላለፊያው ላይ ጉልህ ተጽእኖ ለማድረግ የሚፈልጉ፣ አንዳንዶች የአካባቢው ሁነኛ አዛዥ መሆን የሚፈልጉበት ዓለም አቀፍ መተላለፊያ መስመር ነው::

አሜሪካ፣ የአውሮፓ ሕብረት፣ ሩስያ፣ ቻይና፣ ጃፓን ወዘተ… በርቀት ከሚገኙ ሀገራት መካከል በቀይ ባሕር ላይ ከፍተኛ ትኩረት አድርገው ከሚንቀሳቀሱ ሀገራት ጥቂቶቹ ናቸው:: በቅርብ ከሚገኙት ደግሞ ሳዑዲ አረቢያ፣ ኢራን፣ ግብጽ፣ የዓረብ ኢምሬት፣ ኳታር፣ እስራኤል፣ ቱርክ፣ ወዘተ… ተጠቃሽ ናቸው።

እንደ ሰለሞን ገለፃ፤ የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት ለቀይ ባህር በጣም ቀረቤታ ያላቸውና ምናልባትም በአካባቢው ሊከሰት የሚችል ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖ በቀጥታና በተዘዋዋሪ ሊጎዳቸው ወይም ሊነካቸው የሚችል ነው:: ኤርትራ፣ ሱዳን፣ ጂቡቲና ሶማሊያ ወይም ሶማሊላንድ የቀይ ባህር አጎራባች ሀገራትና ሌሎቹ አባላትም ቢሆኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴያቸው ከቀይ ባህር ጋር የተቆራኘ ነው::

ለምሳሌ የኢትዮጵያ 90 በመቶ የወጪና የገቢ ንግድ እንቅስቃሴ የሚተላለፈው በቀይ ባህር በኩል ነው:: እነደቡብ ሱዳን፣ ኬንያና ኡጋንዳም ቢሆኑ የንግድ እንቅስቃሴያቸው በቀይ ባህር ላይ የሚተላለፍ ነው:: ስለሆነም በቀይ ባህር የሚደረግ ማንኛውንም ፖለቲካዊ፣ ወታደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወዘተ… እንቅስቃሴዎች አፍሪካ ቀንድ አባል ሀገራትን ጥቅም የሚነካ መሆኑ ግልጽ ነው::

አለፍም ሲል ከቻይና፣ ከጃፓን፣ ከአሜሪካ፣ ከአውሮፓ መጥተው ጅቡቲ ላይ ወታደራዊ መሠረት መጣላቸው ስጋት ቢኖራቸው ነው:: ኢትዮጵያም ተመሳሳይ ስጋት ገብቷታል:: የባህር በር የምትጠቀምበትን አካሄድ እየቀየሰች ትገኛለች:: አሁን ያለው በቀይ ባህርና በኤደን ባህረሰላጤ አካባቢ ያለው ወታደራዊ እንቅስቃሴና የፖለቲካ ውዝግብ ሊያሳስባትም ይገባል::

ስለኢትዮጵያ ስናወራ መጀመር ያለብን ከሕዝብ ቁጥራችን ነው:: ከ120 ሚሊዮን በላይ ነን:: ያለወደብ ካሉ ሀገራት መካከል በሕዝብ ብዛት አንደኛ ነን:: ባለፉት ዓመታት ኢትዮጵያ ያሳየቻው የኢኮኖሚ እድገት ከአፍሪካ ተወዳዳሪ የለውም:: እቅዷም ከማደግ ጋር የተያያዘ ነው:: ኢትዮጵያ በምታስበው የማደግ ጉዞዋን ከቀጠለች ከንግድ ጋር የተሳሰረ ነው::

አስተማማኝ የሆነ የባህር በር ያስፈልጋታል:: እስካሁን የምትጠቀምበት አስተማማኝ ወደብ ጅቡቲን ነው:: አሁን ላይ ኢትዮጵያ ከዓመታዊ በጀቷ እስከ 25 በመቶ የሚሆነውን የምታወጣው ለወደብ ኪራይ በመሆኑ ይህ ደግሞ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጫና ያሳድርባታል::

የባህር በር የአንድ ሀገር የህልውና ጉዳይ ቢሆንም ኢትዮጵያ ግን ከሶስት አስርት ዓመታት በላይ ያለወደብ ኖራለች:: ኢትዮጵያ የባህር በር እንዲኖራት ተጠቃሚ እንድትሆን ከጎረቤት ሀገራት ጋር ጥሩ መግባባት እንዲፈጠር እየተጋች ትገኛለች:: ጎረቤት ሀገራት የሚፈልጓቸውን ነገሮች በስፋት ለማቅረብ ቃል ገብታለች::

በሰጥቶ መቀበል መርህ የሕዳሴ ግድብን ጨምሮ በጋራ ለመጠቀም የሚያስችሉ ሌሎች አማራጮችን ጎረቤት ሀገራት እንዲመለከቱ እየጠቆመች ትገኛለች:: ኢትዮጵያ በተለያዩ ጊዜያት በፖለቲካ ሳቢያ የወደብም ሆነ የባህር በር ተጠቃሚነቷን ማረጋገጥ ሳትችል ቆይታለች:: በታሪክ አጋጣሚ ያጣችውን የባህር በር ተጠቃሚነትን አሁን ላይ ለመጠቀም ጥያቄ ማንሳቷ ተገቢም ሕጋዊም ነው:: የተባበሩት መንግሥታት ያወጣው ዓለም አቀፍ ሕግ ኢትዮጵያ የተጠቃሚነት ጥያቄዋን መፍታት ያስችላታል::

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እ.ኤ.አ 1982 ድንጋጌ አውጥቷል:: በዓለም ላይ የባህር በር የሌላቸው 44ቱ ሀገራት እድል እንዲያገኙ ድንጋጌው በግልጽ ያስቀምጣል:: በዚሁ መሠረት ባህር በር የሌላቸው ሀገራት የባህር በርን የመጠቀም ነፃነት ሰጥቷቸዋል:: የባህር ሀብትን የመጠቀም፣ በባህር የማለፍ መብት አላቸው:: ድንጋጌው የባህር በር ያላቸው ሀገራት የሽግግር ሀገራት ይላቸዋል:: ስለዚህ ቀይ ባህር የዓለም ሀብት ነው ማለት ነው::

ለቀይ ባህር የቀረቡ ሀገራት ደግሞ ከሌሎች ሀገራት የበለጠ ሀብታቸው፣ መውጫቸው፣ መግቢያቸው፣ ማረፊያቸው ነው:: ኢትዮጵያም ከቀይ ባህር 12 ማይል ብቻ የምትርቅ በመሆኗ የመሸጋገርም የመጠቀምም መብት አላት:: ሽግግሩ እንዴት ይፈፀም የሚለውን ሀገራት መነጋገር ያስፈልጋቸዋል::

በተባበሩት መንግሥታት ድንጋጌ ኢትዮጵያ የቀይ ባህርንም ሆነ የህንድ ውቂያኖስን መጠቀም ሙሉ መብት ሰጥቷታል:: በዚህ ደግሞ ሁሉም ሀገራት ይግባቡበታል:: ኢትዮጵያም የተፈጥሮ ሀብቷን በመጠቀም የቀይ ባህር የጋራ ተጠቃሚነት መብቷን ታረጋግጣለች:: ለዚህም ሰጥቶ መቀበል መርህን እንደምትከተል በተደጋጋሚ ወትውታላች:: የምትከተለው መንገድ ሰላማዊ የሆነውን እንደሆነ ግልጽ አድርጋለች::

ኢትዮጵያ ብዙ ሀብት ስላላት በጎረቤቶቿ ሆነ በዓለም ሀገራት የምትፈለግ ሀገር ነች:: በጎረቤቶቿ ሁሉ የምትፈለግ ሀገር እሷ የምትፈልገውን ለማክበር ዝግጁ መሆን አለባቸው:: ለምሳሌ የኢትዮጵያ ወንዞች በሙሉ የሚፈሱት ወደ ውጭ ነው:: አንድም ወንዝ ወደ ኢትዮጵያ የሚፈስ ወንዝ የለም:: ጎረቤቶቻችን በሙሉ ወንዞቻችንን ለመጠጣት ይጠብቃሉ:: በተመሳሳይ ጎረቤቶቻችን በተለይም የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ኢትዮጵያ የምጠብቀውን ሊሰጧት ዝግጁነት ያስፈልጋቸዋል::

ለቀይ ባህር ቅርብ የሆነው የምስራቅ አፍሪካ አካባቢ ሰላም፣ እድገት፣ ፀጥታ በስትራቴጂክ መንገዱ ትልቅ ሸክም ያለባት ኢትዮጵያ ነች:: ኢትዮጵያ አካባቢውን ለማረጋጋት ከሌሎች ሀገራት የተሻለ ልምድም ባህልም አላት:: ረጅም ጊዜ ያስቆጠረ ታሪክ እና ሥርዓተ መንግሥት ግንባታ በኢትዮጵያ ስር የሰደደ ስለሆነ መረጋጋትን የመፍጠር ባህል ብርቱ ነው:: ስለዚህ ከየትኞቹም ሀገራት የበለጠ የስትራቴጂ ኃላፊነት ያለባት ሀገር ነች:: የኢትዮጵያ መረጋጋት ለአካባቢው መረጋጋት ዋስትና ነው:: ኢትዮጵያ ጉንፋን ከያዛት ሁሉም ያስነጥሰዋል:: ኢትዮጵያ ካደገች ሁሉም ያድጋል:: ሁሉም የማደግ ሁኔታ ይፈጠርለታል::

ለአብነት ጅቡቲን ብንመለከት እንኳ ባለፉት 12 ዓመታት ያስመዘገበችው እድገት የሚያስገርም ነው:: ለምን ቢባል ከኢትዮጵያ እድገት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ነው:: ከኬንያ፣ ከሱዳንና ከሌሎች ጎረቤቶቻችን ጋር ያለን ግንኙነት እየተጠናከረ እየሄደ ነው:: በኢኮኖሚም፣ በፀጥታ፣ በሁሉም ዘርፎች ጥሩ ውጤት እያሳየ ነው:: ኢትዮጵያ በፀጥታ ማስከበርም ሆነ በኢኮኖሚ እድገት ለአካባቢው ያላት አስተዋፅኦ ወደር የለውም::

> **ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት እንዲቋቋም መስራች አባል ሀገር ነች:: የተባበሩት መንግሥታት ሲቋቋም ኢትዮጵያ እንዲቋቋም አባል የሆነችው የጋራ ፀጥታን ማዕከል አድርጋ ነው**

ኢትዮጵያ ስትራቴጂክ ቦታ ላይ የምትገኝ በመሆኗ የአፍሪካ እና የመካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ከሚተማመኑባቸው ሀገራት መካከል አንዷ ነች:: ከብዙ ነገር አንፃር ኢትዮጵያ በጥሞናና ከምር ሆነው የሚመለከቷት ሀገር ነች:: ከዚህ ቀደም በኢኮኖሚ ረገድ ከምር ሆነው የሚመለከቷት ሀገራት አልነበሩም:: አሁን ይሄ ተቀይሯል:: ከፀጥታና አካባቢውን ከማረጋጋት አንፃርም የኢትዮጵያ ቁልፍ ሚናዋን እየተጫወተች ትገኛለች::

በርግጥ ኢትዮጵያ ሁልጊዜ ፀጥታዋንና ህልውናዋን የምታስከብረው በራሷ በመመካት ነው:: ከዛም አልፎ ብሎ ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ጀምሮ የራሷን ውስጣዊ አቅም፣ የራሷን ህልውና ለማስጠበቅ ከበይነ መንግሥታት ወይም መልቲላተራል በሆነ ሥርዓት ትደጉመዋለች::

ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት እንዲቋቋም መስራች አባል ሀገር ነች:: የተባበሩት መንግሥታት ሲቋቋም ኢትዮጵያ እንዲቋቋም አባል የሆነችው የጋራ ፀጥታን ማዕከል አድርጋ ነው:: አፍሪካ አንድነትም ሆነ አፍሪካ ህብረት እንዲቋቋም ኢትዮጵያ መስራች ሀገር ነች:: በመሪነትም ደረጃ ያደረገችው አስተዋፅኦ ቀላል አይደለም:: ይሄ ሁሉ በይነ መንግሥታት ወይም መልቲላተራል ተቋማት ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነቷ ደጓሚ ናቸው:: የብሔራዊ ደህንነቷ አጋዥ ናቸው:: ኢትዮጵያም በአፍሪካ ውስጥ ያየለ ሚናዋን እንድትጫወት አጋዥ ናቸው::

ኢትዮጵያ እያነሳችው ያለውን የባህር በር መጠቀም ጉዳይ ከላይ የጠቀስናቸው ተቋማት እንዲያግዟትና በፅሞና እንዲመለከቱት ከጎኗም እንዲቆሙ ማድረግ አለባት:: በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ኢትዮጵያ የባህር በርን መጠቀም ጉዳይ እንደሚያሳስባት ማስገንዘብ መቻል አለባት:: የአፍሪካ ህብረት፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትም ሆነ ለሌላ ተመሳሳይ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጉዳዩን እንዲመለከቱት ማድረግ ያስፈልጋል:: ኃያላን ሀገራት እነአሜሪካ፣ እነቻይና፣ የፀጥታው ምክር ቤት ኢትዮጵያ ያለችበትን ሁኔታ ግንዛቤ እንዲያገኙ ማድረግ ይገባል:: ለዓረብ ሊግ ጨምሮ ለሁሉም መናገር መጀመር አለባት::


ከኬንያ በስተቀር ሁሉም ጎረቤቶቻችን የዓረብ ሊግ አባል ሀገራት ሆነዋል:: በአንድ ማህበር ተደራጅተዋል:: ስለዚህ ይህንን መብታችንን ለማስከበር ከዓረብ ሊግ አባል ሀገራት ጋር የምናደርገው ግንኙነት ወሳኝ ይሆናል:: ስለሕዳሴ ግድብ ስናወራ ስለባህር በር ማግኘታችንም በሰጥቶ መቀበል በሙሉ ልባቸው ሊደግፉልን ይገባል:: ለምሳሌ ግብጽ በዓባይ ውሃ ታሪካዊ መብት እንዳላት ስታነሳ ኢትዮጵያ የባህር በር ማግኘት እንዳለባት ቀድማ መደገፍ እንደሚገባት ማሳመን ያስፈልጋል:: ሌሎች የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራትም ቀድመው ኢትዮጵያ የባህር በር ማግኘቷን መደገፍ አለባቸው:: እንዴት ትጠቀም እንዴት ታግኝ በመነጋገር የሚፈታ ይሆናል::

በተለይ የአፍሪካ ህብረት በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት እንዲሰጠውና የአፍሪካ ቀንድን ሁኔታ በሚያይበት ጊዜ ልዩ ትኩረት ሰጥቶት እንዲመለከተው ማድረግ ያስፈልጋል:: ህብረቱ የጋራ ተጠቃሚነትን ታሳቢ አድርጎ ኢትዮጵያ ውሃ ታካፍል እንዳለ ሁሉ የባህር በር ኢትዮጵያ ልታገኝ ይገባል ብሎ መቀመጥ አለበት::

በአጠቃላይ በይነ መንግሥታት /መልቲላተራል ተቋማት/ አንዱ ተግባራቸው ሰላምና ፀጥታ ጉዳይ ላይ መሥራት ስለሆነ ለዚህም ስኬት ኢትዮጵያ ተመራጭ ሀገር ነች:: ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ የፀጥታ አስከባሪ በማቅረብ /ወታደሮችን በማቅረብ/ ያላት ሚና ተጠቃሽ ነው:: ይህ የሆነው ሀገሪቱ ስለተከበረችና የኢትዮጵያ አስፈላጊነትን ስለተገነዘቡ የተደረገ ነው:: ኢትዮጵያ ያላት ሀብት ብዙ በመሆኑ መደራደሪያም ይሆናል::

በርካታ የመደራደሪያ መሳሪያ አላት:: ኢትዮጵያ ልክ እንደሕዳሴው ግድብ ሁሉ የባህር በር የመጠቀም መብቷን ለማረጋገጥ በዲፕሎማሲያዊ መንገድ ለበይነ መንግሥታት በግልጽ ማሳየት ይጠበቅባታል:: ኢትዮጵያ ዓለም ላይ ያላትን የዲፕሎማሲ ተሳትፎ መሠረት አድርጋ የባህር በር ተጠቃሚነት አቋሟ እንዲደገፍና ፍትሀዊ ጥያቄ መሆኑን ማስረዳትና ማሳመን የሚጠበቅ ተግባር ነው::

# ስፖርት



## የትግራይ ክልል ስፖርትን ለማነቃቃት የተጀመረው ጥረት

**ብርሃን ፈይሳ**

በአትሌቲክስና ብስክሌት ስፖርቶች በኦሊምፒክ የኢትዮጵያን ስም ያስጠሩና መልካም ገጽታና የገነቡ በርካታ ስፖርተኞች ከትግራይ ክልል ተገኝተዋል። በእግር ኳስና ሌሎች ስፖርቶችም በተመሳሳይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድኖችን የወከሉ ጠንካራ ስፖርተኞች ተፈጥረዋል። ይህ ሁኔታ ላለፉት ጥቂት ዓመታት በነበረው ጦርነት ምክንያት ተቀዛቅዞ ቆይተል። አሁን ግን የክልሉን ስፖርት ወደነበረበት ለመመለስ በክልሉ፣ በፌዴራል መንግሥት እንዲሁም በተለያዩ የስፖርት ተቋማት ጥረት እየተደረገ ይገኛል።

ከዚህም ጋር ተያይዞ እስካሁን የተሠሩና ከዚህ በኋላም የታቀዱ ጉዳዮችን በተመለከተ የትግራይ ክልል ስፖርት ኮሚሽነር አቶ ተክላይ ፈቃዱ፤ የክልሉን ስፖርት እንዴት ወደነበረበት መደበኛ እንቅስቃሴ ይመለሳል በሚል የተለያዩ ሥራዎች መከናወናቸውን ይጠቅሳሉ። በዚህ ረገድ በብሔራዊ ስፖርት ማኅበራት አዘጋጅነት በክልሉ የተደረጉ ጥቂት የስፖርት ውድድሮች ተስፋ ያሳዩ ሲሆን፤ ቀጣይነት እንዲኖረውም ስፖርቱን ከሚመሩት አካላት ጋር እየተሠራ ነው። ክልሉ አሁንም ከፍተኛ የፋይናንስ እጥረት ላይ የሚገኝ ቢሆንም ባለው አቅም እንቅስቃሴ ከማድረግ ባለፈ በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚከናወኑ ውድድሮች ላይ ተሳታፊ ለመሆን የተቻለው ሁሉ እየተደረገ ነው።

በጦርነቱ ሳቢያ የክልሉ የስፖርት መሠረተ ልማቶች ውድመት ደርሶባቸዋል፤ ነገር ግን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ወደነበሩበት ለመመለስ የሚያስችል ሥራ አልተከናወነም። ይሁን እንጂ መሠረተ ልማቶቹን ወደ ነበሩበት ከፌደራል መንግሥት ጋር መግባባት ላይ የተደረሰ ሲሆን፤ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች በመኖራቸው ወደተግባር እንዳልተገባ ኮሚሽነሩ ያብራራሉ። «በእርግጥ የማዘውተሪያ ስፍራዎቹ ወድመዋል በሚል ሥራዎች ሳከናወኑ አልቀሩም፣ ይልቁንም ባለው ሁኔታ የትግራይ ካፕ በመቀሌ ስታዲየም እንዲካሄድ እንዲሁም ታዋቂው የአትሌቶች ማሠልጠኛ ማዕከል ማይጨውም ሠልጣኞችን እንዲቀበል ተደርጓል። ክለቦችም ሁሉም ሊባል በሚችል ደረጃ ወደ ሥራ ገብተዋል።» ይላሉ ኮሚሽነሩ።



**የክልሉን የስፖርት መሠረተ ልማቶች ወደ ነበሩበት ለመመለስ ጥረት እየተደረገ ነው፣**

የተፈጠረውን የፋይናንስ ችግር ለመቅረፍ የገቢ ማሰባሰቢያ መርሐ ግብሮች ተጀምረው ወደ እንቅስቃሴ የገቡ ቢሆንም አሁን ላይ የመቀዛቀዝ ሁኔታ ይታይባቸዋል። ይህም መሆነው መርሐ ግብሩን ባዘጋጁ አካላት መካከል በተፈጠረ አለመግባባት መሆኑን ኮሚሽነሩ ይጠቁማሉ። በተለይ በእግር ኳስ ስፖርት የሊጉን ተሳታፊ ክለቦች የመደገፍ ሂደት ላይ የሚገኘው የገቢ ማስገኛ መርሐ ግብርም በሂደት ላይ መሆኑንም ነው የሚያነሱት።

የትግራይ ክልል ጊዜያዊ አስተዳደር ምክትል ፕሬዚዳንት ጄኔራል ጻድቃን ገብረተንሳይ፤ ጦርነቱ ከፈጠረው ጠባሳ ለማገገም ከሚደረጉ ተግባራት መካከል ስፖርት አንዱ እንደመሆኑ የጊዜያዊ አስተዳደሩ ድጋፉን እንደሚያጠናክር ይናገራሉ። በጦርነቱ በነበረው ሁኔታ የደረሰው ውድመት ስፖርቱንም የሚነካ ሲሆን፤ አደረጃጀቱ የመፍረስ፣ ወጣቶችም ወደተለያዩ ሥራዎች የመሰማራት ሁኔታ ታይቷል። ይህም የፈጠረውን የስነልቦና መረበሽ ለማስተካከል ጥቂት ጊዜ ይፈልጋል፤ ነገር ግን የስፖርት ማኅበራትን በመደገፍ ረገድ ስፖርቱን የሚመሩ አካላትን በማደራጀት ክልሉም ድጋፍ በማድረግ ላይ ይገኛል። ከዚህ ባለፈ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ያደረገው አይነት ስፖርታዊ እንቅስቃሴ መነቃቃትን ይፈጥራል። በመሆኑም የስፖርት ማኅበራት ይህንኑ አበርትተው እንዲሠሩ ጥሪ አቅርበዋል። ጊዜያዊ መንግሥቱም ለዚህ የተመቻቸ ሁኔታ በመፍጠርና ሰላምንም በማረጋገጥ ረገድ ቁርጠኛ መሆኑንም አስረድተዋል።

«ስፖርት ሰላም እና የማኅበራዊ ግንኙነትን የሚያሳድግ መሣሪያ ነው» የሚሉት ደግሞ የኢፌዴሪ ባሕልና ስፖርት ሚኒስትር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት ናቸው። በጦርነት ምክንያት ተራርቆ የቆየውን ሕዝብ አንድ የሚያደርገውን የስፖርት ዘርፍ በመልሶ ግንባታም አይነተኛ ሚናን የሚጫወት የሰላም ማጽኛ ቁልፍ መሣሪያ ነው ይላሉ። እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለፃ፣ ስፖርት ወጣቶች ተስፋቸው እንዲለመልምና እንዲታደሱ በማድረግ ብቁ ዜጋ እንዲሆኑ ያደርጋል። የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን እና ብስክሌት ፌዴሬሽን እንዳደረጉት የስፖርት ውድድሮችንና ሌሎች ጉባኤዎችን በክልሉ መደረጋቸው ከፍተኛ ጥቅም ይኖረዋል። በመሆኑም ሚኒስትሩ በዚህ ረገድ በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ ሲሆን ከወራት በፊት በሚኒስትሩ የሚመራና የተለያዩ የስፖርት ማኅበራት አመራሮችን ያካተተ ልዑክ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ጉብኝት ተከናውኗል። ከክልሉ ጊዜያዊ አስተዳደር አመራሮች ጋር በመገናኘትም በጉዳዩ ዙሪያ ውይይት ተደርጓል። አቅም በፈቀደ ሁኔታም ድጋፎች መደረጋቸውን ሚኒስትር ዴኤታው ያብራራሉ።

ክልሉ በተለያዩ ስፖርቶች በርካታ ስፖርተኞችን ለብሔራዊ ቡድን በማፍራት የሚታወቅ ሲሆን እነዚህ ክለቦችና የስፖርት ተቋማት በሃገሪቷ በሚደረጉ ውድድሮች ተመልሰው ለስፖርቱ አቅም የሚሆኑበት ሁኔታም ሊፈጠር ይገባል። ክልሉም በስፖርት ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚሆንበትና ተተኪ ስፖርተኞችም የሚፈሩበት ሁኔታ ለመፍጠርም ከተለያዩ የስፖርት ማኅበራት ጋር ምክክር እየተደረገም ይገኛል። ለአብነት ያህል የኢትዮጵያ ፕሪሚየር ሊግ ድምቀት የነበሩት የክልሉ ክለቦች ወደ ውድድር እንዲመለሱ ከኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ጋር ውይይት ሲደረግ መቆየቱንም ሚኒስትር ዴኤታው ያስታውሳሉ። ሚኒስትሩ ይህንን የመሳሰሉ ሥራዎች በማከናወን ላይ ያለ ሲሆን፤ ብሔራዊ ፌዴሬሽኖች ከክልሉ ፌዴሬሽኖች ጋር በጎንዮሽ በቁሳቁስ፣ በገንዘብ እና ሌሎች ድጋፎች ላይ እንዲሠሩ በማድረግ ረገድም የምክክርና ክትትል ሥራዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉ ይሆናል።

የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን በሚመለከትም ዘመናዊው የመቀሌ ስታዲየም ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ወደ ነበረበት እንዲመለስ ምክረ ሃሳቦችን አቅርቧል። በዚህም ጊዜያዊ አስተዳደሩ ጊዜያዊ መፍትሔ በመፍጠር በባለሃብቶች እገዛ እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ስታዲየሙ ወደ አገልግሎት እንዲመለስ የሚችልበት ሃሳብ ቀርቧል። በማኅበረሰብ አቀፍ የስፖርት እንቅስቃሴም በክልሉ ዋና ከተማ እና የዞን ከተሞች ውስጥ ንቅናቄዎች እንዲደረጉና ተግባራዊ እንዲሆኑም ክትትልና ድጋፍ ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ሚኒስትር ዴኤታው አብራርተዋል።

## ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለስልጣን ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

## የደንብ ማስከበር ተግባር በሚዲያ አቅም

**ስሜነህ ደስታ**

የአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን በአዋጅ 74/2014 በአንቀጽ 47 በአዲስ መልክ ከተቋቋመ ጀምሮ ከጊዜ ወደ ጊዜ የውስጥ አሠራርና የተቋም ሪፎርም በማድረግ አደረጃጀቱን ከማዕከል እስከ ወረዳ ድረስ በማስተካከል ሕዝብና መንግሥት የጣሉበትን ኃላፊነት በመወጣት ላይ የሚገኝ ተቋም ነው። ስለሆነም በከተማው የሚስተዋለውን የደንብ መተላለፍ ይከላከላል፤ ይቆጣጠራል፤ እንዲሁም የእርምት እርምጃ ይወስዳል። ከዚህ ጎን ለጎን ከሌሎች የፀጥታ አካላት ጋር በመተባበር የሕግ የበላይነት እንዲሰፍን ሲሠራ ቆይቷል፤ በቀጣይም ይህን ተግባር ይፈጽማል።

ተቋሙ በአዲስ መልክ ከተቋቋመ ጀምሮ በተሰጠው ተልዕኮ መሠረት ከባለድርሻ አካላት ጋር የስምምነት ሰነድ ተፈራርሞ በየሦስት ወሩ የዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ያደርጋል። የ2016 ዓ.ም. ዕቅድን ለመተግበር በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ከ23 የመንግሥት ተቋማት ጋር የትስስር ሰነድ ተፈራርሞ ወደ ተጨባጭ ተግባራዊ ሥራ በገባው መሠረት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት አፈጻጸም ግምገማ ከባለድርሻ አካላት ጋር ኅዳር 4 ቀን 2016 ዓ.ም. መድረክ በማዘጋጀት አካሄዷል። ባለድርሻ አካላቱም አሉ የሚሏቸውን ጠንካራና ሊስተካከሉ የሚገባቸውን ጉዳዮች አንስተው ምክክር ተደርጎባቸዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን የትስስር ሰነድ ከተፈራረመባቸው ጋር ብቻ ሳይሆን ከሌሎች አካላትም ጋር ስለሥራ አፈጻጸሙ ለመወያየትና ለመመካከር፤ እንዲሁም ሊስተካከሉ ይገባል ለሚባሉ ጉዳዮች አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ ነው። ለዚህ ማሳያ የሚሆነው በራሱ አነሳሽነት ለሁሉም የሚዲያ አካላት ጥሪ በማድረግ «የደንብ መተላለፎችን ለመቀነስ የሚዲያ አካላት ሚና» በሚል መሪ ቃል ኅዳር 7 ቀን 2016 ዓ.ም. የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ በማዘጋጀት ምክክር ማድረጉ ነው።

ለአንድ ሀገር እድገት ሚዲያ ትልቅ ጉልበትና አቅም አለው። ለዚህም ነው የሠለጠኑትና ያደጉት ሀገራት መንግሥታት ከሚዲያዎቻቸው ጋር ተናበውና ተቀናጅተው በመሥራት ለሀገራቸው ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ተግተው የሚሠሩት። ሁለቱ ተባብረውና ተግተው በመሥራታቸውም የሀገራቸውን አጀንዳ ወደ ዓለም ይዘው ቀርበው በማስተጋባት ትልቅ ለውጥ ማምጣት ችለዋል።

በዚህ መነሻ ሀሳብ የአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ባዘጋጀው የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ የባለሥልጣኑ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ ደሳለኝ ፋፋ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር ውስጥ በአዋጅ ቁጥር 150/2015 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ አፅድቆ ወደ ሥራ እንድንገባ የሰጠንን አዲሱን የቅጣትና የእርምት እርምጃ ግልጽ ለማድረግ፤ ከዕርምትና ከቅጣት በፊት መከላከልና ግንዛቤ ማስጨበጥ ቀዳሚ አድርገን ስለምንሠራ ለዚህ ደግሞ ሚዲያ ትልቅ አቅምና ጉልበት ነው። ባለሥልጣኑ እየሠራ ያለውን ሥራ እንዲሁም የፀደቀውን ደንብ ለኅብረተሰቡ በአግባቡ ግንዛቤ በመስጠት ተደራሽ እንድታደርጉልን በአክብሮት እጠይቃለሁ ብለዋል። በከተማዋ የሚስተዋለውን የደንብ መተላለፍና ተያያዥ ሕገ ወጥ ጉዳዮችን ለመከላከል የሚዲያ አካላት ከባለሥልጣኑ ጋር በመቀናጀት ርብርብ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን ምክትል ሥራ አስኪያጅና የቅድመ መከላከልና ሥልጠና ዘርፍ ኃላፊ፣ ወይዘሮ አበባ እሸቴ በበኩላቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነድ አቅርበዋል። ሰነዱ ሲዘጋጅ ዓላማ ያደረገው፣ በባለሥልጣኑ አሠራርና በይበልጥ በአዲሱ ደንብ 150/2015 ላይ ከሚዲያ አካላት ጋር የተሻለ መግባባት ላይ ለመድረስና ሚዲያዎች ባላቸው ተደራሽነት መሠረት በከተማዋ የደንብ መተላለፍ እንዲቀንስ የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡና አብሮ ለመሥራት እንዲያስችል ነው።

ወይዘሮ አበባ ስለተቋሙ አመሠራረትና አሁን ስለደረሰበት ደረጃ እንዲሁም ባለሥልጣኑ ያከናወናቸውን ተግባራትና እያከናወናቸው ያሉትን ሥራዎች ሰነዱን መሠረት አድርገው አብራርተዋል። የደንብ መተላለፍ የሚባሉትን የመሬት ወረራ፣ ሕገ ወጥ ግንባታ፣ ሕገ ወጥ የመሬት መስፋፋት፣ ሕገ ወጥ ጎዳና ንግድ፣ ሕገ ወጥ መንገድ አጠቃቀም፣ ሕገ ወጥ ማስታወቂያ፣ ሕገ ወጥ እንስሳት እርድና ዝውውር፣ ሕገ ወጥ ደረቅ ቆሻሻና ፍሳሽ አወጋገድ እና አዋኪ ተግባር መሆናቸውን በመጥቀስ ለተሳታፊ የሚዲያ ባለሙያዎች ግንዛቤ ሊያስጨብጥ በሚችል መልኩ አቅርበዋል። አዲስ በፀደቀው በአዋጅ ቁጥር 150/2015 ላይ ለደንብ መተላለፎች የወጡ የቅጣት ሰንጠረዦችን በመተንተን አስረድተዋል።

ተሳታፊ የሚዲያ ባለሙያዎችም፣ የአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን የሚዲያ አካላትን ስለሚያከናውነው ሥራ ግንዛቤ ይዛችሁ ተባብረን እንሥራ ብሎ ሥልጠና መስጠቱ እንዲሁም ስለሠራቸው ተግባራት የሚዲያ ባለሙያዎች እንዲተቹበት ማድረጉ በጣም የሚያስመሰግነው መሆኑን ጠቅሰዋል። እንዲሁም አዲስ በፀደቀው በአዋጅ ቁጥር 150/2015 ላይ ለደንብ መተላለፎች የወጡ ቅጣቶችን በሰንጠረዥ ተንትኖ በማቅረብ እንዲረዱ በመደረጉ፤ የቀረበው መረጃ ለሁሉም ተሳታፊ በመስጠቱ፤ ለኅብረተሰቡ ለማስረዳት በጣም አጋዥ እንደሆነ ተናግረዋል። ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ የደንብ ማስከበር አባላት የሚያሳዩትን የሥነ ምግባር ግድፈቶች የሚታረሙበት አግባብ እንዲፈጠር አሳስበዋል። ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ለሚዲያ አካላት በሩን ክፍት የሚያደርግበት አሠራር እንዲዘረጋ መድረኩን ለሚመሩ አመራሮች ጠይቀዋል።

መድረኩን የመሩት የባለሥልጣኑ ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ ደሳለኝ ፋፋ፣ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ አበባ እሸቴ እና የባለሥልጣኑ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ተስፋሁን አሉላ ናቸው። ከሚዲያ ባለሙያዎቹ ለተነሱ አስተያየቶችና ጥያቄዎች ከመድረክ መሪዎቹ ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቷል።

በምላሻቸውም፣ የሚዲያ ባለሙያዎቹ በንቃት ሰነዱን መከታተላቸውን አድንቀው፤ የደንብ ማስከበር አባላት በሚያሳዩት የሥነ ምግባር ግድፈትም ሆነ ሌላ ያልተገባ ተግባር ባለሥልጣኑ ከሚወስደው አስተዳደራዊ እርምጃ በተጨማሪ በህግ እንዲጠየቁ የማድረግ ሥራ ስለሚሠራ የሚዲያ አካላት ኅብረተሰቡ በነፃ የስልክ መስመር 9995 መረጃዎቹን በደንብ አጠናቅሮ ጥቆማ እንዲሰጥ የማሳሰብ ሥራ ማከናወን እንደሚጠበቅባቸው አስገንዝበዋል። ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ለሚዲያ አካላት በሩን ክፍት የሚያደርግ ሲሆን፣ ከሚዲያ ተቋማት ሳይላኩ የተዛባ መረጃ የሚያስተላልፉትን ለመለየት የሚደረግ ማጣራት እንደሚከናወን ጠቅሰው ለቀጣይ ከባለሥልጣኑ አመራሮች ጋር ትውውቅ ስለተደረገ በቀጥታ ማግኘት እንደሚቻል፤ ወደፊት የሚያጋጥም ክፍተት ካለም እየተስተካከለ እንደሚሄድ ተገልጾል። በመጨረሻም የደንብ ማስከበር ተግባር በሚዲያ አቅም ሊታገዝ እንደሚገባ መግባባት ላይ በመድረስ ውይይቱ ተጠናቋል።